ሁለት መቶ ሰማንያ አንደኛ ክስ

ወንጀሉ

በ1949 ዓ.ም. የወጣውን የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ለ እና 522/1/ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ በግፍ ሰው መግደል ::

የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሹ ሰውን ለመግደል አስቀድሞ በማሰብ ፀረ አብዮተኞችና የኢህአፓ አባላት ናቸው በሚል ምክንያት በማድረግ ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ :-

1. ቄስ ቦጋለ ሙሉዓለም
2. ወ/ት ጥጋብ መንግስቱ
3. ስበው ሰረፌ ይማም
4. ስማኝ አለባቸው ውቤ

የተባሉትን በቁጥራቸው ስር የነበሩትን ሚያዚያ 18 ቀን 1970 ዓ.ም. ሰዓቱ በትክክል ሊታወቅ ባልተቻለበት ጊዜ ጐንደር ከተማ ውስጥ ዓይነቱ ባልታወቀ መሳሪያ በጥይት በተለይ ጨካኝ ነውረኛ በሆነ ሁኔታ ተደብድቦ እንዲገደል በማድረጉ ተከሷል ::

ሁለት መቶ ሰማንያ ሁለተኛ ክስ

ወንጀሉ

በ1949 ዓ.ም. የወጣውን የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ለ እና 522/1/ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ በግፍ ሰው መግደል ::

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሹ ሰውን ለመግደል አስቀድሞ በማሰብ ፀረ አብዮተኛና የኢድህ አባል ነው በሚል ምክንያት በማድረግ ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ፡-

አዳባ ዘገዬ

የተባለውን በቁጥጥር ስር የነበረውን ሚያዚያ 18 ቀን 1970 ዓ.ም. ሰዓቱ በትክክል ሊታወቅ ባልተቻለበት ጊዜ ጐንደር ከተማ ውስጥ ዓይነቱ ባልታወቀ መሳሪያ በጥይት በተለይ ጨካኝ ነውረኛ በሆነ ሁኔታ ተደበድቦ እንዲገደል በማድረጉ ተከሷል ::

ሁለት መቶ ሰማንያ ሶስተኛ ክስ

ወንጀሉ

በ1949 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ለ እና 522/1/ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ በግፍ ሰው መግደል ::

የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሹ ሰውን ለመግደል አስቀድሞ በማሰብና ፀረ አብዮተኛና የኢድህ አባል ነው በሚል ምክንያት በማድረግ ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ፡-

ቄስ አበራ ቸኮል

የተባለውን በቁጥጥር ስር የነበረውን ግንቦት 2 ቀን 1970 ዓ.ም. ሰዓቱ በትክክል ሊታወቅ ባልተቻለበት ጊዜ ደብረታቦር ከተማ ውስጥ ዓይነቱ ባልታወቀ መሳሪያ በጥይት በተለይ ጨካኝ ነውረኛ በሆነ ሁኔታ ተደብድቦ እንዲገደል በማድረጉ ተከሷል ::

ሁለት መቶ ሰማንያ አራተኛ ክስ

ወንጀሉ

በ1949 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ለ እና 522/1/ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ በግፍ ሰው መግደል ::

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሹ ሰውን ለመግደል አስቀድሞ በማሰብ፡ ፀረ አብዮተኞችና የኢ.ህ.አ.ፓ አባላት ናቸው በሚል ምክንያት በማድረግ ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ፦

1. ወ/ሮ ታደሰ ደገፋ በዳሶ
2. ወ/ሮ አዳሙ አበራ ሳልህ
3. ወ/ሮ ሲሳይ ቦጋለ ጥላዬ
4. ወ/ሮ ዓለማየሁ አዱኛ በየነ

የተባሉትን በቁጥጥር ስር የነበሩትን ግንቦት 2 ቀን 1970 ዓ.ም. ሰዓቱ በትክክል ሊታወቅ ባልተቻለበት ጊዜ ደባርቅ ከተማ ውስጥ ዓይነቱ ባልታወቀ መሳሪያ በጥይት በተለይ ጨካኝ ነውረኛ በሆነ ሁኔታ ተደብድበው እንዲገደሉ በማድረጉ ተከሷል ::

ሁለት መቶ ሰማንያ አምስተኛ ክስ

ወንጀሉ

በ1949 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ለ እና 522/1/ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ በግፍ ሰው መግደል ፦

የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሹ ሰውን ለመግደል አስቀድሞ በማሰብና ፀረ አብዮተኛና የኢ.ህ.አ.ፓ አባላት በሚል ምክንያት በማድረግ ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ፦

1. ጌታሁን ቦጋለ
2. ዓቢ ዓለም ዘለቀ
3. ሰጠ ዓለም በሪሁን
4. ግርማይ ብርሃኔ ገ/መስቀል

የተባሉትን በቁጥጥር ስር የነበሩትን ግንቦት 18 ቀን 1970 ዓ.ም. ሰዓቱ በትክክል ሊታወቅ ባልተቻለበት ጊዜ ጐንደር ከተማ ውስጥ ዓይነቱ ባልታወቀ መሳሪያ በጥይት በተለይ ጨካኝ ነውረኛ በሆነ ሁኔታ ተደብድበው እንዲገደሉ በማድረጉ ተከሷል ::

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ሁለት መቶ ሰማንያ ስድስተኛ ክስ

ወንጀሉ

በ1949 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ለ እና 522/1/ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ በግፍ ሰው መግደል::

የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሹ ሰውን ለመግደል አስቀድሞ በማሰብና ፀረ አብዮተኛና የኢ.ዲ.ህ አባል ነው በሚል ምክንያት በማድረግ ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ :-

ወ/ር ገብረሕይወት ታረቀኝ

የተባለውን በቁጥጥር ስር የነበረው መጋቢት 15 ቀን 1970 ዓ.ም. ሰዓቱ በትክክል ሊታወቅ ባልተቻለበት ጊዜ ባልታወቀ ስፍራ ዓይነቱ ባልታወቀ መሳሪያ በጥይት በተለይ ጨካኝ ነውረኛ በሆነ ሁኔታ ተደብድቦ እንዲገደል በማድረጉ ተከሷል ::

ሁለት መቶ ሰማንያ ሰባተኛ ክስ

ወንጀሉ

በ1949 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ለ እና 522/1/ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ በግፍ ሰው መግደል::

የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሹ ሰውን ለመግደል አስቀድሞ በማሰብ ፀረ አብዮተኛና የኢድህ አባል ነው በሚል ምክንያት በማድረግ ህግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ :-

አባተ ዓለማየሁ

የተባለውን በቁጥጥር ስር የነበረውን ግንቦት 22 ቀን 1969 ዓ.ም. ሰዓቱ በትክክል ሊታወቅ ባልተቻለበት ጊዜ ፣ አይክል ከተማ ውስጥ ዓይነቱ ባልታወቀ መሳሪያ በጥይት በተለይ ጨካኝ ነውረኛ በሆነ ሁኔታ በገመድ ተሰቅሎ እንዲገደል በማድረጉ ተከሷል ::

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንተኛ ክስ

ወንጀሉ

በ1949 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ለ እና 522/1/ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ በግፍ ሰው መግደል ::

የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሹ ሰውን ለመግደል አስቀድሞ በማሰብና ፀረ አብዮተኛ በሚል ምክንያት አድርጎ ህግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ :-

ፋንቱ ካሳ

የተባለውን በቁጥጥር ስር የነበረውን ነሐሴ 15 ቀን 1970 ዓ.ም. ሰዓቱ በትክክል ሊታወቅ ባልተቻለበት ጊዜ ጐንደር ከተማ ውስጥ ዓይነቱ ባልታወቀ መሳሪያ በጥይት በተለይ ጨካኝ ነውረኛ በሆነ ሁኔታ ተደብድቦ እንዲገደል በማድረጉ ተከሷል ::

ሁለት መቶ ሰማንያ ዘጠነኛ ክስ

ወንጀሉ

በ1949 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ለ እና 522/1/ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ በግፍ ሰው መግደል ::

የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሹ ሰውን ለመግደል አስቀድሞ በማሰብና ፀረ አብዮተኛና የኢ.ህ.አ.ፓ አባላት ናቸው በሚል ምክንያት በማድረግ ህግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ :-

1. ደሳለኝ ላቀው
2. ምስጋናው አካልነህ
3. አለምነሽ ኃ/ማርያም
4. ትውረስ ገብረየስ
5. ሙሉሰው ቃጨር
6. አስፋ አመኑ

የተባሉትን በጎንደር ከተማ ውስጥ ዓይነቱ ባልታወቀ መሳሪያ እንዲገደሉ በማድረጉ

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ተከሳል ::

ሁለት መቶ ዘጠናኛ ክስ

ወንጀሉ

በ1949 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ለ እና 522/1/ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ በግፍ ሰው መግደል ::

የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሹ ሰውን ለመግደል አስቀድሞ በማሰብና ፀረ አብዮተኛና የኢ.ህ.አ.ፓ አባላት ናቸው በሚል ምክንያት በማድረግ ህግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ :-

1. አበባው ፀጋዬ
2. ፍቃዱ ፀጋዬ

የተባሉትን በቁጥጥር ስር የነበሩትን በየካቲት ወረ 1970 ዓ.ም. ትክክለኛ ቀኑና ሰዓቱ ሊታወቅ ባልተቻለበት ጊዜ ጐንደር ከተማ ውስጥ ዓይነቱ ባልታወቀ መሳሪያ በጥይት በተለይ ጨካኝ ነውረኛ በሆነ ሁኔታ ተደብድቦ እንዲገደል በማድረጉ ተከሳል ::

ሁለት መቶ ዘጠና አንደኛ ክስ

ወንጀሉ

በ1949 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ለ እና 522/1/ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ በግፍ ሰው መግደል ::

የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሹ ሰውን ለመግደል አስቀድሞ በማሰብና ፀረ አብዮተኛና የኢ.ህ.አ.ፓ አባል ነው በሚል ምክንያት በማድረግ ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ

ዳዊት ገብረእየሱስ

የተባለውን በቁጥጥር ስር የነበረውን በየካቲት ወር 1971 ዓ.ም. ትክክለኛ ቀኑና ሰዓቱ ሊታወቅ ባልተቻለበት ጊዜ ጐንደር ከተማ ውስጥ ዓይነቱ ባልታወቀ መሳሪያ በጥይት በተለይ ጨካኝ ነውረኛ በሆነ ሁኔታ ተደብድቦ እንዲገደል በማድረጉ ተከሳል ::

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ሁለት መቶ ዘጠና ሁለተኛ ክስ

ወንጀሉ

በ1949 ዓ.ም.የወጣውን የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ለ እና 522/1/ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ በግፍ ሰው መግደል ፡፡

የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሹ ሰውን ለመግደል አስቀድሞ በማሰብና ፀረ አብዮተኞች ናቸው በማለት ፡ ምክንያት በማድረግ ፡ ህግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ፡

1. አራጋው ጓንጉል
2. ክብብ ፈረደ
3. እንዳለው በዜ
4. አንዳርጌ አበበ
5. አባተ ዓለማየሁ

የተባሉትን በቁጥር ስር የነበሩትን በጥር 29 ቀን 1970 ዓ.ም. ሰዓቱ ሊታወቅ ባልተቻለበት ጊዜ ፡ ደብረታቦር ከተማ ውስጥ ዓይነቱ ባልታወቀ መሳሪያ በጥይት በተለይ ጨካኝ ነውረኛ በሆነ ሁኔታ ተደብድበው እንዲገደሉ በማድረጉ ተከሷል ፡፡

ዮሴፍ ኪሮስ
ልዩ ዐቃቤ ሕግ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ይህ ትክክለኛ ግልባጭ
ከይግባኝ ባይ የጸረሰጠችበት ቀን — 21/4/1998 ዓ.ም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

የወ/መ/ቁ/03112
ህዳር 2ቀን 1998

ዳኞች፡-ሰለሞን አረዳ
ሐፊዝ አባጀማል
ረዳኢ በላይ

ከሣሽ፡-ልዩ ዐ/ሕግ ዩሴፍ ኪሮስ ቀርበዋል፡፡
ተከሣሽ ፡-በእነ ሻለቃ መላኩ ተፈራ ከማ/ቤት ቀርቧል
ተ/ጠበቃ ፋንታሁን ገላነህ አልቀረቡም የላቸውም
መዝገቡ በቀጠሮ ያደረው ለምርመራ ሲሆን ፍ/ቤቱም መርምሮ ተከታዩን ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ፤

ተከሣሹ ተከላከል የተባለው በልዩ ዐ/ሕግ ከቀረቡበት ክስ፡-

1) በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ለ እና 281/ሀ ሥር
በድርጊት 55 የተጠቀሰው አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 74 የተጠቀሱት ከስድስት ሰዎች ግድያ በስተቀር
በድርጊት 88 የተጠቀሰው አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 104 ከተጠቀሱት ውስጥ አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 105 ከተጠቀሱት ውስጥ አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 115 የተጠቀሱት ሁለት ሰዎች ግድያ በስተቀር
በድርጊት 118 የተጠቀሱት አምስት ሰዎች ግድያ በስተቀር
በድርጊት 149 የተጠቀሱት ሶስት ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 193 የተጠቀሰው አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 197 የተጠቀሱት ሁለት ሰዎች ግድያ በስተቀር

ስለ ትክክለኛ ግልባጭ

ECHN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

በድርጊት 207 የተጠቀሱት ሁለት ሰዎች ግድያ በስተቀር
በድርጊት 211 የተጠቀሰው አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 231 የተጠቀሰው አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 232 የተጠቀሰው አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 248 የተጠቀሰው አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 257 ከተጠቀሱት 45ሰዎች አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 259 ከተጠቀሱት 45ሰዎች አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 260 የተጠቀሱትን አስራ አንድ ሰዎች ግድያ በስተቀር
በድርጊት 262 የተጠቀሱትን ስምንት ሰዎች ግድያ በስተቀር
በድርጊት 274 የተጠቀሰውን አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 275 የተጠቀሰውን አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 276 ከተጠቀሱት አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 277 የተጠቀሰውን ሁለት ሰዎች ግድያ በስተቀር
በድርጊት 286 የተጠቀሰውን አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 287 የተጠቀሰውን አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 288 የተጠቀሰውን አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 289 የተጠቀሱትን ስድስት ሰዎች ግድያ በስተቀር
በድርጊት 291 የተጠቀሰውን አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 292 የተጠቀሰውን አንድ ሰው ግድያ በስተቀር
በድርጊት 261 የተጠቀሱትን ሰማንያ ሶስት ሰዎችግድያ በድምሩ 149 ሰዎች ግድያ በስተቀር በተቀሩት ድርጊቶች በብይኑ በተገለፀው መሠት በድምሩ 583 ሰዎች ግድያ ተሳታፊነት በልዩ ዐ/ሕግ ማስረጃ በመረጋገጡ።

2/ በወንጀለኛ መ/ሕግ ቁጥር 32/1/ ለ እና 522/1/ሀ መሠረት ራሱን ችሎ የቀረበው ክሳድ የግፍ አገዳደል ክስ ሥር፣

በክስ 295 ከአንድ ሰው ግድያ
በክስ 301ከአንድ ሰው ግድያ
በክስ 348 ከአንድ ሰው ግድያ
በክስ 388 ከአንድ ሰው ግድያ
በክስ 396 ከአንድ ሰው ግድያ
በክስ 422 ከአንድ ሰው ግድያ
በክስ 441 ከሁለት ሰው ግድያ
በክስ 452 ከሁለት ሰው ግድያ
በክስ 456 ከአንድ ሰው ግድያ

220

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

በክስ 464 ከአንድ ሰው ግድያ

በክስ 467 ከአንድ ሰው ግድያ

በክስ 528 ከአንድ ሰው ግድያ

በክስ 537 ከአንድ ሰው ግድያ በድምሩ አስራ ስድስት /16/ ሰዎች ግድያ በስተቀር በሌሎች ክሶች በብይኑ የተገለፁትን በድምሩ 392/ሶስት መቶ ዘጠና ሁለት/ ሰዎች ግድያ ተሳታፊነት በልዩ ዐ/ሕግ የሠውና የሰነድ ማስረጃ በመረጋገጡ፡፡

3/ በወ/መ/ሕ/ቁ/ 538 መሠረት ሆን ተብሎ ስለተደረገ ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ በሚል ክስ ስር

በክስ 554 ከተጠቀሰው አንድ ሰው ላይ አካል ጉዳት ማድረስ

በክስ 567 ከተጠቀሰው አንድ ሰው ላይ አካል ጉዳት ማድረስ

በክስ 575 ከተጠቀሰው አንድ ሰው ላይ አካል ጉዳት ማድረስ

በድምሩ ሶስት ሰዎች ላይ አካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል በስተቀር በሌሎች በብይኑ በተገለፁት ክሶች የተጠቀሱትን በድምሩ በሰማንያ ሶስት ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ማድረሱ በልዩ ዐ/ሕግ ማስረጃ በመረጋገጠ እንደሆነ መዝገቡ ያስረዳል፡፡

ተከሣሹም ክሱን ለመከላከል በመከላከያ ማስረጃነት ያቀረበው ማስረጃ

ሀ/ የሰው መከላከያ ምስክር በተመለከተ መሃላ ፈጽመው የመሰከሩት 1ኛ መ/ምስክር ታደሰ ደገፋ በዳሳ፡-

የመጣሁት ለምስክርነት መሆኑን አውቃለሁ፡፡ ከተከሣሹ ጋር ጠብ ሆነ ዝምድና የለኝም ተከሣሽን የማውቃቸው ኢ.ህ.አ.ፓ ይዞኝ በዚህ ምክንያት ታስሬ በነበርኩበት ነው፡፡ በምህረት የተፈታሁት በሰባት ወሬ በእሳቸው/ተከሣሹ/ ነው፡፡ ብዙ ሰው ታስሮ ነበር አዳሙ አበራ፣ሲሳይ ቦጋለና ዓለማየሁ አዱኛ አብረን ነበረ አዳሙ ሞቷል ሲባል ሰምቻለሁ መሞቱን አላየሁም፡፡ ጎንደር ነው የነበረው እኔና ሲሳይ አብናት ወረዳ ነበርን ሞቷል መባል አልሰማሁም የአዳሙ አብራ አያት ስም አላወቅም አንድ ላይ ነው የታሰርነው የተፈታነውም አንድ ላይ ነው፡፡ በእዬ ኃ/ስላሴ ጊዜ ከሐረር ወደ ጉንደር በወታደርነት የመንግስት ሥራ ተዛወሬ ወደ 30 ዓመት ቆይቻለሁ እዚሁ ቦታም ልጆችና ቤት አሉኝ ከእኔ ጋር የታሰረ መዓት ሰው ነበረ አንተዋወቅም የሰረኝ የጊዜው መንግስት ነው በማለት መስክረው ተመልሷል፡፡

2ኛ መ/ምስክር አስር አለቃ ሲሳይ ቦጋለ ጥላዬ የመጣሁት ከደብዳቤው እንደተረዳሁት ሻለቃ መላኩ ከተከሰሱበት መ/ምስክር ሆኜ ነው በደንብ አላውቃቸውም፡፡ አሁን ግን አየሁዋቸው በዚያን ወቅት በደርግ የሰሜን ጎንደር አስተዳዳሪ ነበር ፀብ ሆነ ዝምድና የለንም ታች ጋይንት ወረዳ በነበረኩበት ጊዜ በእብናት ሚሊሻ ሊያስታጥቁ ሊመጡ አያቸዋለሁ፡፡ ግንቦት 1970ዓ/ም አስር ቤት ነበርኩ፡፡ የታሰርኩት ጃን አሞራ ወረዳ በነበርኩበት ጊዜ ጥር ወር 1970ዓ/ም በኢ.ህ.አ.ፓ ተማርከን ከጓደኞች ጋር ታስረን

ፀለ ትክክለ ግልባጭ

221

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ሰንብተን ስንለቀቅ ስሜን አውራጃ ደባርቅ አውራጃ ሄድን አውቃቸሁ ነው መሣሪያ የሰጣችሁ የተማረካችሁም ኢ.ህ.አ.ፓ ናችሁ በማለት ታስረን እስከ ጳጉሜ 5ቀን 1970ድረስ ከዛ መስከረም 2 በዓልን ምክንያት በማድረግ በምህረት ተብሉ 1500 ሰዎች ተፈትተናል። ከተፈታን የማስታውሳቸው 1ኛ መ/ምስክር የነበሩት ታደሰ ደገፍ ጓደኞች ወ/ር አለማየሁ አዱኛ ግንቦት 1996 ዓ5ም. በእግዚአብሔር ታሞ የሞተው ወ/ር አዳሙ አበራ የአያቱን ስም አላውቅም አራት ነን ፋሲል ደስ ማዘጋጃ አዳራሽ የ3ቀን ነው የአራት ቀን ትምህርት ተሰጥቶን/የንቃት/1500 ሰው በአንድ ጊዜ ተፈታን አብዛኛውን ብዙ ወጣት ተማሪ ነው። የማስታውሰው አንድ አቶ ንጉሤ ተሰማ ከነልጆቻቸው አስታውሳለሁ የቆላ ዱባ ሰው ነበሩ። የታሰርነው በደባርቅ አውራጃ ፖሊስ ተጠርተን በማርቼዲስ ወደ ጎንደረ መጥተን አንደኛ ፖሊስ ጣቢያ እንደገባን የሳቸው/ተከሣሹ አስፔሻሉች መቶ አለቃ አበራ በተባለው ወደ ምርመራ ቦታ ተወስደን ዋልን ለምንድነው መሣሪያ የሰጣችሁ በሚል በጥፊ በእርግጫ ተደበደብን ተታኩሥናል ከአቅማችን በላይ ነው አልን የታሰርነው የካቲት 5ቀን 1970ዓ/ም እስከ ጳጉሜ 5ቀን 1970ዓ/ም ድረስ ነው። ጉንደር ማ/ቤት ከአሁን በፊት ባህርዳር ጠ/ፍ/ቤት እንደዚሁ በእነ መቶ አለቃ አበራ/የእሳቸው አስፔሻሉች/ ተጠርቼ ተጠይቄአለሁ። እንደኢንፎርሜሽን የሰማሁት ተገድለዋል ተብዬ ነው ከዚየም ሰምቻለሁ በማለት መስክረው ተመልስዋል።

3ኛ መ/ምስክር ዋና ሳጅን ዓለማየሁ አዱኛ በየነ አድራሻዩ ፎኖተሠላም ወረዳ 01 ቀበሌ የቤት ቁ.1229 ነው ባህርዳር ትራፊክ ፖሊስ ነኝ የመጣሁት በሻለቃ መላኩ ተፈራ መ/ምስክርነት ትፈለጋለህ ተብዬ በመ/ቤቴ መሸኛ ተሰጥቶኝ ነው እኔ የማውቃቸው በኢ.ህ.አ.ፓ. ምክንያት በታሰርኩ ጊዜ ተከሣሽ የጎንደር ክ/ሀገር የኢሠፓ አንደኛ ፀሐፊ ነበር ዘጠኝ ወር ከሶስት ወይም ከአራት ቀን ታስሬ መስከረም 1ቀን 1970ዓ/ም በአብዩት በዓል ምክንት ተብሉ በምህረት ተለቃችኋል በሻለቃ መላኩ ተፈራ ትዕዛዝ ተብለን 210ሰዎች ተለቀናል የታሰርነው ብዙ ነው መዓት ሰው ነበር ከዚህ መሀል ነው የተፈታነው 210ሰው የሶስት ቀን የንቃት ሕግ ተሰጥቶን ነው የተለቀቅነው በሲኒማ አዳራሽ ሌሉችም አብረውኝ ታስረው የነበሩና የተፈቱ ታደሰ ደገፋው አዳሙ አበራ፣ ሲሳይ ቦጋለ፣ የሚባል ፖሊስ የነበረ ከማዕከላዊ ምርመራ ወደ ማ/ቤት ሄደናል። በእከሌ አይልም በአብዩታዊ ዘመቻ ኮሚቴ የሞት ፍርድ ተፈርዶብኝ እነደነበር ሰምቻለሁ። ከወጣሁ በኋላ ከነበርነው እስረኛ ውስጥ እርምጃ የተወሰደበት አለ ስንለቀቅ የቀሩም ነበሩ ኢ.ህ.አ.ፓ አባል ናችሁ እየተባሉ ነው። የሚወጡ የነበረው በአራታችን ላይ የሞት ፍርድ ተፈርዶብን እንደነበረ ያወቅኩት እዛ የአብዩታዋ ዘመቻ ኮማቴ አባል የነበሩ ሌሎች ባለሥልጣኖች በክልል ሶስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የተከሰሱ አሉ እነሱ በሕይወት ስላሉ ቀርበው ይመስክሩልን ብለው ቀርበን ስላስረዳን ነው። በ1993ዓ/ም እስር ቤት በቆየንበት ጊዜ እርምጃ የተወሰደባቸው ሰዎች ይህ ነው ማለት አልችልም

ትክክል ግልባጭ

223

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ለምሣሌ ተጣርቶ ይወጣል አንድ ሰው የት እንደሚሄዱ አላውቅም ዓይኔ እስካለዩ ይሄ ተደርገዋል። ማለት አይቻልም። ይጠራል ይሄዳል ለፍቼ ነው የሚባለው ሁሉም በስም ሞክሼ የታሰረ ሌላ ታደሰ ደገፋ የሚባል አልነበረም ዓለማየሁ የሚባል የአባቱን ስም የማላውቀው ልብስ ሰፊ ነበር ምን ያህል እስረኛ እንደነበረ ማወቅ አይቻልም የተለያየ ክፍል ስለሆነ አራታችን የታሰርነው በተለያየ ቀን ነው የተፈታነው ለዘጠኝ ወር ቆይተን መስከረም 1ቀን 1970 ዓ/ም ስንፈታ የቀሩ ነበሩ ከተፈታን በኋላም ምህረት ተሰጥቶ ተፈትተዋል ኢ.ህ.አ.ፓ ተብለን ነው አራታችን ከመታሰራችን በፊት ብዙም አንተዋወቅም በፖሊስነቴ ሲሳይ ቦጋለን አውቃለሁ እስር ቤት ነው የተገናኘነው ሲሳይ የሚባል ሌላ ሰው አልነበረም አደሙ አበራ የሚባል አላውቅም አማራ ጠ/ፍ/ቤት ሄጀ የመሰከርኩት ገደሉ ተብሉ ክስ ስለቀረበባቸው ነው።

ተከሣሽ ግንቦት 23ቀን 1996ዓ3ም የተፃፈ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 142/3/ መሠረት የተከሣሽነት ቃል ሰጥቷል ይዘቱም

1/ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ዘመነ መንግስት የተፈፀመው ሕጋዊ ተግባራትን ወደ ኋላ ሄዶ በሕገወጥነት የሚፈረጅ ክስ ማቅረብም ሆነ መቀበል አይቻልም።

ይህች አገር በታሪክ ብዙ እውነታዎች ከተፈራረቁባት አንዱ የ1966 አብዩት ከመሪ ድርጅት አስቀድሞ ሕዝባዊ አብዩት ስለአጥለቀለቀ ለውጭ ወራሪ ሀይል በር እንዳይከፍተና ሥርዓቱ እንዳይደፈርስ በልዩ ልዩ የጦር ክፍሉች የተመረጡ አስተባባሪ ኮማቴ አባል ለመሆን በቃሁ።

በማንም ፈቃድ ያልመጣውና ሊቀር የማይችለው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ሊመራ የሚችል የተደራጅ የፖለቲካ /አካል/ ስላልነበረ ጠንካራ የድርጅታዊ መዋቅር ተዋረድና ትጥቅ መለዩ ለባሽ ዘንድ በመኖሩ አጣዳፊ ለነበሩት ድርቅ ሴክተር ሪቪው የታክሲ ነጅዎች ጥያቄ የተማሪዎች እንቅስቃሴ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዩች ከፍተኛ ሠላማዊሰልፍ.....ወዘተ መንግስት ትኩረት ሣይሰጥ የመለዩ ለባሹን ደመወዝ የመጨመር እርምጃ ወስዶ ጭማሪወና የተገባለት ቃል የሠራዊቱን ብሶት ያስታገሰ ቢመስልም በዚህ እነዳይገታ በነበረው የሕዝብ ጥያቄና ግፊት ለአገሪቱ ታማኝ መሆን ይቻል ዘንድ የንጉሠ ነገሥቱን ሥልጣን ከጥያቄ ውስጥ መክተት አስፈለገ። አስተባባሪ ኮሚቴው የዘውድ አገዛዝ ለማራመድ ቢሞክርም ከእንግሊዝ አዘጋሚ ለውጥ ይልቅ ሕዝባዊ ግፊት የፈረንሣይና የሩሲያን አብዬቶች ሥር ነቀል ባህርይ ያዘ የወቅቱን ለዘብተኛ ካቢኔ በፀጥታ ኮሚሽን አማካይነት ሕዝባዊውን ማዕበል ለመግታት የተደረገው ሙከራ ይልቁንም የካቢኔውን ውድቀት አፍጥነው ሰፊው ሕዝብ ሥርነቀለል ለውጥ እንዲደረግ ጠየቀ ቢሆንም አልጋወራሹ ንጉስ መሆን እንደሚችል በአዋጅ አሳውቀን ንጉሠ ነገሥቱ በይፋ አውርድን ለመሬት ላራሹን ሌሉች ለውጦች ሁኔታዎች አመቻችን

ስለ ሕክሰ ግልባጭ

223

ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ከባህሪያቸው አኳያ ከአዲሱ አውነታ ጋር መጓዝ ሲያቅታቸው ሕብረተሰቡ በማያቋርጥ የዕድገት ሂደት ነውና ሕገ መንግስቱ ከአሮጌው መንግስት ጋር ይወድቃል የአውሮፓ የዘውድ ሥርዓትና ዘውዳዊ ሕገ መንግስታት በአዝጋሚና በሥር ነቀል የለውጥ ሂደት እየወደቁ የመጡት በዚህ ሁኔታ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ከዚህ ሁኔታ ያላመለጠችው በዚህ ምክንያት አንጂ በደርግ አባላት የግብረአበርነት ወንጀልና አድማ የተነሳ አልነበረም የጊ.ወ.ለመንግስትና የሊ/መንበሩን የሚወስነው አ/ቁጥር 2/1967 መታወጅ ጊዜያዊ መስተዳደሩም በአጭር ጊዜ ውስጥ የመንግስታትና ዓለም አቀፍ ጅርጅቶች ዕውቅና አገኘ በ1967 መባቻ ላይ ደርግን በተቃራኒው እንደለዘብተኛ የሚመለከቱ ኃይሎች ብዙ ነበሩ ሶሻሊዝም አንድነው መጓዝ ያለብን በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መርህ ብቻ ነው ተባልን በዚህ ጉዳና አብረን ተጓዝን የተመረጠው ጉዳና የአንድ ፖርቲ በቸኛ የበላይነት የሚያሰፍን ነበርና በዚህ የሥልጣን እረካብ ላይ ብቻቸውን ለመፈናጠጥና መልሰው እኛ ኑ ለመደፍጠጥ የደረጉት ጥረት ያልተሳካላቸው ሁሉ የተገላቢጦሽ የእኛኑ ማርክሲስትነት ካለ በኋላ ይህ ክስ የተመሰረተብኝ ሰዎች በ1966-1967 በአብዛኛው የተማሪው እንቅስቃሴ ተሳታፊዎት የኋላ ኋላ የዕድገት በሕብረት ዘማቾች የነበሩ እንደመሆኑ ቢያንስ የአድማው አነሳሾች እንደነበሩ ዘንግተውት ይሆን መልሱ መልሱ ፍ/ቤት ህሊና እተዋለሁ፡፡

ለአንድ አገር መንግስት አመራር የሚሰጥ መስተዳዳር ከአመጣጡ ከአስራሩ ከአስተዳደሩ ከፖሊሲው ወዘተ አኳያ ውግዘት ወይም ትችት በእርግጥ ሊደርስበት ይችላል ይሁን እንጂ የተወገዘው ወይም የተተቸዉ መስተዳዳር ሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት ሕገ ወጥ ነበር ማለት አይደለም የወጡ ሕጉች ቢሻሻሉ በቀድሞ ሕግ የታሰሩ ሕገወጥ ነበሩ ማለት አይደለም ተጽዕኖው በአንድ ወቅት ሊቀር የሚችል ሆኖ ሳለ ከቀጠለ ኢ.ፍትሐዊ ነበር ማለት ይቻላል ዳሩ ግን ፍ/ቤቶች ወደ ኋላ ሄደው የዚያን ወቅት ሕጋዊ ድርጊት በሕገወጥነት የሚፈርጅ ክስ የማየት ስልጣን እንዳይኖራቸው ብቻ አይደሉም ሕጋዊነቱን ጭምር የመቀበል ግዴታ የአለባቸው መሆኑን አዋጅ ቁ.1/1934 አንቀጽ 5 አዋጅ ቁ/3/1987 አንቀጽ 2/3 የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች አዋጅ አንቀጽ 11/2 እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስ አንቀጽ 22 መሠረት እንዲሁም ከፍ ብሉ በተዘረዘረ ምክንያቶች በጊዜያዊ ወታደራዊ አ/ደርግ ዘመነ መንግስት የተፈፀሙ ተግባራት በተፈፀሙበት ወቅት የሚያስቀጡ ወንጀሎች እስካለነበረ ድረስ ወደ ኋላ ሄዶ ድርጊቶችን መክሰስ ሕጋዊ አይደለም ተቀባይነትም አይኖረውም፡፡

የተከሰሰበት ወንጀል ተግባር አልፈፀምኩም እንዲፈፀምም አላደረግኩም ለመፈፀምም ሆነ ለማስፈፀም ሐሳብ ዓላማና ፍላጉት አልነበረኝም የፖለቲካ ትስስሩ አባላትም እንዲገደሉ አላደረግኩም፡፡

ስለ ሕከክለ ማልባጭ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ተከላከል በተባልኩባቸው ድርጊቶች ሁሉ ልዩ ዐ/ሕግ ወንጀሉን ለመፈፀሜ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ውጪ በሰውም ሆነ በሰነድ ስላላስረዱብኝ እንደገና አንዲያጤነው የክሱ ማመልከቻ ሕግን ያልተከተለና ግልጽነት የጉደለው መሆኑን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 111 እና 112 በመጥቀስ 56 ድርጊቶችን የማድያውን ቀንና ወር አይጠቅሱም 271 ድርጊቶች የማድያውን ሥፍራ አይገልፁም 280 ድርጊቶች ደግሞ የማድያውን መሣሪያ አይገልፁም ራሱን ችሉ የቀረበው ክስና አካል በማጉደል በቀረበው ክስ ላይ 6 ድርጊቶች የማድያውን ሰዓት ቀንና ወር አይገልጽም፡፡

156 ድርጊቶች የማድያውን ቦታና መሣሪያ አይገልጹም፡፡ 5 ድርጊቶች ጭራሹን ሰዓት ቀን፣ወር፣ዓ/ም የማድያውን ሥፍራና መሣሪያ የማይገልጽ ሲሆን የአካል ጉዳት በማድረስ ተፈፅመዋል በተባለው የወንጀል ዝርዝር ውስጥ ከድርጊት 567 እስከ 592 ያሉትን በሙሉ የማድያውን ሰዓት ቀን፣ወር፣ዓ/ም የማድያው ሥፍራና መሣሪያን እየገልጽም 576ኛ እና 581ኛ ድርጊቶች ጭራሹኑ ሰዓት ቀን፣ወር፣ዓ/ም የማድያው ሥፍራና መሣሪያ የማይገልፁ መሆኑን

መሠረታዊ የሆነ የማስረጃ መርሆዎች በብይኑ መታለፍ አግባብነት አይደለም የልዩ ዓ/ሕግ የሰወ ማስረጃም ክሱን አላስረዱም ሥርዓቱ የፈጠራቸው ተጉጂዎችና ተፈራጆች በሐሰትና በተበቃይነት ተከሣሾችን ወንጅለዋል ተከሣሾችን አበጠልጥለዋል የማጋለጥ ዘመቻም አካሂደዋል፡፡ ጅቡቲ በስደት ላይ እያለሁ በኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ ወታደሮች ጥይት ተደብድቤና ታፍኜ ወደ ኢትዮጵያ ከመጣሁ በኋላ እስከዛሬ በእስር በመማቀቅ ላይ እገኛለሁ ይህም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9/4 እና ሰብአዊ መብቶች አዋጅ የተደነገገውን የሚጥስ ነው፡፡

ልዩ ዐ/ሕግ በተጉጂነት ወይም በተፈራጅነት አቋም ይዘው በተከሣሾች ላይ ሊመስክሩ የሚችሉ መረጃና ጥቆማ ሊመሰጡ ተከሣሾችን ለማስቀጣት ከልዩ ዐ/ሕግ ጽ/ቤት ጋር ቆርጠው ለተነሱና ለተባበሩ ሰዎች ሁሉ የገንዘብ ጉርሻ የጉዳት ካሣ የጡረታ አበል ከኪራይ ነፃ ቤት የሥራ ቅድሚያ ዋስትና እንደሚያገኙ ቃል ገብቶ በተከሣሾች ላይ ክስ ከተመሠረተበት ጊዜ ድረስ በመንግስት መገናኛ ብዙሃን አውታሮች ቅስቀሳና ጥሪ ሲያደርግ መቆየቱ ምልመላም ሲያካሂድ መቆየቱ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/31/1 የሚቃረን አሰራር ነው ይህም በጉንደር ከተማና ልዩ ልዩ ሥፍራዎች በአ/አበባ ከተማ በዳግሚዊ ምኒሊክ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት አዳራሽ በወረዳ 11 ፍ/ቤትና በየመንገዱ የተካሄደብኝ የስም ማጥፋት ዘመቻ የተሰባሰቡ ምስክሮች ናቸው በቀጥታ ማስረጃ የተደገፈ አይደለም፡፡

የልዩ ዐቃቢ ሕግ የቴክኒክ ማስረጃ ቀጥተኛ በሆነ የኤክስፖርት ምስክር ተደግፎ የቀረበ ባለመሆኑ አጠራጣሪ ነው፡፡

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

በአንድ ችሎት መታየት የሚገባው ጉዳይ በተለያዩ ችሎቶች መታየቱ ተከሣሽ ስለሚጎዳኝ በ1ኛ እና 6ኛ ወንጀል ችሎቶች ሐምሌ 13ቀን 1990ዓ/ም ያቀረብኩት የክስ መቃወሚያ በ13/10/94 የልዩ ዐቃቢ ሕግ ማስረጃ የሰጠሁት መቃወሚያ አስተያየት በ3/13/95 ያቀረብኩት ተጨማሪ መቃወሚያ አስተያየት ውሣኔ ለማግኘት ሲገባቸው ወደ ጉን ታልፈው የልዩ ዐ/ሕግ ማስረጃ አንድም ሣይቀር ተቀባይነት አግኝቶ እንድከላል ብይን መስጠቱ አግባብ አይደለምና ውሣኔ እንዲሰጥባቸው።

በወ/መ/ሕ/ቁ/32/1/ለ/ እና 281/ሀ የተመለከተም የወ/መ/ሕ/ቁጥር 281 በፖለቲካ ተሳስሮ የተቋቋመውን የሕብረብሔርን ማህበራዊ የሆነ አንድ ክፍል ወይም በክስ ማመልከቻው የፖለቲካ ቡድን የሚል መጨመሩ በጀኖሳይድ ኮንቬንሽን A/RES/260A/111/ ዲስሞር 9 ቀን 1948 ያላከተተው ስለሆነ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ክስ ነው ፈራሚ አገሮች ከተቀበሉት በኋላ በራሳቸው ፍላጉትና አነሳሽነት የኮንሼኑን አንቀጾች በማስፋትና በማጥበብ መለወጥ እንደማይችሉና የኮንቬኑም አንቀጾች አንድነትና ሙሉነት ስምምነቱ በፀደቀበት ጊዜ ከነበረው ሁኔታ እንዲጠብቁ የኢንተርናሽናል ሕግ መርህ የሚያስገድድ መሆኑን ፈራሚ አገር የማሻሻያ ሀሳብ ካለው ጥያቄውን ለተባበሩት መንግስታት በጽሁፍ ማቅረብ እንዳለበት እንጂ የሰው ልጆችን ሰብአዊ መብት ለማስፋት በሚል ኮንቬክሽኑ ሊያሻሽለው ሥልጣን ስላልተሰጠው አይችልም የፌዴራል ሕገ መንግስቱም ይህ እንዳይሆን በአንቀጽ 9/4፣13/2፣እና 9/1 አጥብቆ ይከላከላል።

በሩዋንዳ ቀድሞ ይጉዝላቪያ በአሁኑዋ ይጉዝላቪያ የተፈፀመውን የዘር ማጥፋት ወንጀል ክስ በኢንተርናሽናል ፍ/ቤት ለመዳኘት የተደረገው አካሄድና አፈፃፀም ከጀኖሳይድ ትርጉም ጋር ፍፁም ተመሣሣይ መሆኑንና በፖለቲካ ተሳስሮ የተቋቋመውን የሕብረብሔርን ማህበራዊ የሆነ አንድ ክፍል ሕዝብ ወይም የፖለቲካ ቡድን የሚለውን አለመጨመሩን

በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች አዋጅ አንቀጽ 11/2 እና ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22 /1 መሠረት በፖለቲካ ተሳስሮ የተቋቋመውን የሕብረብሔርን ማህበራዊ የሆነ አንድ ክፍል ሕዝብ ወይም የፖለቲካ ቡድን የሚለውጥ በጀኖሳይድ ኮንቬንሽን ትርጉምና ድንጋጌ ውስጥ እንደ ወንጀል ያልተጠቀሰ በመሆኑ የወንጀል ሕጉ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሠራ ስለሆነ የወንጀል ክሱን እንዲሰረዝ ሕጉ ማስገደዱ

የ1948 የኢትዩጵያ ሕገ መንግስት ለ1949 ዓ/ም ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረትና የበላይ በመሆኑ በተመሣሣይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት ለ1949 ወንጀለኛ መቅጫው ሕግ የበላይ መሆኑን በአንቀጽ 13/2 ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ሕገ አካል መሆናቸውን ከመግለጽ በወንጀለኛ መቅጫው የተካተተው የፖለቲካ ቡድን የሚለው ከፍ ብለው ከተገለፁት ሕገ መንግስቶችና ከጀኖሳይድ ኮንቬንሽኑ ጋር

ECLN

ልክ ትክክል ግልባጭ

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

በተቃረነ የተካተተ ስለሆነ መተርጉምም ያለበት ከአለም አቀፍ መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ስላለበት ስምምነቱን በመለወጥ በፖለቲካ ተሳስሮ የተቋቋመውን የሕብረብሔርን ማህበራዊ የሆነ አንድ ክፍል ሕዝብ ወይም የፖለቲካ ቡድን የሚል በመጨመር የዘር ማጥፋት ወንጀል ክስ ለማቅረብ የማይቻልና የቀረበውን ቢሆን መሠረዝ ያለበት መሆኑን

የጀኖሳይድ ኮንቬንሽን ለብሔራዊ ሕጉች የበላይ በመሆኑ በጀኖሳይድ ኮንሼንሽን አንቀጽ 5 የኮንቬስኑና አንቀጾች በሕጋቸው ውስጥ አስገብተው በመደንገግ ኮንቬንሽኑና ተግባራዊ ለማድረግ ግዴታ ገብተዋል የዘር ማጥፋት የሚመለከተውን ወንጀል ትርጉም እንዳለ በኢትዩጵያ የ1949 ዓ/ም ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጸ 281 ውስጥ መካተቱ የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት ቁጥር 1 ተ.ቁ 2 የሚያስረዳ ስለሆነ ከኢንተርሽናል መርህ ውጪ መሆኑን በመግለጽ ክፍ ብሉ በተገለፀው ምክንያት የሕግ መሠረት የሌለው ክስ በመሆኑ እንዲያስረዝና ተከሣሽን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ149/2 መሠረት በነፃ ፍ/ቤቱ እንዲያሰናብተኝ በማለት ጠይቋል፡፡

ግንቦት 18ቀን 1997ዓ/ም የተፃፈ የመከላከያ ሰነድ ማስረጃ ከነመገለጫው አቅርበዋል 154 ገጽ ያካተተ የመፋረጃ ሣጣብም አቅርበዋል፡፡

ተከሣሹ ክሱን በመከላከል የዘረረው የጽሁፍ ማስረጃ፡-

1) የጀኖሳይድ ወንጀልን ለመከላከልና ለመቅጣት በ1948 የወጣው የጀነባ ስምምነት ዶኩሜንት 7.A/R&S/ 260/A/111/ 9 ዲሰምበር 1948
2) ደኩሜነት 7 ገጽ 152
3) ደኩሜነት 7 ገጽ 151
4) ደኩሜነት 7 ገጽ 102
5) ደኩሜነት 7 ገጽ 19 ፖራግራፍ 96
6) ደኩሜነት 7 ገጽ 22 ፖራግራፍ 113
7) ደኩሜነት 11

ዓለም አቀፍ ፍ/ቤት የጀኖሳይድ ወንጀል ለመከላከልና ለመቅጣት ሜይ 28 ቀን 1951 በተደረገው ሪሶሉሽን ላይ የሰጠው የምክር አስተያየት ገጽ 167 የመጀመሪያ ዓመድ የመጨረሻ ፖራግራፍ

8ዶክሜንት 82

የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ከ1991 ዓ/ም/እ.ኤ.አ/ጀምሮ በቀድሞው ዩጎዝላቢያ ውስጥ የተፈፀመውን ከባድ የሰብአዊ መብት መጣስ ሃላፊ የሚሆኑ ሰዎች ላይ ወንጀል ክስ ለማቅረብ ኢንተርናሽናል ትሪቡናልን ለማቋቋም ያቀረቡት ሪፖርት 5/25704 .3 ሜ4 1993 ገጽ 223 አንቀጸ 4 ጀኖሳይድ

ገጽ 435 አንቀጸ 4 ጀኖሳይድ

ስለ ትክክል ግልባጭ

228

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

9ዶክሜንት 83

የፀጥታው ምክር ቤት ከ1991 /እ.ኤ.አ/ በዩጎዝላቪያ ግዛት ውስጥ የተፈፀመው ከባድ የሰብአዊ መብት መጣስ ወንጀልን በሀላፊነት በሚጠይቁ ሰዎች ላይ ክስ ለማቅረብ የኢንተርናሽናል ትሪቢዩናል ስታቱት የፀደቀበት ሪሶልሽን

S/RAS/825/1993/ 25 ሜይ 1993 ገጽ 435 አንቀጽ 4 ጆኖሳይድ

10ዶክሜንት 94

የፀጥታወ ምክር ቤት በሩዋንዳና አጎራባት መንግታት ወስጥ የተፈፀሙውን ከባድ የሰብአዊ መብት መጣስና የጂኖሳይድ ወንጀል በሃላፊነነት የሚጠይቁ ሰዎች ላይ ክስ ለማቅረብ ኢንተርናሽናል ትሪቢዩናል ለማቋቋም የጠሰው ውሣኔ

5/RS/955/1994 ኖቨምበር 8/1994 ገጽ 494 አንቀጽ 2 ጆኖሳይድ

11ኛ የጊ/ወ/አስተዳደር ደረግና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደገና ለመወሰን የወጣው ቁጥር 110/1969፣

12ኛ በአዋጅ ቁጥር 110/69 አንቀጽ 7/10 መሠረት በጊ/ወ/አስተዳደር ደርግ በቁ/ወ/መ/ል/29/766 ታህሳስ 21ቀን 1969 ዓ/ም በክፍለሃገር ለተመደቡ የደርግ አባሉች የወጣ የሥራ ሃላፊነትና መመሪያ

13ኛ የብሔራዊ አብዩታዊ ዘመቻ መምሪያ አዋጅ ቁጥር 129/1969ዓ/ም

14ኛ ከጎብረተሰብአዊነት ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት አብዩታዊ ዘመቻ መምሪያ ለ501፣503፣504፣505፣506፣507፣ ግብረሃይሉች ለ2፣3፣6፣7፣14፣15፣16፣ ክ/ጦሮች የተላለፈ የጦር ሜዳ ደንብ

15ኛ በኢትዩትጵያ የሽግግር መንግስት በአዲስ አበባ አስተዳደር በቀጠና 5 ከአራዳ አውራጃ ፀጥታ ጽ/ቤት ለቀጨኔ አውራጃ ጉዳይ ጽ/ቤት የቀረበ ደብዳቤና በኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ላይ የቀረበ የተከሣሽ ከሳሽነት ክስ ሲሆን የመከራከሪያ ነጥቦችም ልዩ ዐ/ሕግ ያቀረበብኝ ክሶች እንድከላከል ፍ/ቤቱ ብይን የሰጠ ቢሆንም የተከሰስኩበት የወንጀል ድርጊት ለመፈፀም ለማስፈፀም ሀሳብ ዓላማና ፍላጉት ያልነበረኝ መሆኑ

- ወንጀሉም ያልፈፀምኩኝ በመሆኑ

- በፖለቲካ ተሳስሮ የተቋቋመ የጎብረብሔርን ማህበራዊ የሆነ አንድ ክፍል ሕዝብ ወይም የፖለቲካ ቡድን አባላትን በሞላ ወይም በከፊል ለማጥፋት ከሌሉች ጋር በግብረአበርነት ያላቀድኩ በመሆኑ

የጥፋቱን ሥራ በማቋቋም ትዕዛዝ በመስጠት ዘርን የማጥፋት አድራጎት በሥራ ያላዋልኩና የፖለቲካ ትስስሩ አባላት እንዲገደሉ ያላደረኩ መሆኑን ጨካኝና ነውረኛ በሆነ ሁኔታ ሆነ ብዬ በክሡ የተጠቀሡትን ግለሰቦች እንዲገደሉ ወይም ከባድ የአካለ ጉዳት እንዲደርስባቸው ያለደረኩ መሆኑን፣

ፊርማ ትክክለ መልስ

226

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

በቀረበብኝ ክስ እንድከላከል ብይን የተሰጠብኝ ቢሆንም ልዩ ዐ/ሕግ የወንጀሉ ድርጊት ለመፈፀሜ ባቀረበው ማስረጃ ያላስረዳብኝ መሆኑን

በጀኔሻ ኮንቬንሽን /A/RES/260/A/111/ 19 DEC 1948/ አንቀጽ 2 ሥር የፖለቲካ ተሳስሮ የተቋቋመ የሕብረብሔርን ማህበራዊ የሆነ አንድ ክፍል ሕዝብ ወይም የፖለቲካ ቡድን ያላከተተ ሆኖ እያለ ይህ ሐረግ በኢትዩጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 281 መካተት የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ክሱ ሊያስጠይቀኝ ስለማይገባ ፍ/ቤቱ ያቀረብኩት የጽሁፍ ማስረጃና የመከላከያ መግለጫ አይቶ ከክሱ በነፃ ያሰናብተኝ የሚል ነው፡፡

ተከሣሹ ባቀረበው የጽሁፍ መከላከያ ማስረጃ መሠረት በማድረግ ያቀረበው የመከራከሪያ ነጥቦች

የፖለቲካ ቡድኖች በጀኖሳይድ ኮንቬንሽኑ አንዲካተቱ የማሻሻያ ሀሳብ ቀርቦ የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ በሙሉ ድምጽ ሳይቀበለው ከመቅረቱም በላይ የተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ ኢንተርናሽናል ፍርድ ቤት አለም አቀፍ ኮንሼንሽን የተቀበሉ አባል መንግስታት በራሳቸው ፍላጉትና ተነሳሽነት የኮንሼንሹኑን አንቀጾች ማስፋትም ሆነ ማጥበብ በዓለም አቀፍ መርህ መሠረት የማይችሉ ናቸው፡፡

የጀኖሳይድ ኮንቬንሽን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ጥበቃ አካል በመሆኑ እየሰፋና እየዳበረ የሚሄድ ቢሆንም አንድ አባል አገር ኮንቬንሽኑን በራሱ ሊያሻሽለው ሥልጣን በሕግ አልተሰጠውም አባል አገር ኮንቬንሽኑን ለማሻሻል ለተባበሩት መንግስታት ሃሳብ ማቅረብ የሚችለው በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 16 ለመሆኑ ተመልክቷል፡፡

በቀድሞዋ የጎዝላቢያ የተፈፀመው የዘር ማጥፋት ወንጀል ክስ የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሓፊ ሜይ 3 ቀን 1993 በቁጥር 5/25704/1993/ ባቀረቡት ሪፖርት የጀኖሳይድ ትርጉም ከዋናው ኮንቬንሽን ተመሣሣይ ሲሆን የፖለቲካ ቡድን አላከተተም የፀጥታ ምክር ቤቱም ይህንን ጉዳይ በተመሣሣይ ሁኔሃተ ውሣኔ ያስተላለፈበት ጉዳይ ነው፡፡

በሩዋንዳ የተፈፀመው የዘር ማጥፋት ወንጀል ክስም የፀጥታው ምክር ቤት ኖቬምበር 8ቀን 1994 በቁጥር 955/1994/ ባወጣው የኢንተርናሽናል ፍ/ቤት ማቋቋሚያ ቻርተር አንቀጽ 2 ለወንጀሉ ትርጉም ሲሰጥ በጀኖሳይድ ኮንቬንሽን ከተሰጠው ትርጉም ውጪ የፖለቲካ ቡድን እንዲካተት አላደረገም፡፡

ስለሆነም በወ/መ/ሕግ የተካተተው የዘር ማጥፋት ወንጀል ውስጥ የፖለቲካ ቡድን በመጥቀሱ በዓለም አቀፍ ሕግ አንፃር መሠረት የሌለው በመሆኑ ወንጀሉ

ECLN

ቅክክል ግልባጭ

229

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

የፈጠራ ነው ክልከላ በሌለበት ሁኔታ ደግሞ የወንጀል ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ ስለማይሰራ ፍ/ቤቱ ከክሱ በነፃ ያሰናብተኝ ::

1948 የተሻሻለው የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት በፖለቲካ ተሳስሮ የተቋቋመውን የሕብረብሔርን ማህበራዊ የሆነ አንድ ክፍል ሕዝብ ወይም የፖለቲካ ቡድንን ፈጽሞ ዕውቅና የማይሰጥ ስልጣን በብቸኝነት ለንጉሠ ነገሥቱ የሚሰጥ ለመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 2፣4፣ እና 26 ተመልክቷል::

የ1949ዓ/ም የኢ.ወ.መ.ሕግ የታወጀው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 34 መሠረት ስለሆነ የወ.መ.ሕግ አንቀጽ 281 የሕገ መንግስቱ አንቀጸ 2፣4፣እና 26 የሚፃረር በመሆኑ በዚሁ ሕገ መንግስት አንቀጽ 122 መሠረት ዋጋ የሌለው ከመሆኑም በላይ የተሻሻለው ሕገ መንግስትና ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የበላይ ሕጉች ስለሆኑ የወ/መ/ሕግ ቁ/281 የጀኖሳይድ ሕግ የሚቃረን ስለሆነ የወንጀለኛ መ/ሕጉ ተፈፃሚነት የለውም::

የወ/መ/ሕ/ቁ/281 የአማርኛ ቅጂ የፖለቲካ ቡድን የሚል ሐረግ የሌለወ በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 109 መሠረት ዕውቅና የሚሰጠው የአማርኛው ቅጂ ስለሆነ በዚህ ልጠየቅ አይገባም በክሱ የተጠቀሱትን ቡድኖችም በወቅቱ ዕወቅና አልተሰጣቸውም::

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 9 መሠረት ማንኛውም ሕግ ልማዳዊ አስራር ወይም ለሕገ መንግስቱ የሚፃረር ማንኛውም ውሣኔ ተፈፃሚነት የሌለው ለመሆኑ የተደነገገ ስለሆነ በ1949 የወጣው ወ/መ/ሕግ ቁ/281 ሥር የተመለከተው የፖለቲካ ቡድን የሚለውን ሀረግ ከዓለም አቀፍ ሕግ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9/4 እና 13/2 መሠረዝ የሚገባው ነው::

የሰብአዊ መብት ጥበቃ ዕድገት የሚከናወነው በዓለም አቀፍ ደረጃ እንጂ በተናጠል አለመሆኑም በቅረቡ የተጀመረው Anarchic conflicts ማስረጃ ነው::

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳዳር ደርግ በሕግ የተቋቋመ ሕጋዊ መንግስት በመሆኑ ኢትዮጵያ ትቅደም የሚለው ዓለም የመቃወም አድማ የማድረግ ሥራ ማቆም ያለፈቃድ ሰላማዊ ሰልፍና ሰብሰባ ማድረግ የተከለከለ መሆኑና የዚህን አዋጅ ሕግ ቁጥር 8 ሆነ ወደፊት የሚወጡ ሕጉች የሚተላለፉ ሰዎች ጉዳያቸው በጦር ፍ/ቤት እንዲታይና ውሣኔው ይግባኝ የሌለው መሆኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1/1934 አንቀጽ 5/ሀ በነጋሪ ጋዜጣ ሲወጣ ማናቸውም ፍ/ቤት ማናቸውም አዋጅ ድንጋጌ ደንብ ውሣኔ ትዕዛዝና ማስታወቂያ የመቀበል ግዴታ ያለበት በመሆኑ ፍ/ቤቱ የጊ/ወ/መንግስት የተቋቋመበት አዋጅ ቁ/1/1967 የመቀበል ግዴታ ያለበት ነው::

ኢህአፓ፣አዲዩ፣ሻዕቢያ፣ሕወሐት፣አነግወዘተ ከመንግስት ዕውቅና ያልተሰጣቸውና በሕገወጥ መንገድ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ መሆናቸውና የደርጉ ሊ/መንበር በርዕሰ

ፀሐፊ ትክክል ግልባጭ

230

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ብሔርነት አገሪቱን የመምራት የጦር ሃይሉችን በበላይ አዛዥነት የመምራት የሕዝቡ ሠላምና ፀጥታ እንዲሁም የአገሪቱን አንድነት እንዲጠብቁ ለማድረግ በፀረ-ሕዝብና ፀረ አብዮተኞች ላይ እርምጃ ለመወሰድ በአንቀጽ 8/1፣8/6፣8/9 ሥልጣንና ሐላፊነት ያለው ነው።

ጊ/ወ/መንግስት ታህሳስ 21ቀን 1969ዓ/ም ባወጣው መመሪያ መሠረት በክፍለሀገሩ የተመደቡ የደርግ አባሉች በገጠርና በከተሞች ውስጥ የአድሃሪያ ትጥቅ ማስፈታትና ለጥበቃ ጓዶች የማስታጠቅ የኢኮኖሚ አሻጥሮችን በማጋለጥ ወደ ፍርድ የማቅረብ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ኘሮግራም መሠረት ሕዝቡ በየደረጃው እንዲደራጅ የማስተባበር ስልጣን የተሰጠወ ሲሆን ሻዕቢያ ሕ/ወ/ሐ/ት ኢ.ህ.አ.ፓ. ኢ..ዲ.ዩ ወዘተ ከወዝ አደሩ ፖርቲ ምስረታ ወጭ ናቸው።

የብሔራዊ አብዩታዊ ዘመቻ አዋጅ ቁጥር 129/69 የወጣው ፀረ ሕዘብ ፀረ አንድነትና ፀረ አብዮት የውጭ ሃይሉችን ለመከላከልና ብሉም ለመደምሰስ በመሆኑ ይህን ለመተግበር የብሔራዊ ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ በጉንደር ክፍለሃገር በሰሜን ዕዝ ሥር ተቋቁሞ ስልጣንና ሃላፊነት ተሰጥቷቸዋል።

የበላይ አዛዥ የሆነውን የሰሜን ዕዝ አንዱ ክፍል የሆነው የጉንደር ክፍለሀገር የፀጥታ ሁኔታ እየተከታተለ መደበኛውን ጦር የፖሊስ ሠራዊትና ሕዝባዊ ሠራዊቱን በማስተባበር ፀረ-አንድነት ፀረ-ሕዝብና ፀረ-አብዮት ሀይሉችን የመደምሰስ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

የክፋለሀገሩ አዘአኮ በሕጉ በተሰጠው ሥልጣንና ከዕዙ የበላይ አዛዥ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በአዋጁ አንቀጽ 16 መሠረት የአውራጃው አዘአኮ ኮማቴዎች የሚያከናውኑትን ተግባር ለማስተባበር የመቆጠጠር ስልጣን የተሰጠው ሲሆን በአየአውራጃው ፀረ-አብዩት ፀረ አንድነት ተግባሮች እየተከታተለ በየአውራጃው ያሉት የአዘአኮ ኮሚቴዎች ሁኔታውን እንዲያውቁትና አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰዱ የማድረግ ስልጣን ያለው ከመሆኑም በላይ በፀረ-አብዩተኞች ላይ የሚደረግ አሰሳ ማስተባበርና አስፈላጊው እርምጃ የመወሰድ ሥልጣን ያለው ነው።

ማንኛውም ኢትዩጵያ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚደረገው የብሔራዊ አብዩታዊ ዘመቻ መምሪያ የዕዝ አዛዥ ወይም የአብዩት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚሰጠው ትዕዛዝ የአብዩት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚሰጠው ትዕዛዝ የመፈፀም ግዴታ ያለው ሲሆን ትዕዛዙን የማያከብር እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት ወይም በሞት ሊቀጣ እንደሚችል ተደንግገዋል።

በዚህም መሠረት በሰሜን ዕዝ ሥር የተቋቋመው የጦር ፍ/ቤት በአዋጁ የበላይ አዛዥ በቀረበው የክፍለሀገሩ የፀጥታ ጉዳዩች ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25/2 እና ከሕብረተሰብአዊት ጊ/ወ/መንግስት ብሔራዊ አብዩታዊ ዘመቻ መምሪያ ለ501፣ከ503

ፀለ ትክክል ግልባጭ

231

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

እስከ 507 ላሉት ግብረ ሃይሉች ለ2፣3፣6፣714፣15፣16 ክፍለጦሮች በተላለፈው የጦር ሜዳ ደንብ መሠረት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን ልዩ ዐቃቢ ሕግ ይህንኑ ደንብ በእነ ኮ/ል መንግስቱ ሃ/ማርያም መዝገብ በማስረጃነት ያቀረበው ስለሆነ በመ/ማስረጃነት ይያዝልኝ፣

የክፍለሀገሩ የአዘአኮ ኮማቴ ከበላይ ዕዝ የተላለፈለት ውሣኔ ማስፈፀሙ የሕግ ከለላ ያለው መሆኑን የሚያሣይ ነው።

ተከሣሹ በጉንደር አቻውን ነበር የሚታገለው ቦታው ውስጥ እንደመሆኑ መጠን የሻዕቢያ የወያኔና ኢዲዩ ምሽግ ነበር የፀረ ሕዝቦች ፀረ ሕዝብ ተግባር በማየሉ አንድ ክፍለጦር እስከመከላከል ደርሰናል። የኢትዩጵያ አብዩት ከወሰደው እርምጃ ፀረ ሕዝቦች ያደረሱትን ጭፈጨፋ በእጥፍ ይበልጣል። መላኩ ብዙ ትዕግስት የሌለው ወደ ወታደርነት የሚያደላው ስለነበር አገርህ ነው ታገል ብለን ነበር የላክነው የሚል ቃል ከኮሌኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም ትዝታ በማስረጃነት የቀረበ ሲሆን በደርጉ ሊ/መንበር ትዕዛዝ ለፈፀምኩት ድርጊት አያስጠይቀኝም።

ድርጊቱ በሕግ የተፈቀደና በበላይ ትዕዛዝ የተፈፀመ በመሆኑ ሊያስጠይቀኝ የማይችል ነው።

ቤቴ አለፍ/ቤት ትዕዛዝ በመበርበሩ የመ/ማስረጃ ሊሆኑኝ ይችሉ የነበሩ ሰነዶች በመጥፋታቸው በዚህ ምክንያት የደረሰብኝን አቅም ማጣት /forcmajeure/ በሀላፊነት ሊያስጠይቀኝ አይገባም ወ/መ/ሕ/ቁ.67

ጅቡቲ በስደት በነበርኩበት ጊዜ በኢህአዴግ ትዕዛዝ መሠረት የመግደል ሙከራ ተደርጉብኛል ከሕክምና ከወጣሁ በኋላ እጄና እግሬ በሰንሰለት በማሠር አምጥተውኝ የሰም ማጥፋት ኘሮፓጋንዳ የነዛብኝ ስለሆነ ይህ አድራጉት የሽግግር ወቅት ቻርተር እንቀጽ 1 የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9/4 እና የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች አዋጅ አንቀጽ 41/1 የሚሰጥስ ነው።

ልዩ ዐ/ቃቢ ያቀረቡው ማስረጃ የወንጀሉ ድርጊት ለመፈፀሜ አያስረዳም በአንድ ችሉት መታየት የሚገባው ጉዳይ በተለያየ ችሉት መታየት የለበትም።

ከመስከረም 2 ቀን 1967 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 1970ዓ/ም ድረስ በጊዜያዊ ወ/አ/ደርግ ወይም መንግስት አባልነት በወ/መ/ሕ/ቁ/32/1/ሀ፣286/ሀ በወ/መ/ሕ/ቁ/32/1/ ለ እና 281/ሀ በወ/መ/ሕ/ቁ/32/1/ለ እና 414 በወ/መ/ሕ/ቁ/32/1/ለ እና 416 በመተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋል ተብዩ ጥቅምት 15ቀን 1987ዓ/ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ በፌ/ከ/ፍ/ቤት 1ኛ ወንጀል በእነ ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም የክስ መዝገብ ውስጥ በ20ኛ ተራ ቁጥር ክስ ተመስርቶብኝ እየተከታተልኩ ሲሆን፣

በ6ኛ ወንጀል ችሉት 1969-1975 ዓ/ም የጉንደር ዋና አስተዳዳሪ የአብዩትና ዘመቻ አስተባበሪ ኮሚቴ ሊ/መንበር ሆኖ ሲሰራ በወ/መ/ሕ/ቁ/32/1/ለ እና

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

281/ሀ፣በወ/መ/ሕ/ቁ/32/1/ለእና522/1/ለ፣በወ/መ/ሕ/ቁ/32/1/ለ እና 538 የተመለከቱትን በመተላለፍ ያስፈፀመው ወንጀል ተከሷል የሚል ክስ ቀርቦብኛል፡፡

ስለሆነም ይህ ክስ በ1ኛ ወንጀል ችሉት ከ1969-1970ዓ/ም የቀረበብኝን ክስ ስር የሚጠቃለል ስለሆነ ክሱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 130/2/ሀ እና ረ መሠረት እንዲሰርዝ በድጋሚ እጠይቃለሁ የሚል ነው፡፡

ተከሣሽ የመፋረጃ 1541ኛ ሀሳብ ያቀረበ ሲሆን የመከላከያ ማስረጃ በማጠናከር ያነሣው ክርክር በልዩ ዐቃቢ ሕግ ተግባር ከዐ/ሕግ ሚና ጋር የሚቃረን ነው ሕጋዊ ተግባራትን በሕገወጥነት የሚፈርጅ ክስ ማቅረብ አይችልም የወ/መ/ሕ/ቁ/538 ተጠቅሶ የቀረበውን ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የወንጀለኛ መ/ሕ/ቁ/281 የሕግ መሠረተ ሀሳብ /Principle of legality/ የሚሰጥ ነው፡፡ የክሱ አቀራረብ ጉደሉነት የመከላያ ማስረጃ ለማቅረብ እንቅፋት ሆኖአል፡፡ የወ/መ/ሕ/ቁ/281 ሁለት ክስ የያዘ ነው፡፡ በክሱ በፖለቲካ ቡድኖች ተብለው የቀረቡት በወቅቱ ምን ያደርጉ ነበር? የልዩ ዐ/ሕግ ማስረጃ ወንጀል ለመፈፀሜ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ውጪ አያስረዳም፡፡ የዐ/ሕግ ማስረጃ ቀደም ብለ ሊደርሰኝ ይገባ ነበር የሚል ሲሆን ፍ/ቤቱ የመፋረጃ ሀሳብን በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

ፍ/ቤቱ ተከሣሹን ያቀረበው መከላከልያ ክርክርና ማስረጃ የልዩ ዐ/ሕግን ክስና ማስረጃዎችን አስተባብለዋል ወይስ አላስተባበለም የሚለውን ጭብጥ መነሻ በማድረግ ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ተከሣሹ ያቀረባቸው የመከላከያ ምስክሮች ሶስት ሲሆኑ የሰጡትን የምስክሮች ቃል አራቱም ከኢህአፓ መሣሪያ ማስረከባቸው ኢህአፓ ስለሆናችሁ ነው በማለት እንዲታሰሩ አብረውም ታስረው እያሉ አብረው መፈታታቸው ያስረዱ በመሆኑና እነዚህ በተጉጂነት /ክሽ/ 284ኛ የተገለፀ ሰዎች በመሆናቸው 3ቱ ራሳቸው ቀርበው በማስረዳታቸው ጥርጣሬ እንዲኖር የሚያደርግ ሁኔታ መኖሩን መረዳት ስለተቻለ አብሮ ከተፈታ በኋላ ሞቷል ተብሉ ለፍ/ቤት ያልቀረበው አዳሙ አበራ የአያቱ ስም አናቅም በማለታቸው ብቻ ብዙ እስረኞች በነበሩበት አካባቢ ሁሉም እስረኛ ከአነአያቱ ያውቃል ተብሉ የማይገመት በመሆኑ አብረዋቸው መታሰሩንና መፈታቱን የገለፀበት አዳሙ አበራ ጭራሽ ስለሰውዬ ያላስረበት ምክንያት እስገለፀ አብሮ በእስር ቤት ቆይቶ አብሮ መፈታቱ በገለፀበት ሁኔታ ስለተጉጂው ማወቃቸው አልነበራቸውም የሚያስብል ሆኖ ስለአገኘነው ተከሣሽ በ284ኛ ክስ በአራት ሰዎች ግድያ ተከላክለዋል የሚያስብል ሁኔታ መኖሩን ስለተገነዘብን በመከላከሉ ምክንያት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/149 /2/ ነፃ ነው ብለናል፡፡

ዕለ ትክክል ግልባጭ

15

238

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ተከሣሹ ለፍ/ቤቱ የሰጠው ቃል የጽሁፍ ማስረጃ በማስመልከትና ክሱን አስመልክቶ ያቀረባቸው የመከላከያ ክርክሮች ተመሣሣይ በመሆናቸው ከአንድነት የሚታዩ ናቸው፡፡

ተከሣሹ የቀረበብኝ ክስ ድርጊት ለመፈፀም ሀሳብ ዓላማ ፍላጐት አልነበረኝም ድርጊቱ አልፈፀምኩም ከሌሎች ግብረ አበሮች ጋር በመሆንም ድርጊቱ እንዲፈፀም አላቀድኩም የጥፋቱን ሥራ በማቋቋም ትዕዛዝ በመስጠት ዘርን የማጥፋት አድራጎት በሥራ ላይ አላዋልኩም፡፡ የፖለቲካ ትስስሩን አባላት እንዲገደል አላደረግኩም ጨካኝና ነውረኛ በሁኔታ በክሱ የተጠቀሱትን ግለሰቦች እንዲገደል ወይም ከባድ የአካል ጉዳት እንዲደርስባቸው አላደረኩም የሚል ክርክርም አቅርበዋል፡፡

በመሠረቱ ተከሣሹ እንዳከላከል ብይን የተሰጠበት ምክንያት ልዩ ዓ/ሕግ ጽፎ ባቀረበው የወንጀል ክሰ ተከሣሹ ከ1969 ዓ.ም. አንስቶ እስከ 1975 ዓ.ም. ድረስ በጊ.ወ. አስተዳደር ደርግ ወይም መንግስት የጐንደር ክፍለ ሀገር ዋና አስተዳዳሪያ የአብዩትና ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ ሊ/መንበር ሆኖ ሲሰራ በሌላ መዝገብ ክስ ከቀረበባቸው ግብረ አበሮቹ ጋር በመሆን በፖለቲካ ተሳስሮ የተቋቋመውን የጎብረብሔር የሆነ ክፍለ ሕዝብ በሞላ ወይም በከፊል ለማጥፋት በግብረ አበርነት በማቀድ የጥፋቱን ሥራ በማቋቋም ትዕዛዝ በመሥጠት ይህንንም አድራጎት ሥራ ላይ ለማዋል የተለያዩ የምርመራ የማሠቃያ የመግደያ አካላት በማደራጀት መቺ ሀይል፣ አስፔሻል ፎርስና የመብረቅ ኮሚቴ በማዘጋጀት ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር በማካሄድ ዕቅድ ለማሣካት በቀጥታ በወቅቱ በነበረው መንግስት በሚሰጠ መግለጫዎች በመቀበል ተከሣሹም በደረጃው በነበረበት ክፍ/ሀገር የፖለቲካ ትስስር የነበራቸው ሰዎች ወይም ቡድኖች ማለትም ኢ.ሕ.አ.ፖ፣ ኢ.ዲ.ዩ.አ.ኤልኤፍ፣ ሕ.ወ.ሐ.ትና የመሣሠሉትን የፖለቲካ ቡድን አባላት የሆኑ ሰዎች ለማጥፋት እንዲያስችለው ከመደበኛ የመንግስት መዋቅርና አሰራር ውጪ ከፍ ብሎ የተገለፀው ሀይልና ከሚቴ እንዲሁም ከክፍለሀገር እስከ አውራጃና ወረዳ የተዋቀረ መኖሩ እንዚህንም በተከሣሽ ብቻ የተቋቋሙ ለተከሣሹ ተጠሪና ታዛዥ የነበሩ በሰው ሀይል፣ በመሣሪያና በቁሳቁስ የተደራጅ መሆናቸው እነዚህ ድርጅቶችና ቡድኖች ተከሣሹን ከማጀብ ጀምሮ በተለይ የፖለቲካ ትስስሩ አባላት የነበሩ ሰዎች ከሚኖርበት፣ ከሚሠሩበት ከመንገድ ሌሊትና ቀን በመሣሪያ አድነው በመያዝ ለመመርመሪያ ባዘጋጅው የተከሣሹ ቤተመንግስት ኢሰብአዊ በሆነ ምርመራ ገርፎ የሚያሠቃይ በቀጥታ በግድያ የሚሣተፍ በአንድ ኮሎኔል እና በሌሎች መኮንኖች የሚመራ በሥሩም ተራ ወታደር የነበሩት አስፔሻል ፎርስ እንደነበረው ይህንን ሀይል የመረመረው በእያንዳንዱ ጉዳይ ለተከሣሹ የውሣኔ ሀሣብ የሚቀርብና የሚወስን መብረቅ ኮሚቴ በሚባልና ሰዎች በመያዝ በመመርመር እስከሞት የሚደርስ ውሣኔ የሚሰጥ በተከሳሽ ሲፀድቅም በሥራ ላይ የሚተረጐመው ኢ.ዘ.አ.ኮ እስከ ወረዳ በማቋቋም የውሣኔ ሀሳብ ከመሰጠት አልፎ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

በእነዚህ ኮሚቴዎች ያልታዩ ግን ተከሣሹ በቀጥታ ሰዎች እንዲገደሉ፣ እንዲገረፉ ውሣኔ በሚሰጠበት ጊዜ አስፈጽመው ሪፖርት የሚያደርጉለት መሆናቸው እስፔሻል ፎርሶቹ ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ ገርፈው አካሉን በድን በማድረግ ከተጐጂው በስቃይ ካገኙት ቃል ምርመራ መግለጫ ላይ አብዮታዊ እርምጃ ነው ተብሎ እየቀረበለት ተከሣሹም ያለ ፍ/ቤት ፈቃድና መቅረብ ፍ/ቤትም ቀርበው አያስከሰሰም የተባሉትን ሰዎች ሣይቀር በራሱ ሥልጣን ለዚሁ በመረጣቸው እስፔሻል ፎርሶችና ፖሊሶች ምርመራ እንዲጣራባቸው በማድረግ ለውሣኔ ወደ ራሱ እንዲላኩ በቁ. 12/7/09 በቁ. 147/69 የተፃፈ ቋሚ ትዕዛዝ ሰጥቷል።

ተከሣሹም ባቁቋማቸውና ባደራጃቸው አካላት ተይዘው ተመርምረው በተገኘው የምርማራ ግጭት /ግኝት/ ላይ የውሣኔ ሀሳብ በማስቀመጥ ወይም መግለጫ በማውጣት ለውሣኔ ሲያቀርቡለት ያደራጃቸው ኮሚቴዎችና ቡድኖች ሊረዱት በሚችሉ የሚስጥር ማስተላለፊያ ልዩ ምልክቶች ፊደላትና ሆሄያት በመጠቀም ምንም ዓይነት ልዩ ጦር ፍ/ቤት ሣይቁቋም በፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በማስመሰል የጦር ፍ/ቤት ውሣኔ ሰጥቷል በማለት በሚሰጣቸው ትዕዛዞች እየገለፀ በፍ/ቤቶች መወሰን የነበረባቸው ትናንሽ ጉዳዮችን በመንጠቅ እነዚህ ትናንሽ ምክንያቶች /ድርጊቶች/ ፈጽመዋል በሚልም ጭምር የግድያና የግርፋት እንደሁም እስራት በማጣመር ወይም በተናጠል ግድያውና ግርፋቱ ከነመጠኑ በመግለጽ የሚፈፀምበት ቦታና የአፈፃፀሙ ሁኔታ በመወሰን የበታቾቹ እንዲያስፈጽሙ ለመፈፀማቸውና ለማስፈፀማቸው ሪፖርት እንዲያደርጉ በማድረግ የፈፀመው በ1949 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ.. 32/1/ለ እና 281/ሀ/ የተመለከተውን ዘር በማጥፋት በሰበአዊ ፍጥረት ላይ የሚፈፀም ወንጀል በወ.መ.ሕ.ቁ. 32/1/ለ እና 522/1/ሀ የተመለከተው በግፍ ሰውን መግደል ወንጀለና በወ.መ.ሕ.ቁ. 32/1/ለ እና 538 የተመለከተው ከባድ የአካል ማድረስ ወንጀልን የሚያቋቁም ነው በማለት ሲሆን ተከሣሹ የካደውን ክስ የልዩ ዐ/ሕግ የሰውና የሰነድ ማስረጃ ቀርቦ አስረጅነቱ ፍ/ቤቱ ሲመዝነው ተከሣሹ በሥሩ የሚገኙትን ልዩ ልዩ ክፍሎች በጐንደር ክፍለሀገር በሚኖረው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሊከተሉትና ሉያከናውኑት የሚገባቸው ተግባር ዕቅድ ነድፎ ከመጋቢት 12 ቀን 1969 ዓ.ም. ጀምሮ ሥራ ላይ የሚውል በቁጥር 147/69 መጋቢት 12 ቀን 1969 ዓ.ም. መጋቢት 12 1969 በአድራሻ ለክፍለሀገሩ አስተዳደር ጽ/ቤት ለክፍለሀገሩ የንብረት ዕዝ መምሪያና ለክፍለሀገሩ ፖሊስ ዋና መምሪያ በግልባጭ በጎንደር ክፍለ ከተማ ለሚገኙ የ20 ቀበሌዎች ማህበራትና የተለያዩ መ/ቤቶች በተፃፈ ቋሚ ትዕዛዝ የፖሊስ ማስፈፀሚያ መመሪያ /1ኛ ሰ.ማ/ ማስተላለፍ ትዕዛዙ የደረሳቸው ክፍሎችም በትዕዛዙ መሠረት እንዲፈጽሙ እንዲያስፈጽሙ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን በዚህ ትዕዛዝ መሠረት የቀበሌ የደህንነት አባላትና የፀጥታ አስከባሪዎች ፀረ ሕዝብ ነው የሚሉትን እያደኑ እንዲይዙ እርምጃ

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

እንዲወስዱ /እንዲገድሉ/ ፈቃድ ሳይኖረው ከከተማ ክልል ውጭ የሚገኝ ሰው የአካባቢው የገበሬ ማህበር በቁጥጥር ሥር እንዲያውሉ በአካባቢው ፖሊስ ጣቢያም ከእነዚህ ሀይሎች ጋር በመተባበር፣ የወንጀለኛውን ጉዳይ አጣርቶ የምርመራ መዝገቡን በአስቸኳይ በክፍለ ሀገሩ ተነቃናቂ የደርግ ጽ/ቤት ለተቋቋመው አብዮታዊ የጦር ፍ/ቤት እንዲያቀርቡ ሥልጣን መስጠቱ ግዴታም መጣሉ፣ ፀረ-አብዮት ድርጊት ፈጽመዋል ከሚባሉት በተጨማሪ ሌላ ዓይነት ወንጀል ፈጽመዋል በተባሉት ላይ ከሰሜን ዕዝ ተነቃናቂ የደርግ ቡድን በተሰጠው የመወሰን የዲስፕሊን መመሪያ መሠረት እንዲፈፀም በመግለጽ ቋሚው የመመሪያ ትዕዛዝ ለተላለፈላቸው ክፍሎች ጥር 24 ቀን 1970 ዓ.ም. በቁጥር አ.ዘ.አ.ክ/አለን/1288/70 መተላለፍ መመሪውም ክፍሎቹ በተዋረድ እንዲያስተላልፍ ማስገንዘቡ /2ኛ ሰ.ማ/ ያስረዳል።

ህዳር 9 ቀን 1970 ዓ.ም. ከሰሜን ተነቃናቂ የደርግ ቡድን ለሰሜን ትዕዛዝ ተሰጠ የተባለው የዲስፕሊን መመሪያ ሥራን ለማስከበር ለክ/ሀገሩ ጊ.ወ.አ.ደርግ አባልና ሊ/መንበር ለሰሜን ዕዝ አዛዥና ወደታደራዊ ፖለቲካ ሀላፊ ሥልጣን የሚሰጥ ከአብዮታዊት/ትና ከባድ ማስጠንቀቂያ እስከ እርምጃ መውሰድ የሚያስችል ደረጃ ያስቀመጠ የዲስፕሊን መመሪያው ለማስከበር ሥልጣን የሰጠው ቡድን በማንኛውም ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድ ወስነው ማስፈፀም የሚያስችላቸው ሥልጣን ማስጨበጡ የሚያስረዳና ተከሣሹ ዕቅዱና ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስችለው በፀረ አብዮተኝነት ሆነ በሌላ ማንኛውም ዓይነት ወንጀል ተጠርጥሮ በማንኛውም ሰው የመያዝን /ሥልጣን/ የሚሰጥ ለተከሣሹም የተፈፀመውን ማንኛውም እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር በሚያስችለው ሚስጢራዊነት በጠበቃ ማዕከላዊ አሰራርና የአፈፃፀም ዝግጅታዊ አተገባበር መመሪያዎቹ ባስገኙለት ምቹ ሁኔታዎች ባደረገው ተግባራዊ የሥር እንቅስቃሴ ያስገኘው ውጤት

ተከሳሽ በጸረ ሕዝብነት የሚጠረጠር ሆነ የዲስፕሊን መመሪያው የሚዘረዝራቸው ወንጀሎች እንዲሁም ተከሳሹ ተይዞ እንዲቀርብለት የሚፈልገው ሰው ወንጀል ሰርቷል በሚል የሚይዙ የሚያስይዙ የሚገርፍና የሚገድሉ ለዚሁ ብሎ የመረጣቸውና ባደራጃቸው የተለዩ ሀይሎች ሌሊት የሰው ቤት እየበረገዱ በመግባት የሚፈልጉትን ይዘው የሚያስሩበት ክፍል ከሌላው እስረኛ በማይገናኙበት በተለየ ሁኔታ እንዲታሰሩ የተደረገበት ለምርመራ የሚያስወጡዋቸው የሚመልሷቸው አውጥተውም ግድያ የሚፈጽሙባቸው ይኸው በተመደበው ሀይል መሆኑን የሚይዙትም ከቤታቸው፣ ከመንገድ፣ ከስራቦታ፣ ከትምህርት ቤት በማንኛውም ሰዓት መሆኑን ምርመራ የሚካሄደው ተከሳሹ ከሚኖርበት ቤተመንግስት ግቢ ውስጥ መሆኑን በዚህ ወቅትም ከባድ ግርፋት ይፈፀምባቸው እንደነበረ ለምርመራ ሆነ ለግድያ በተለየ ሀይሎች ከቀኑ 11 በኋላ እስረኛው በየክፍሉ እንዲገባ ከተደረገ በኋላ መሆኑን እና ሌሊት መሆኑን በእንደዚህ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ሁኔታ የሚወሰዱት በተከሳሹ በተቋቋሙ ሀይሎች የተያዙ የፖለቲካ እስረኞችና በዲስፕሊን መመሪያው በስርቆትና በመሳሰለው ሌላ ወንጀል ተጠርጣሪነት የተያዙ እንደነበሩ በየጊዜው ከሳምንት ከሁለት ሳምንት በኋላ ከአምስት መቶ ስድስት መቶ እስረኛ በእስፔሻሎች ከነበሩበት ክፍል እየተጠሩ ወጥተው ሳይመለሱ የሚቀሩ በርካታ መሆናቸው በየጊዜው በየቤታቸው በራፍና በየጥርጊያ መንገድ ተገድለው ጥለው የሚታዩ ማልቀስም ሆነ አስከሬን ማንሳት የተከለከለና በእስፔሻሎች በፊታቸው ማልቀስ ቀርቶ ማልቀሱን በወሬ የሰሙትን እቤቱ ድረስ ሄደው ድብደባ ይፈጽሙበት እንደነበረ አስከሬኑ እየተጠበቀ በወደቀበት እንዲውል ከተደረገ በኋላ አስቀድመው በእስረኞች ባስቆፈሩት ጉድጓድ እየወሰዱ እንደሚጥሉት ተከሳሹ እየተገኘ በወህኒቤት ግቢ ውስጥ በትዕዛዙ በእነዛ እስፔሻሎች ግድያ ይፈፀም እንደነበረ ተራው የሚጠባበቀው እስረኛም ተሰልፎ ሬሳውን እየዞረ እምቧበል እየተባለ ይል እንደነበረ እስረኞቹ በመኪና ተጭነው ሲወሰዱ ኡኡታና ጩኸት ስለማይሰሙ በኤሌክትሪክ ገመድ እየተገደሉ በመኪና ውሰደው በትልቅ ጉድጓድ ይደፉዋቸው እንደነበረ። ከተገደሉ በኋላ የሚጣሉበት ጉድጓድ የሚያስቆፍረው(ቆፍረው) የእስፔሻል ፎርስ አዛዥ ለልማት በሚል በእስረኞች እንደነበረ ከተገደሉም በኋላ ለእስረኛ ጠያቂ ቤተሰብ ለልማት ሄደዋል ተብሎ በጠባቂዎች ይነገረው እንደነበረ አዲስ አበባ ሄደዋልም ይባል እንደነበረ ለልማት ሄደዋል የተባለለት እስረኛ ተገድሎ ይገኝ ስለነበረ ለልማት ሄደዋል የሚለውን መልስ የሚሰጠው ጠያቂ ቤተሰብ መሞቱን ይረዳ እንደነበረ ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1973 ዓ.ም ድረስ ተገድለው በአዘዞ ጦር ካምፕ ከቀበርዋቸው በላያቸው ላይ መፀዳጃ ቤት የጥይት መጋዘንና የሰራዊት መሰብሰቢያ አዳራሽ ተሰርቶበት እንደነበረ ከ1974 ዓ.ም እስከ 1983 ዓ.ም በማራኪ ወይም በሳሙና በር በላይ ላይ የተሰራበትን በማስቆፈር በድምሩ 1400 የሰው ጭንቅላትና አፅም ብቻ ማውጣት እንደተቻለ ሌላው እንደቀረ የተገደሉት ሰዎች የሚጣሉበት በጎንደር ሉዛማሪያም በእስረኞች ጉድጓድ ይቆፈር እንደነበረ ይህም እንደማይታወቅ ለልማት ነው ይባል እንደነበረ ከዚህም ተቆፍሮ የሰው አፅም መውጣቱ በወቅቱ የጎንደር ወህኒ ቤት የሽፍት ሀላፊና ጉድጓዱን ካስቆፈሩት አንዱ የሆኑትን ሳይቀር የመስከሩበት በአጠቃላይ ሰዎች የሚያዙት በምርመራ ወቅት የሚገርፉት በጎንደር ከተማም ሆነ በሌሎች የክ/ሀገሩ ልዩ ልዩ ከተሞች ይገደሉ የነበሩት በአደባባይ እንዲገረፉ ይደረግ የነበረው በሻለቃ መላኩ ብቻ በሚታዘዙ እስፔሻል ወታደሮች እንደነበረ በምስክሮች ተረጋግጧል።

የቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎችም በፀረ ሕዝብነትና በሌላም አይነት ወንጀል የሚጠረጠሩ ሰዎች ከመያዝ ጀምሮ እስከ ግድያ ልዩ ልዩ እርምጃ መውሰድ የሚያስችል ትዕዛዝና መመሪያ ማስተላለፍን ይህንንም በተዋረድ እስከ ታች ሚስጢራዊነት በጠበቀ መልኩ ሥልጣኑን ለመጠቀምና ለመቆጣጠር የሚያስችል የተማከለ አሰራር እንዲኖረው

ስለ ጌሌሳ ግልባጭ

237

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ያስቻለው ትዕዛዙን የሚያስፈጽሙለትን ልዩ ልዩ ክፍሎችና በድኖች በማደራጀት ዕቅዱን ለመተግበር ዓላመውን ማስፈፀም መቻሉ

በወቅቱም ፀረ ሕዝብና ወንጀለኞች ናቸው ተብለው ሰዎች ተይዘው ምርመራ ተካሂዶባቸው በሚቀርቡለት የምርመራ ግኝት መግለጫዎች ወይም የኮሚቴ ውሳኔዎች ላይ በሚያፀድቅበት ጊዜና በሚሰጥበት ጊዜ አብዮታዊ እርምጃ ይወሰድበት ቀይሽብር ይፋፋምበት በአንደኛ ደረጃ አልፏልን የመሳሰሉትን በወቅቱ ግድያ መሆኑን ማስተላለፊያ የጋራ መግባቢያነታቸውን ይታወቁ የነበሩትን ዓረፍተ ነገሮች ከመጠቀም ባሻገር ውሳኔው የሚፈፀምበት ቦታ ፣የእስራቱንና ግርፋቱን መጠን በመግለፅ ይህን ያህል ጅራፍ ከተገረፈ በኋላ ይህን ያህል ጊዜ ይታሰር፣ በገመድ ስቅላት ይገደል፣ በጥይት ይገደል ብሎ ለመወሰን የተለያዩ የአማርኛና የእንግሊዝኛ የሚስጢር መለያ ቃላቶችን ፊደሎችና ሆኼያቶችን በመጠቀም ይወሰን እንደነበረ የሚያስረዱ ሆነው በመገኘታቸው ከዚህ በላይ የተገለፁትን በሰው ምስክርና በሰነድ ማስረጃ የተነገሩትን ክንውኖች በጦር ፍ/ቤት የተሰጡ ውሳኔዎች እንደሆኑ በሚናገር መልኩ በሚፅፋቸው የገለፀ ቢሆንም ድርጊቶቹ የተፈፀሙት ከሰሜን ዕዝ በተላለፈ መመሪያ መነሻነት በመሆኑ ፈርሞ ያስተላለፋቸው ትዕዛዞችም በጦር ፍ/ቤት የነበረው ህላፊነት እና እንዲህ ዓይነት ተግባር መፈፀም የሚችል እንደነበረ የሚያመለክቱ ሆነው በመገኘታቸው ፀረ-ሕዝቦች ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለውና ለግድያ ያበቃቸው የሌብነት ሆነ ሌላ ወንጀል መፈፀም አለመፈፀም በማስረጃ የሚጣራ ጉዳይ ሆኖ ይህንንም አይቶ የመወሰን ሥልጣኑ የፍ/ቤት በመሆኑ በሕግ ካልተሻረው ወ/መ/ሕግና ሥነ-ሥርዓት ውጭ የተፈፀመ ድርጊት ሆኖ ፍ/ቤቱ ስለአገኘው አንዲከላከል ብይን ሰጥቷል፡፡

ስለዚህ ተከሳሹ ተከላከለ ለማለት ያበቁትን በሰውና በሰነድ ማስረጃ የተነገሩበትን ድርጊቶች አለመፈፀማቸው ለማስረዳትና ለማስፈረስ ያነጣጠረ መከላከያ ማቅረብ የሚጠበቅበት እንጂ በአባባል ማስተባበል የማይቻለው ስለሆነ ክርክሩ በማስረጃ አስደግፎ ያላስረዳ ስለሆነ አባበሉ የሚገልፀውን የልዩ ዐ/ህግ ክስና ማስረጃ ለማስተባበል በሕግ እና በማስረጃ ብቃት የተደገፈ ሆኖ ስላላገኘነው ክርክሮቹ ፍ/ቤቱ አልተቀበላቸውም

ሌላው ያቀረበው የመቃወሚያ በተመለከተ በወ/መ/ሕግ/ቁጥር 281 ስር የቀረበው ክስ የዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ስለጂኖሳይድ የወሰነውን በሚቃረን መልኩ በስህተት እንዲካተት መደረጉ ከዓለም ህግና በ1948 ዓ.ም ከወጣው ሕገ መንግስት መንፈስ ውጪ በመሆኑ ሊያስከስሰኝ አይችልም

ተመሳሳይ ክስ በ1ኛ እና 6ኛ ወንጀሎች እንዲቀርቡ መደረጉ ያለአግባብ ነው

ወንጀሉ የተፈጸመበት ቦታ ሰዓት፣ወርና ቀን፣ዓ.ም አልተገለፀም የሚለውና ከይርጋ ሕግ ጋር በተያያዘ ሆነ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.130 መሰረት ተደርገው መቅረብ ይገባቸው የነበሩ ሆነው የቀረቡትን መቃወሚያዎች ፍ/ቤቱ ዘርን የማጥፋት በሰብዐዊ

ዐቃቤ ሕግ ግልባጭ

238

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ፍጥረት የሚፈፀም ወንጀል በሚደነግገው በወ/መ/ህግ/ቁ.281 ስር የሚወደቅ ክስ መሆኑን በመቀበልና በወቅቱም ቀርበው የነበሩ መቃወሚያዎች ውድቅ በማድረግ የክሶቹ አመሰራረትና አፃፃፍ በወ/መ/ህ/ቁጥር 281፣522፣538 እና 32/1/ለ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ የቀረቡ ክሶች ግልፅና የማያሻማ ይዘት ያላቸው ናቸው በማለት ተቀብሎ ተከሳሽ እምነት ክህደት ቃሉን እንዲሰጥ ተደርጎ በመካዱ ክሱን የሚያስረዳው ማስረጃ እንዲቀርብ ከተደረገና ክርክሩ ተካሄዶ ከተከሳሽ አስተያየት ጋር እንዲከላከል የሚያደርግ ብይን ከተሰጠ በኋላ የቀረቡ ሆነው ስለተገኙና በመከላከያ መከራከሪያነት ሊቀርቡ የማይገባቸው ሆነው ስለተገኙ ፍ/ቤቱ ውድቅ እንዲሆን ወስኗል፡፡

በልዩ ዓ/ህግ የስነድ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ቀደም ሲል አቅርባቸው የነበሩ በወቅቱ ታይተው የታለፉትን አሁንም የቀረቡት አልተቀበልናቸውም

ተከሳሽ በማስረጃነት የጠቀሳቸው በሌላ የክርክር መዝገብ የተሰጡ ውሳኔዎች ክርክሮች በዚህ መዝገብ ለቀረበው አግባብነት ስለሌላቸው አልተቀበልናቸውም

ደርግ ህጋዊ መንግስት ነው የሚሰራባቸው ሕጎች አውጥቷል፡፡ መንግስቱ የፖለቲካ በድኖቹን ዕውቅና አልሰጠም ፀረ አብዮት ብድኖች ከወዛደሩ ፖርቲ ውጭ ናቸው የአብዮተኞች ዘመቻ አዋጅ የወጣው ፀረ አብዬተኞች ለመደምሰስና ለመከላከል የወጣ ነው ይህም ለመተግበር በሰሜን ጎንደር ብሔራዊ ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ በህግ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ይህ ሀላፊነት የተሰጠው ማንኛውም ሰው በተግባር ማዋል ሕጋዊ ግዴታው ነው፡፡ የበላይ ትዕዛዝ ማስፈፀሜ የህግ ከለላ ነው፡፡ ወደ ክልሉ የሄድኩት በደርጉ ሊ/መንበር ትዕዛዝ ነው፡፡ በበላይ ትዕዛዝ ለፈፀምኩት ድርጊት አያስጠይቀኝም በትዕዛዙ መሰረት ባልፈፅም ለሕይወቴ ያሰጋኝ ነበር ለሚለው ክርክር ጊዚያዊ ወታደራዊ መንግስት በመንግስትነት ቢቋቋምም በአገር ውስጥ በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህግጋት ሥር የተደነገጉትን የሰብዐዊ መብት ሕጎችን በመጣስ የወንጀል ተግባር ከፈፀመ በወንጀል አይጠየቅም ማለት አይደለም፡፡ መንግስት ሕገወጥ ተግባር ተፈጽመዋል ካለ በሀገሪቱ ሕግመሰረት ስለ ተጠርጣሪነት ስለመያዝና ማሰር ከታሰረም በኋላ ስለአያያዝና ፍትሕን የማግኘት መብት የሚደነግጉ ሕጎች ተፈፃሚነታቸው በጠበቀ መልኩ በፍትሕ መድረክ እንዲፈረድበት በማድረግ በፍርድ መሰረት መቅጣት ነው፡፡ ተከሳሽ ተከላከል የተባለበትን የወንጀል ድርጊቶች በአዋጅ ቁጥር 129/69 አ.ዘ.አ.ኮ.ን. ያቋቋመው አዋጅ በሚፈቅደው ሥልጣንና ተግባር የተፈፀመ የአ.ዘ.አ.ኮ.ውሳኔ ስለሆነ ሕጋዊ ተግባር ነው የሚያስጠይቅ አይደለም የሚለው ዋና የመከራከሪያ መከላከያው ነው በመሰረቱ አዋጅ ቁጥር 129/69 አ.ዘ.አ.ኮ.ን. ለማቋቋምና ሥልጣኑን ለመወሰን የወጣ አዋጅ መሆኑ ይታወቃል ሆኖም ግን ይህ አዋጅ ዋናውን የወንጀለኛ መቀጫ ሕግና ሥነ-ሥርዓትን የማይሽር ከመሆኑም ባሻገር በማንኛውም ደረጃ ለሚገኙ የአ.ዘ.አ.ኮ አባላት ነጭ ሽብርን

ዐቃቤ ትክክል ገልባጭ

259

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

በቀይ ሽብር ለውጡ በሌላ አነጋገር ፀረ-ሕዝቦችን ግደሉዋቸው የሚለውን ሥልጣን አልሰጣቸውም፡፡ እንዲከላከል ብይን በተሰጠባቸው ድርጊቶች የተገለፁት ሰዎች በተቃዎሚነት ተኩስ ከፍተው በተኩስ ልውውጥ የተገደሉ ሳይሆን በክሱ እንደተመለከተው መቃወም በማይችሉበት ተከሳሹ በአደራጃቸው ተይዘው በሚያዘው እስር ቤት በቁጥጥር ስር የነበሩ ለመሆኑ በልዩ ዓ/ሕግ ማስረጃ ተረጋግጧል ግድያ ፍርፋትና ጉዳት የደረሰባቸው ፀረ-አብዮትና ፀረረ-ሕዝቦች ተብለው ነው፡፡ ሰዎች ፀረ-ሕዝቦች ናቸው አይደሉም? ሆነው ምን ወንጀል ሰሩ? የሚለው ጉዳይ ከማስረጃ ጋር በማገናዘብ የመረመረና ጥፋተኛ መሆኑን ሲረጋገጥ ሕጋዊ እርምጃ የመውሰድና የማስወሰድ ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት ብቻ ሲሆን ተከሳሽ ከግብረ አበሮቹ ጋር በሌላ ህግም ሆነ በአዘአኮ አዋጅ ቁጥር 129/69 በተሰጠው ስልጣን ነጭሽብር በቀይሽብር ይለወጥ በማለት ውሳኔ ማስተላለፍ ህጋዊ አያሰኘውም፡፡ በዚህም ተጎጂዎቹ እርምጃ የተወሰደባቸው የወንጀል ሕግና ሥነ-ሥርዓት መሰረት ባደረገ ዳኝነት ለማየት ሥልጣን በተሰጠው የዳኝነት አካል ታይቶ በተሰጠ ፍርድ በመሆኑ ብይኑን ሊያስለውጥ የሚያስችልና የልዩ አቃቤ ህግ ክስና ማስረጃ የሚያፈርስ ማስረጃ አላቀረበም በመሆኑም ድርጊቱን የፈፀምኩት በህግ መሰረት ነው ቢልም ይህንን የሚያስረዳለት ማስረጃ ሳያቀርብ የሀገሪቱን ሕግ በመተላለፍ በፈፀመው የወንጀል ተግባር መከላከያ ሊሆን የማይችል ነው፡፡

ተከሳሹ ወደ ጎንደር የተላከው ትዕግስት የሌለው የወታደርነት ባህሪ ያለው በመሆኑ ሊታገል ነው የሚል ማስረጃ ያቀረበ ቢሆንም ተከሳሹ ጎንደር የሄደው አለመገደዱ የሚያሳይ ሲሆን የፈፀመው የወንጀል ተግባርም ሊያስወግደው የማይችል መገደድ ስር ሆኖ ለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም ተከሳሹ ድርጊቱን የፈፀምኩት ታዝዤ ነው ቢልም ፍፁም መገደድ የሌለበት ሁኔታ የተሰጠው የበላይ ትዕዛዝ ሕገወጥ ድርጊት እንዲፈፀምበት ከሆነ መፈፀም እንደሌለበት የህግ ግዴታ መኖሩን እያወቀ ለፈፀመው የወንጀል ተግባር ድርጊቱ የፈፀምኩት ታዝዤ ነው ማለት መከላከያ ሊሆነው የማይችል ስለሆነ አልተቀበልነውም

ተከሳሹ ቤቴ ተበርብሮ መከላከያ ሊሆነኝ የሚችል ማስረጃ ጠፍቶብኛል ያለ ቢሆንም ምን እንደጠፋበት በዝርዝር ባልገለፀበት ሁኔታ ተከሳሹ ማስረጃ ጠፍቶበታል ለማለት አስቀድሞ የሚመለከተው አካል አቅርቦ ያረጋገጠበትን አላቀረበም

ተከሳሹ የመግደል ሙከራ ተፈፅሞብኛል፡፡ ማለቱ ድርጊቱ ሕገወጥ ቢሆንም የመግደል ሙከራ ኢ.ህ.አ.ዲ.ግ የፈፀመበት ለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም አድራጊው ከታወቀም ክስ የሚቀርብበት እንጂ መከላከያ ሊሆነው የሚችል አይደለም፡፡

በተከሳሹ ላይ የስም ማጥፋት ወንጀል ተፈፅሞብኛል ይበል እንጂ ማን እንደፈፀመበት አልገለፀም ተፈፅመዋል ቢባል እንኳ ስም አጥፊው በሕግ ከመጠየቅ

240

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

አልፎ ለቀረበበት ክስ መከላኪያ ማቅረብ ባለበት ደረጃ ይህንኑ በመከላከያነት የልዩ ዓ/ህግ ማስረጃ ለማፍረሱ ማቅረቡ የሚያስረዳለት አይሆንም ተገቢነትም የለውም በመሆኑም አልተቀበልነውም

የተደረገው አጠቃላይ ክርክርና የቀረበው ማስረጃ በማገናዘብ ፍ/ቤቱ ሲመዝነው ተከሳሹ በልዩ ዓ/ሕግ ከቀረበበት ክስ ውስጥ በ284ኛ ክስ ከተመለከቱት ወ/ር ታደሰ ደገፉ በዳሶ፣ ወ/ር ሲሳይ ቦጋለ ጥላዬ እና ወ/ር ዓለማየሁ አዱኛ በየነ፣ወ/ር አዱኛ አበራ በስተቀር በሌሎች ተከላከል የተባለባቸው ክሶች በማስረጃ የተነገረበት በማነጣጠር የልዩ አቃቤ ሕግን ክስና ማስረጃ በመፈታተን ተቃራኒውን አስረድቶ ማፍረስና ማስተባበል ያልቻለ ሆኖ ተገኝቷል።

በመሆኑም ተከሳሹ የጊ.ወ.አስተዳደር.ግ ወይም መንግስት የጎንደር ክፍለ ሀገር ዋና አስተዳደሪና የአብዮትና ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ ሊ/መንበር ሆኖ ሲሰራ በክሱ የተመለከተውና በማስረጃ የተረጋገጠውን ድርጊት በመፈፀምና እንዲፈፀም ያደረገውን ሥራ ውጤት ዓለም አቀፍን የሚደነግገው የመኖር መብት መርህ በሚፃረር ስለሰብአዊ አያያዝና የአካል ነፃነትን የሚደነግጉ ሕጉች በጣሰና ያልተሻረውን የወንጀለኛ ሕግና ሥነሥርዓትን በሚቃረን ሥልጣን ማይኖረው ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ሰዎች ከሕግ ውጪ እንዲያዙ እንዲመረመሩ እንዲገረፉና እንዲገደሉ የሚያስደርግ ሥልጣን የሚሰጥ ትዕዛዝ በማስተላለፍ ተጠርጣሪነቱንም ከፀረ-ሕዝብ ሆኖ በመገኘት በሰፋ/መልኩ/ ማስኬድ እንዲያስችለው ሰዎች በአነስተኛ ወንጀሉችም ጥርጣሬ መነሻ በማድግ በፈለገው መልኩ የተለያየ እርምጃ በውሰድ የሚያስችል የዲሲፒሊን መመሪያ አውጥቶ በማስተላለፍ ይህንንም በሚተገብሩለት በራሱ ብቻ የሚታዘዙትን ቡድኖች ኮሚቴዎች በማወቀር እንዲታሠሩ ማድረጉ አፈፃፀሙም በተማከለና ሚስጢራዊ በሆነ የመቆጣጠር መንገድ እየተከታተለ በሚያቀርብበት ውሣኔም በማጽደቅና በቀረበለት የምርመራ ግኝት መግለጫ ላይም እየወሰነ ለሚፈጽሙ ክፍሉች እያስተላለፈ መፈፀሙንም እንዲያረጋግጡለት እየተቆጣጠረ በማስፈፀምና በመፈፀም ተግባሩ የተገኘ መሆኑና በክሱ በተመለከቱትን ተጉጂዎች ላይ በማስረጃ በተነገረው መልኩ ጉዳት ያስከተለ በርካታ ተጉጂዎች በተጠረጠሩበት ቀላል የሥርቆት ወንጀል ምክንያት በሚመስለው ሲታይ በክርክር በማስረጃ ቢረጋገጥ እንኳ ቢባል የመጨረሻ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት ቅጣት ገደብ በማያልፈው ጭምር በበርካታ ሰዎች ላይ ግድያ እንዲፈፀምባቸው የተደረገ መሆኑን የሚያስረዳ ሆኖ ስለተገኘ ተከሣሹ ተከላከል በተባለባቸው የክስ ድርጊቶች፣

በ284ኛ የተጠቀሱት አራት ሰዎች ግድያ በስተቀር፣

1/ ከ1ኛ ክስ እስከ 54ኛ ክስ በ56ኛ ክስ እስከ 87ኛ ክስ፣ከ89ኛ ክስ እስከ 114ኛ ክስ፣ በ116ኛ እና 117ኛ ክስ ከ119ኛ ክስ እስከ 138ኛ ክስ 148ኛ ክስ/119-148/ከክስ 150ኛ እስከ 192ኛ ክስ ከ194ኛ ክስ እስከ 196ኛ ክስ ከ198ኛ ክስ እስከ 206ኛ ክስ ከ208ኛ ክስ እስከ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

210ኛ ከስ ከ212ኛ ክስ እስከ 230ኛ ክስ ከ233ኛ ክስ እስከ 247ኛ ከሰ ከ249ኛ ክስ እስከ 258ኛ ክስ በ261ኛ ክስ እስከ 263ኛ ክስ እስከ 273ኛ ክስ ከ276ኛ ክስ እስከ 283ኛ 285ኛ ክስ እና በ292ኛ ክስ ድርጊቶች 276፣283 በድምሩ በ579 ሰዎች/አምስት መቶ ሰባ ዘጠኝ/ ግድያ ማስፈፀምና ተሳታፊነት ተጠቅሶ በቀረበበት የሕግ አንቀጽ ሥር ጥፋተኛ ነው በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ149/1/ መሠረት ፍ/ቤቱ ወስኗል።

2/ ከክስ 293ኛ እስከ 294ኛ ክስ ከ296ኛ ክስ እስከ 300ኛ ክስ ከ302ኛ ክስ እስከ 387ኛ ክስ ከ389ኛ ክስ እስክ 395ኛ ክስ ከ397ኛ እስከ 421ኛ ክስ ከ423ኛ ክስ እስከ 440ኛ ክስ 440ኛ ከ442ኛ ክስ እስከ 455ኛ ክስ ከ457ኛክስ እስከ 463ኛ ክስ ከ465ኛ እስከ 466ኛ ክስ ከ468ኛ እስከ 536ኛ ክስ እና ከ538ኛ ክስ እስከ 540ኛ ክስ በድምሩ 392ሰዎች ግድያ በወ/መ/ሕ/ቁጥር 32/1/ ለ እና 522 ሥር ጥፋተኛ ነው በማለት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 149 መሠረት ፍ/ቤቱ ወስኗል።

3/ በክሱ 541ኛ እስከ 553ኛ ክስ ከ555ኛ ክስ እስከ 566ኛ ክስ ከ568ኛ ክስ እስከ 574ኛ ክስ እና ከክስ 376ኛ እስከ 605ኛ ክስ ተጠቅሶ በቀረበበት የሕግ አንቀጽ ሆነ ተብሎ ስለተደረገ ከባድ የአካል ጉዳት ወንጀል ክስ ስር በ83ሰዎች/ሰማንያ ሶስት/ላይ አካል ጉዳት ማድረስ ጥፋተኛ ነው በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 149 መሠረት ፍ/ቤቱ ወስኗል የቅጣት አስተያየት ካላቸው ያቅርቡ ብለናል።

ልዩ ዐ/ሕግ በ2/03/98 የተሻ አስተያየት /የቅጣት/3ገጽ አቅርበዋል ኮፒ ለተከሣሽ ተሰጥቷል ተከሣሹ የቅጣት ማቅለያ አስተያየት ለማቅረብ ጊዜ እንዲሰጠው ጠይቋል።

ተ ከ ሣ ሽ

1) ተከሣሽ የሚቀርበውን የቅጣት አስተያየት ከቀጠሮ በፊት በማ/ቤት በኩል በመላክ ያያይዝ
2) ተከሣሽ ያለባቸውን የጡረታ ችግር ማስወገድ እንዲችሉ ማ/ቤቱ ለ4ቀን አጃቢ እንዲመድላቸው አዘናል።

የቅጣት ውሣኔ ለመስጠት ለ26/3/98 ዓ/ም ተቀጠረ።

የዳኞች ፊርማ፣ሠለሞን አረዳ
ሐፊዝ አባጀማል
ረዳኢ በላይ

ECLN

ፀሐ ትክክል ግልባጭ

243

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

የኮ.ቁ.03112

ህዳር 29 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፣ ሠለሞን አረዳ

ሐፊዝ አባጀማል

ረዳኢ በላይ

ከሳሽ.....ልዩ አቃቤ ህግ አቶ ዩሴፍ ኪሮስ ቀርቧል

ተከሳሽ.....ሻለቃ መላኩ ተፈራ ከማዕከል ማ/ቤት መቅረባቸው አረጋግጠናል፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው በተከሳሹ ላይ ቅጣት ለመወሰን ሲሆን ፍ/ቤቱም ተከሳሹ ጥፋተኛ በተባለት የወንጀል ድርጊት ከልዩ አቃቤ ህግ እና ከተከሳሹ የቀረበው የቅጣት አስተያየት ህጉን በማገናዘብ ተከታዩን የቅጣት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ቅ ጣ ት፣

ተከሳሹ በልዩ አቃቤ ህግ ክቀረበበት ክሶች ውስጥ ጥፋተኛ የተባለው ከ1969 ዓ.ም. አንስቶ እስከ 1975 ዓ.ም. ድረስ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳዳር ደርግ ወይም መንግስት የጉንደር ክፍለ ሃገር ዋና አስተዳደርና የአብዮትና ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ ሊ/መንበር ሆኖ ሲሠራ በሌላ መዝገብ ክስ ክቀረበባቸው ግብረአበሮቹ ጋር በመሆን በፖለቲካ ተሳስሮ የተቋቋመውን የህብረ ብሔርን ማህበራዊ የሆነ ክፍለ ህዝብ በመላው ወይም በከፊል ለማጥፋት በግብረአበርነት በማቀድ የጥፋቱን ሥራ በማቋቋም ትዕዛዝ በመስጠት እንዲሁም ይህንኑ አድራጉት ሥራ ላይ በማዋል የተለያየ የምርመራ የማሰቃያና የመግደያ አካላት በማደራጀት መቺ ኃይል እስፔሻል ፎርስና የመብረቅ ኮሚቴ በማዘጋጀት ነፃ እርምጃ ቀይ ሽብር በማካሄድ የፖለቲካ ትስስር የነበራቸው ሰዎች እንዲገደሉ በማድረግ1ኛ በድርጊት፣

1፣2፣3፣4፣5፣6፣7፣8፣9፣10፣11፣12፣13፣14፣15፣16፣17፣18፣19፣20፣21፣22፣23፣24፣25፣ 26፣27፣28፣29፣30፣31፣32፣33፣34፣35፣36፣37፣38፣39፣40፣41፣42፣43፣44፣45፣46፣4748

ሻለቃ ደሬካ ግልባጭ

243

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

፣ 49፣ 50፣ 51፣ 52፣ 53፣ 54፣ 56፣ 57፣ 58፣ 59፣ 60፣ 61፣ 62፣ 63፣ 64፣ 65፣ 66፣ 67፣ 68፣ 69፣ 70፣ 71
፣ 72፣ 73፣ 74፣ 75፣ 76፣ 77፣ 78፣ 79፣ 80፣ 81፣ 82፣ 83፣ 84፣ 85፣ 86፣ 87፣ 89፣ 90፣ 91፣ 92
93፣ 94፣ 95፣ 96፣ 97፣ 98፣ 99፣ 100፣ 101፣ 102፣ 103፣ 104፣ 105፣ 106፣ 107፣ 108፣ 109፣ 110,111
፣ 112፣ 113፣ 114፣ 116፣ 117፣ 118፣ 120፣ 121፣ 122፣ 123፣ 124፣ 125፣ 126፣ 127128፣ 129፣ 130
፣ 131፣ 132፣ 133፣ 134፣ 135፣ 136፣ 137፣ 138፣ 139፣ 140፣ 141፣ 142፣ 143፣ 144፣ 145፣ 146፣ 147
፣ 148፣ 150፣ 151፣ 152፣ 153፣ 154፣ 155፣ 156፣ 157፣ 158፣ 159፣ 160፣ 161162፣ 163፣ 164፣ 165፣
166፣ 167፣ 168፣ 169፣ 170፣ 171፣ 172፣ 173፣ 174፣ 175፣ 176፣ 177፣ 178፣ 179፣ 180፣ 181፣ 182፣
183፣ 184፣ 185፣ 186፣ 187፣ 188፣ 189፣ 190፣ 191፣ 192፣ 194፣ 195፣ 196፣ 198፣ 199፣ 200፣ 201፣
202፣ 203፣ 204፣ 205፣ 206፣ 208፣ 209፣ 210፣ 212፣ 213፣ 214፣ 215፣ 216፣ 217፣ 218፣ 219፣ 220፣
221፣ 222፣ 223፣ 224፣ 225፣ 226፣ 227፣ 228፣ 229፣ 230፣ 233፣ 234፣ 235፣ 236፣ 237፣ 238፣ 239፣
240፣ 241፣ 242፣ 243፣ 244፣ 245፣ 246፣ 247፣ 249፣ 250፣ 251፣ 252፣ 253፣ 254፣ 255፣ 256፣ 257፣
258፣ 261፣ 263፣ 264፣ 265፣ 266፣ 267፣ 268፣ 269፣ 270፣ 271፣ 272፣ 273፣ 276፣ 277፣ 278፣ 279፣
280፣ 281፣ 282፣ 283፣ 285 እና በድርጊት 292ኛ ድርጊት በድምሩ 579/አምስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሰዎች ግድያ ተሳታፊነት በማስረጃ በረጋገጡና መከላከል ባለመቻሉ በወንጀለኛ መ.ህግ ቁጥር 32/1/ለ እና 281/ሀ ሥር የተመለከተው ዘርን ስለማጥፋት በሰብአዊ ፍጥረት ላይ ስለሚደረግ ወንጀል ተላልፎ በመገኘቱ ነው።

2ኛ በክስ 293፣ 294፣ 296፣ 297፣ 298፣ 299፣ 300፣ 302፣ 303፣ 304፣ 305፣ 306፣ 307
፣ 308፣ 309፣ 310፣ 311፣ 312፣ 313፣ 314፣ 315፣ 316፣ 317፣ 318፣ 319፣ 320፣ 321፣ 322፣ 323፣ 324
፣ 325፣ 326፣ 327፣ 328፣ 329፣ 330፣ 331፣ 332፣ 333፣ 334፣ 335፣ 336፣ 337፣ 338፣ 339፣ 340፣ 341
፣ 342፣ 343፣ 344፣ 345፣ 346፣ 347፣ 348፣ 349፣ 350፣ 351፣ 352፣ 353፣ 354፣ 355፣ 356፣ 357፣ 358
፣ 359፣ 360፣ 361፣ 362፣ 363፣ 364፣ 365፣ 366፣ 367፣ 368፣ 369፣ 370፣ 371፣ 372፣ 373፣ 374፣ 375
፣ 376፣ 377፣ 378፣ 379፣ 380፣ 381፣ 382፣ 383፣ 384፣ 385፣ 386፣ 387፣ 389፣ 390፣ 391፣ 392፣ 393
፣ 394፣ 395፣ 397፣ 398፣ 399፣ 400፣ 401፣ 402፣ 403፣ 404፣ 405፣ 406፣ 407፣ 408፣ 409፣ 410፣ 411
፣ 412፣ 413፣ 414፣ 415፣ 416፣ 417፣ 418፣ 419፣ 420፣ 421፣ 423፣ 424፣ 425፣ 426፣ 427፣ 428፣ 429
፣ 430፣ 431፣ 432፣ 433፣ 434፣ 435፣ 436፣ 437፣ 438፣ 439፣ 440፣ 442፣ 443፣ 444፣ 445፣ 446፣ 447
፣ 448፣ 449፣ 450፣ 451፣ 452፣ 453፣ 454፣ 455፣ 457፣ 458፣ 459፣ 460፣ 461፣ 462፣ 463፣ 465፣ 466
፣ 468፣ 469፣ 470፣ 471፣ 472፣ 473፣ 474፣ 475፣ 476፣ 477፣ 478፣ 479፣ 480፣ 481፣ 482፣ 483፣ 484
፣ 485፣ 486፣ 487፣ 488፣ 489፣ 490፣ 491፣ 492፣ 493፣ 494፣ 495፣ 496497፣ 498፣ 499፣ 500፣ 501፣
502፣ 503፣ 504፣ 505፣ 506፣ 507፣ 508፣ 509፣ 510፣ 511፣ 512፣ 513፣ 514፣ 515፣ 516፣ 517፣ 518፣
519፣ 520፣ 521፣ 522፣ 523፣ 524፣ 525፣ 526፣ 527፣ 528፣ 529፣ 530፣ 531፣ 532፣ 533፣ 534፣ 535፣
536፣ 538፣ 539 እና 540ኛ ክስ የተገለፁትን በድምሩ 392/ሶስት መቶ ዘጠና ሁለት ሰዎች /ግድያ ተሳታፊነት በማስረጃ በመረጋገጡና ተከሳሽ መካላከል ባለመቻሉ በወ/መ/መህ/ቁ 32/1/ለ እና 522/1/ሀ የተመለከተው ከባድ የግፍ አገዳደል ወንጀል ተላልፎ በመገኘቱ።

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

3ኛ በክስ 541፣542፣543፣544፣545፣546፣547፣548፣549፣550፣551፣552፣553፣554 ፣555፣556፣557፣558፣559፣560፣561፣562፣563፣564፣565፣566፣567፣568፣569፣570፣571 ፣572፣573፣574፣576፣577፣578፣579፣580፣581፣582፣583፣584፣585፣586፣587፣588፣589 ፣590፣591፣592፣593፣594፣595፣596፣597፣598፣599፣600፣601፣602፣603፣604፣እና 605ኛ ክስ በድምሩ 83/ሠማንያ ሶስት/ሰዎች ላይ ሆነ ተብሎ ስለተደረገ ከባድ የአካል ጉዳት ተሳታፊነት በማስረጃ በመረጋገጡና ተከሳሹም መከላከል ባለመቻሉ የኢትዮጵያ ወ.መ.ህግ ቁጥር 538/538/የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት ተላልፎ በመገኙቱ ነው።

የልዩ አቃቤ ህግ በቁጥር ከ-5/108/98/ል0 በ02/03/98 የተፃፈ አስተያየት አቅርበዋል ይዘቱም።

- ተከሳሹ በከፍተኛ የስልጣን ደረጃ ላይ ይገኝ የነበረ በመሆኑ

- ይህን ከፍተኛ ስልጣኑን ለህዝብ ጥቅምና እድገት ከማዋል ይልቅ በተመደበበት ማማስት ራሡን ከሃገሪቱ ህግ፣ልማድ እና ሥርዓት ውጭ ራሡን የክፍለ ሃገሩ የህግ አውጪ፣ህግ ተርጓሚ እና አስፈፃሚ በማድረግ የራሡን ልዩ ኃይልና መርማሪ በማደራጀት የዘር ማጥፋቱን የግፍ አገዳደል ወንጀሎችን ሥራ መጠነ ሠፊ በሆነ ሁኔታ እንዲፈፀም በከፍተኛ ሁኔታ ስልጣኑን የተጠቀመበት በመሆኑ።

ተከሳሹ ከሌሎች የሃገሪቱ ክፍለተ ሃገራትና ባለስልጣናት በተለየ ሁኔታ በመደበኛ ፍርድ ቤት ዳኝነት የሚታዩ ጉዳዩችን ሣይቀር በስልጣኑ ቀምቶ ራሱን የዳኝነት አካል በማድረግ እጅግ አሰቃቂ የሆኑ እና የጥንታዊ ጋርዩሽ ሥርዓት ማህበርን የሚያስታውሱ ሁኔታዎች የሠው ልጅ በገበያ ቦታ ተሰቅሎ ወይም በጥይት ተደብድቦ እንዲገደል ገበያተኛው በተሰበሰበበት ጀርባው በጅራፍ እንዲገረፍ በቀጥታ በማዘዝ እጅግ አሰቃቂ የሆኑ ወንጀሎችን መፈፀሙ።

ለወንጀሉ ለአፈፃፀም እንዲያመቸው ራሡ ብቻ የሚያዛቸው ልዩ ኃይል የሚባሉና በካባቢው በጨካኝ ተግባራቸው የሚታወቁና የሚፈሩ ወታደሮች በማደራጀት በቀጥታ በመምራት ተበዳዩቹን ከህግ ውጭ እንዲገደሉ ወይም እንዲገረፍ በቀጥታ በማዘዝና የሠጠው ትዕዛዝም ስለመፈፀሙ ራሡ በመከታተል ወንጀሉ እንዲፈፀም ማድረጉ ይፈፅመው የነበረውን ወንጀል ሠውን ለመጉዳት ፍፁም ፍቃደኛ በመሆን እጅግ ልዩ በሆነ ክፋትና ጨካኝነትን የሚያሳይ ሁኔታ በመሆኑ።

ተከሳሹ የወንጀል ተግባሩን የፈፀመው በጎንደር ክ/ሃገር በተንቀሳቃሽ የደርግ አባልነት ከተመደበበት ከ1969 ዓ.ም. ጀምሮ ክ/ሃገሩን እስከለቀቀበት 1976 ዓ.ም. ድረስ መሆኑ ሲታይ ተከሳሹ ወንጀል መፈፀም መያውና ተግባሩ ያደረገው መሆኑን የወንጀሉ አፈፃፀም ሲታይ በአብዛኛው ግድያዎች ይፈፀሙ የነበሩት በሌሊትና በተበዳዩች ቤተሠቦችና ሌሎች ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ እጅግ ጨካኝ በሆነ ሁኔታ መሆኑ ሲታይ የወንጀሉ አፈፃፀም በሌሎች ሰዎችና በተበዳይ ቤተሠቦች ላይ ሽብርና ፍርሃትን

ECHN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

በሚፈጥር ሁኔታ የተፈፀመ በመሆኑና በተደጋጋሚ እና ተደራራቢ ወንጀሎች በመፈፀሙ::

ተከሳሹ በክ/ሃገሩ ለተፈፀሙ የዘር ማጥፋትና ከባድ የግፍ አገዳደል እና ከባድ የአካል ጉዳት ወንጀሎች በሙሉ ዋና ጠንሳሽ ትዕዛዝ ሠጭና የወንጀሉ ሥራ መሪ በመሆን ተግባሩን የፈፀመ በመሆኑ::

በተከሳሹ በግፍ እንዲገደሉ እና ጀርባቸው እንዲገረፉ የተደረጉ ተበዳዩች ክፍሉ ለሃገርና ለወገን ይጠቅማል ያሉትን ሃሳብ በማቅረብ ደርግ የገባውን ቃል ኪዳን አክብሮ ወደጦር ሠፈሩ እንዲመለስ በምትኩ ህዝባዊ መንግስት እንዲቋቋም የጠየቁ የሃገሪቱ ምርጥ ወጣቶች ሲሆኑ እነዚህ ተበዳዩች ተከሳሹ በቀጥታ በሚመራቸው የልዩ ኃይል አባላት ተሳደው ተይዘውና በቁጥጥር ሥር የነበሩ በህገወጥ ምርመራቸው አካላቸውና እምሮአቸው ዝሎ ተከሳሹ ለራሱ ቤተመንግስት ባቋቋመው እስር ቤቶችና ወህኒ ቤቶች የነበሩ ህጉ የተለየ ጥበቃና እንክብካቤ የሚያደርግላቸው እስረኞች ከፊሉ ደግሞ የሐገሪቱን ህግ ተላልፋችኃል ተብለው በፖሊስ ቁጥጥር ሥር የነበሩ ከጥቃቅን የሥርቆት ወንጀል ጀምሮ የሠው መግደል ወንጀል ፈፅማችኃል ተብለው በፍ/ቤት ቀርበው በመከራከር ላይ የነበሩ ወይም ወደ ፍ/ቤት ለመቅረብ በዝግጅትላይ የነበሩና ምናልባት ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ቢታይ መለቀቅን ጨምሮ አንስተኛ ቅጣት ሊጣልባቸው የሚችሉ ነገር ግን በተከሳሹ ህገ ወጥና ኢ.ሠብአዊ በሆነ ውሣኔ ለሞት ለማርፋትና ለእስራት የተጋለጡ እስረኞች መሆናቸው::

በተከሳሹ የዘር ማጥፋት አድራጎት አምስት መቶ ሰዎች በከባድ የግፍ አገዳደል ተደራራቢ ወንጀሎች ሶስት መቶ ዘጠና ሁለት ሰዎች በድምሩ ለዘጠኝ መቶ ሰባ ሁለት ሰዎች ግድያና ለሠማንያ ሶስት ሰዎች ከባድ የአካለ ጉዳት ወንጀሎች ጥፋተኛ በመሆኑ፣በድርጊቱም ከፍተኛ የሆነ ህይወት መጥፋትና አካል ጉዳት በማድረሡ ከላይ በተዘረዘሩ ምክንያቶች በወ.መ.ህ.ቁጥር 81/1/ሀ,ለ,ሐና መናሠ/188 እንዲሁም በወ/መ/ህ/ቁጥር 82/1/ሀ//189/1/ሀ መሠረት ተከሳሹ የሞት ቅጣት በሚያስከትሉ ተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ ተከሳሹ በሞት እንዲቀጣ ውሣኔ እንዲሠጥበት የሚያመለክት ነው::

ተከሳሹም ህዳር 6 ቀን 1998 ዓ.ም. የተፃፈ የቅጣት ማቅለያ አስተያየት 10 ገፅ አቅርበዋል ይዘቱም

እድሜዬ 58 አመት ሲሆን ለ15 አመት ያህል በስደትና በእስር ቤት አገኛለሁ ንብረቴም ተዘርፎ ባዶ እጄ ቀርቻለሁ ከግንቦት 22 1983 ደመወዝ የተቋረጠብኝና የጡረታ አበል የማላገኝ ነኝ ከቤተሠቤ ሥራ ያለው ስለሌለና ሌላ ገቢ ስለሌለኝ ከ12 ቤተሠቤ ጋር በከፍተኛ ችግር ላይ እገኛለሁ:: ቤት ኪራይ መክፈል አቅቶኝ ተከስሼ ተወስኖብኝ ወደፊት ሃብት ሳፈራ የፍርድ ባለዕዳ ነኝ::

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

የመጀመሪያዋ ልጄ በእናትዋ ሞትና በእኔ መታሠር ምክንያት እንደወጣች መቅረትዋ ያደረኩት ጥረት ስላልተሳካልኝ ልቤን በሐዘን የሠበረው በመሆኑ ጥፋት በሆነው ነገር ሁሉ ከልቤ ያዘንኩና የተፀፀትኩ ስለመሆኑ የሚልና ከሰውነቴ ያልወጣው ጥይት/እርሳስ/ከሳምባው ጋር በሚያደርገ ንክኪ ለከፍተኛ የሳል በሽታ እንዳደረገው በሐኪም የተነገረው መሆኑን የኦኘራሲዩን ጠንቅ የወገብና የኩላሊት ህመምተኛ ያደረገው መሆኑን የስኳር ነርቭና የአስማቲክ ብሮንካይትስ ህመምተኛ መሆኑን በአ/አበባ ዩኒቨርስቲ በልዑል ብዕደማርያም ላብራቶሪ ትምህርት ቤት የ12ኛ ክፍል ማጠናቀቁ ለ3 አመት በሐረር ጦር አካዳሚ ተምሮ በም/መቶ አለቃነት ማዕረግ መመረቁን በሐገር መከላከያ ሚኒስቴር በምድርጦር ልዩ ልዩ ክፍሎች በመስራት የሻለቃነት ማዕረግ መድረሡ ከነበረበት ክፍልም ተመርጦ የደርግ አባል ሆኖ መስራቱ የጉንደር ክፍለ ሐገር ዋና አስተዳዳሪ ኢ.ሠ.አ.ኮ ተጠሪ የኢ.ሠ.ፖ ፀሐፊ የኢ.ሠ.ፖ ማዕከላዊ ኮሚቴ ቁጥጥር ኮሚሽን ም/ሊ/መንበር በመሆን እስከ 1983 ግንቦት ወር መስራቱ በወንጀልም ተከሶና ተቀጥቶ የማያውቅ መሆኑን በእስር እያለም የማረሚያ ቤቱን ደንብ መመሪያና ትዕዛዝ በማክበር በተለያዩ የትምህርት መስኮች ተምሮ በከፍተኛ ውጤት መመረቁ።

ከ1969 ዓ.ም. መጀመሪያ ጀምሮ የሶማሊያ መንግስት ጦር የፈፀመው የማስፋፋት ወረራ ከውስጥ ኃይሎች መቀነባበር ለመመከትና ለመደምሰስ ህዝቡን ለማሳተፍ አዋጅ ቁጥር 110/69 መታወጅና ወደ 300 ሚሊሻ መዝመቱ የመደብ ትግል መካሄዱ የማይቀር እውነት መኖሩ የፖለቲካ መስመር ትግል በግራ ኃይሎች ጐራም ከፍተኛ ጉዳት ማድረሡ እንደማይቀር በኤርትራና በትግራይ በረሃዎች እንደሁም በኢ.ህ.አ.ፖ ውስጣዊ ትግል የታየው ይኸው አይቀሬ ክስተት መኖሩን የጉንደር ክፍለ ሃገርም በተካሄደው ሹምሽር ሂደት አካል አንዱ መሆኑን ፀረ ህዝብ ፀረ አንድነትና ፀረ አብዮት ኃይሎች የላቸውን በብዙ ወገኖች የመግደልና የማቁሰል አደጋ ማድረሳቸው የከተማው ነጭ ሽብር ከፖሊስና ከህግ አስከባሪ ኃይሎች ቁጥጥር ውጭ የነበረበት ወቅት መኖሩ ከጐንደር ከተማ በስተቀር ሁሉም የአውራጃና የወረዳ ከተሞች መዘረፋቸውን የደርግ ሊ/መንበር የሰፊው ህዝብ ሠላምና ፀጥታ የሃገሪቷ አንድነት እንዲጠበቅ የማድረግ በፀረ ህዝብና ፀረ አብዮተኞች ላይ እርምጃ የመወሰድ ስልጣን ይኖረዋል ተብሎ ስለተደነገገ ለባለስልጣኑ አለመታዘዝ በጦር ፍርድ ቤት በወ/መ/ህ/ቁ 311 እስከሞት የሚያደርስ ቅጣት የሚያስቀጣ መሆኑን በተመሣሣይ በአዋጅ ቁ. 129/69 መደንገጉ ከመፈፀም በቀር ሌላ የተሻለ አማራጭ መንገድ ማግኘት አለመቻሉ ከበላይ አካል የተሰጠው ቁርጠኛ ወታደራዊ ትዕዛዝ የሠራዊቱ ደንብ በማያዘው መሠረት ተቀብሎ ለመፈፀም መገደዱ ወደ 1ኛ ችሎት እንዲጠቃለልለት በግለፅ በጊዜው የነበረውን ውስብስብና አስቸጋሪ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በወ/መ/ህ/ቁ. 69/70/2፣76/1፣78፣79/1/ሀ እና 185 ፍ/ቤቱ በመሰለው ቅጣቱን ማቅለል ይችላለል ተብሎ በተደነገገው መሠረት ፍርድ ቤቱ በነፃ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ያሰናብተኝ ብለዋል። በማረሚያ ቤት የወሰዳቸው ልዩ ልዩ የትምህርት መስኮች የተሰጠው የምስክር ወረቀቶች አቅርበዋል።

ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል። ተከሳሹ ጥፋተኛ ነህ የተባለባቸው የህግ ድንጋጌዎች ማለት፣

1. የወ/መ/ህ/ቁጥር 281/ሀ እንደሚያዘው ከአምስት አመት እስከ እድሜ ልክ ፅኑ እስራት እጅግ ከባድ ከሆነ በሞት ፍርድ የሚያስቀጣ መሆኑን

2.የወ.መ.ህ.ቁ 522 እንደሚናገረው በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም በሞት እንደሚያስቀጣ

3.የወ/መ/ህ/ቁ. 538 እንደሚደነግገውም እስከ አስር አመት ሊደርስ በሚችል ፅኑ እስራት ወይም ከአንድ አመት በማያንስ እስራት እንደሚያስቀጡ ይናገራሉ። ቅጣት ለመስጠትም የወንጀሉ ከባድነትና ተከሳሹ የአፈፃፀም ባህርይ የሚኖረው አደገኛነት ተከሳሹም የቀድሞ ህይወት ታሪኩ እድሜው የግል ኑሮው ሁኔታና እንዲሁም ወንጀሉን ለመፈፀም ያነሳሱትን ምክንያቶችና ያሳቡን አላማ የትምህርቱን ደረጃ የጥፋቱን ከባድነትና ያፈፃፀሙን ሁኔታዎች በመገመት በራሡ አጥፊነት መሠረት ነው።

በተከሣሹ ላይ የሚጣለው ቅጣት ለመመጠን ቅጣትን የሚያቃሉሃ የሚያከብዱ ሁኔታዎች መኖራቸው ወይም አለመኖራቸው መፍተሹ ተገቢ ነው ተከሣሹ ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ በጉንደር ክፍለሀገር የደርግ/የመንግስት/አባል ተወካይ የዚሁ ክፍለሀገሩ ዋና አስተዳዳሪና የክ/ሃገሩ አዘአኮ ሊ/መንበር ሆኖ ይሠራ ነበር ይህንን ሥልጣኑን በመጠቀምም ፀረ ሕዘብ ነው ተብሉ የሚፈረጅው ለማጥፋትና ነጭሽብርን በቀይሽብር ለውጦ አርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ዕቅድ ነድፎ የቀበሌ የሕዝብ ደህንነት አባሉችና የፀጥታ አስከባሪዎች እያደኑ እንዲይዙ አብዩትዊ እርምጃ እንዲወስዱ/እንዲገድሉ/ፈቃድ ሣይኖረው ከከተማ ክልል ውጪ የሚገኝ የአካባቢው ገበሬ ማህበር በቁጥጥር ሰር እንዲያውለው የአካባቢው ፖሊስ ጣቢያም የወንጀለኛውን ጉዳይ አጣርቶ የምርመራ መዘገቡ በአሰቸኳይ በክፍለሃገሩ ተነቃናቂ የደርግ ቡድን ጽ/ቤት ለተቋቋመው አብዩታዊ ጦር ፍ/ቤት የማቅረብ ግዴታን የሚጥል ከመጋቢት 12ቀን 1969ዓ/ም ጀምሮ በተግባር የሚውል በቁጥር 147/69 በ12/7/69 በተፃፈ ለክፍለሀገሩ አስተዳደር ሕብረት ዕዝ መምሪያ ፖሊስ ዋና መምሪያ በአድራሻ በተፃፈ በግልባጭም በጉንደር ከተማ ይገኙ ለነበሩ 20 የቀበለ ማህበራት በአውራጃ ደረጃ የተቋቋመወ ለነበሩ መ/ቤቶች የዕቅዱን ማስፈፀሚያ ቁሚ ትዕዛዝ አስተላልፏል።

ይህም ብቻ ሣይሆን በፀረ አብዩተኝነት /ፀረ-ሕዝብነት/ከሚያስጠረጥር ምክንያት ሌላ በልዩ ልዩ ወንጀሉች ስለሚከሰሱ ሰዎች ውሣኔ አሰጣጥ አስመልክቶ በሌላ ገለልተኛ አካል እንዲታይ የሚያደርግና ተከሣሹ በለ/መንበርነት በሚመራው ቡድን ታይቶ በማንኛውም ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ አብዩታዊ እርምጃ /ግድያ/እንዲወሰድ መወሰኑና

ስለ ትክክል ግልባጭ

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

መፈፀም ሥልጣን ይሰጣል የተባለው የዲሲፕሊን መመሪያ አብዩታዊ ትምህርትና ከባድ ማስጠንቀቂያ መጠነኛ ቅጣት የሞት ቅጣት መስጠት የሚያስችል በ3ደረጃ መድቦ ማየት የሚያስችል እንዲሆን ገልጾ በሁኔታ መድቦ የሚታይ ድርጊት ነው የለውን በመዘርዘር በጥፋተኛቹ የተጠሪ የምርመራ መዝገብ በክፍለሀገሩ ለተቋቋመው ጦር ፍ/ቤት እንዲላክ እንዲያደርጉ መመሪያውም በስራቸው ለሚገኙ ክፍሉች እንዲያስተላልፉ ቋሚ ትዕዛዙ ለተላለፈላቸው ክፍሉች በተመሣሣይ ሁኔታ በቁጥር አዘአኮ/አለ3/288/70 ጥር 24ቀን 1970ዓ/ም በተፃፈ መመሪያ ሰጥቷል።

ዕቅዱንና ትዕዛዙን በተግባር ለማስፈፀም እንዲያስችለውም በተዋረደ ከተቋቋመው አዘአኮ በተጨማሪ ከቋቋማቸው ሀይሉች አንዱና አብዩታዊ ነፃ እርምጃ በመውሰዱ ትምህርት መሥጠትን ዓላማ አድርጉ የጦር ፍ/ቤትን ተክቶ ቀይሽብር ለማስፈጎም ሥልጣን ያለው ሆኖ ከተግባሮቹ አንዱ አጥፊናቸው በሚላቸው ላይ ቀይሽብር የሚያፋፋም ወሣኔ በመስጠት በደርግ ቡድን መሪው ማስፀደቅ የሚጠበቅበት መብረቅ የተባለ ኮሚቴ አቋቁመዋል ከፍ ብሉ በተገፀው መክንየት የሚጠረረጠረ ሰዎች የሚይዙ የሚመረምሩ እና በተጠርጣሪዎቹ ላይ የሚሰጠው ወሣኔ የሚያሰፈፀሙ በተከሣሽ ብቻ የሚታዘዙ የተለዩ የታጠቁ /አስፔሻል ፎርሶች/ሃይሉች አደራጅቷል።

ምርመራ የሚካሄድበት ቦታም ተከሣሹ በሚቀመጥበት ቤተ መንግስት ውስጥ እንዳሆን አድርገዋል። ከምርመራ በኋላም በወህኒ ቤት የሚያርፍበት የተለየ ክፍል እንዲዘጋጅ ተደርገዋል።

ይህንን መነሻ በማድረግ የተከናወነው ተግባር ስንመለከተው በዚህ ሁኔተ የተጠረጠሩ ሰዎች የሚያዙት ሕዝቡ እስፔሻሉች እያለ በሚጠራቸው የተለዩ ሀይሎች ከየሚሠሩበት ቦታከመንገድ እና ከየመኖሪያ ቤታቸው በማንኛውም ሰዓት ያለ ፍ/ቤት በመያዥና የመበርበሪያ ትዕዛዝ ሌሊትም በር እየበረገዱ ቤት ወስጥ በመግባት ልጅ የታዘለበትን አንቀልባ ማሠሪያ ሣይቀር እየበጠሱ የፊጢኝ በማሰር ከጉያዋ የምትነጠቀው ወላጅ እናት ሳትቀር እየተደበደቡ የጉን ስብራትና ጥርስ ማውለቅን በሚያስከትል መልኩ እየፈተሹም ወርቅ ሆነ ሌላ ንብረት እየወሰዱ ያስሩዋቸው እንደነበረ፣

ወደ ምርመራ ክፍል ከተወሰዱ በኋላም ኤሌክኘተር ስምንት ቁጥር እግርን አጣጥፎ እንደኪስ ሰቅሉ መደብደብ ውሃ በያዘ በርሜል ውስጥ እያስገቡ እያስወጡ በኤሌክትሪክ መግረፍ ውሃ ነክሮም ትንፋሽ ማሳጣትን በመሣሠሉት የግርፊያ ዓየነቶች ከበራብልት በተዘጋጀ አለንጋ አጠና በኤሌክትሪክ በሽቦ በገመድ የመግረፊያ መሣሪያዎች በመጠቀም በደም የተጨማለቀ ጨርቅ አፍ ውስጥ በመክተት ና ክላሽን እያደገኑ ይገርፉ እንደነበረ እንጠልጥለዋቸውም እየሄዱ ደም በአፋቸውና በአፍንጫቸው ይወጣ እንደነበረ ጥርሳቸውም ሁሉ የተነቀሉ እንደነበረ በብልታቸውም ላይ ይቆሙ እንደነበር በድብደባውና በቶርች ብዙት ሽባነት በሚያስከትል በሬንጅም እየጠበሱ ጀርባቸወ እጅና

249

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

እግራቸው ቆስሉና ተቆራርጦ እንደነበር በዚህም በምርመራ /መግረፊያ/ወጥተው ወደ ታሰሀረበት ክፍል በራፍ ላይ ሲደርሱ ቁስን ጨምሮ በግርፋቱ ሰዎቹ መሞተቸው በምርመራ ቦታም ተጠርጣሪዎቹ ስለማመናቸው ወይም አለመማመናቸው ተከሣሹ መቶ አለቃ አበራ ከተባለው የእስፔሳሎች/የተከሣሹ አጃቢዎች/መርማሪዎች/ሀላፊ ጋር በስልክ ይነጋገር እንደነበረ ምርመሪ መዝገቡ የቀረብልኝ ተከሣሽም ይቅረብልኝ እያለ እንደአስፈላጊነቱ ያዝዝ እንደነበረ በማስረጃ ተረጋግጧል።

በዚህ የምርመሪ ስልት ከተጠርጣሪዎቹ በተገኘ ቃል የምርመራ ግኝት እየተባለ በሚቀርበለት መግለጫ ላይ በቀጥታ እንዲያስፈጽሙ ያቋቋማቸውና የደራጃቸው ክፍሉች ብቻ ሊረዱት በሚችለ የሚሰጢር መግባቢያ ኮድ ማለትም የአማርኛና እንግሊዝኛ ሆኽያት ፊደላት ቃላት ሐረግ በመጠቀም እንዲሀም ቀይሽብር ይፋፋምበት አብዩታዊ እርምጃ የወሰድበት በ1ኛ ደረጃ አልፏል የሚልና የመሣሠሉትን ዓረፍተነገሮች በመጠቀም ውሣኔ ይሰጥ እንደነበር እንዲወስኑ ሥልጣን የሰጠቸው ካሚቴዎችም የሰጡትን ውሣኔ በማጽደቅ ውሣኔ ይሰጥ እንደነር ተረጋግጧል ኮዶቹ ውሣኔዎች ናቸው የሚያስተላለፉት እውነታም ግድያና ግርፋት መሆኑን ተረጋግጧል። ይህም አሰራሩ ውስብስብና ሚስጢራዊ እንዲሆን አድርጎታል ለጠርጣሪዎቹ ግን አደገኛ ሁኔታን ፈጥሮባቸዋል ውሣኔው የተጣለው ቅጣት ዓይነትና የሚፈፀምበት ሁኔታ እንዲሁም የሚፈፀምበት ቦታ የሚያካትትና ስለመፈፀሙ ሪፖርት እንዲደረግ የሚያዝ ነው።

በቶርች በተገኘው ቃል መሠረት ተደርጉ መወሰኑ በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘ ማስረጀ ውድቅ መሆኑን የሚደነግገው ሕግ የሚፃረር ከመሆኑም በላይ በዚህ ሕገ ወጥ ሥራው ከተመርማሪዎቹ ተገኘ በተባለው ቃለ አረቄ የጠጣበትን ላንድ የአረቂ መሊኪያ እስከ ቀንድ ከብት በሚደርስ ልዩ ልዩ ንብረት ሠርቋል በሚል ከ95/ዘጠና አምስት/ሰዎች ያላነሱ በማታለል ከ3ሰዎች ያላነሱ እምነት ማጉደል በሚል ከ4ያላነሱ ሰዎች የዘወትር ሌባ ነው በሚል 4ሰው ያላነሰ አደገኛ ሰራ ፈትና ኪስ አውላቂ ነወ በሚል ከ5ሰው ያላነሰ ማጅራት መቺ ነው በሚል ከአንድ ሰው ያላነሰ ተማሪዎች እንዳይማሩ አድርገዋል አነሳስተዋል ከፋፍለዋል በሚል/በአድማ/ በተያያዘ ከ11ሰው ያላነሰ ቤት አቃጥለዋል በሚል ከ2ሰው ያላነሰ ከ5ብር እስከ 200 ብር የሚደርስ ጉቦ ተቀብለዋል በሚል ከ10ሰው ያላነሰ ጥይትና መሣሪያ ሸጧል በሚል ከ16ሰው ያላነሰ ሕፃን ልጅ ሰው አፍነው ሸጧል በሚል ከ16ሰው ያለነሰ ዘርፈዋል በሚል ከ6ሰው ያላነሰ በድምሩ ከ165 ሰወ ያላነሱ የተገደሉበት ሁኔታ እና ለፈጥኖ ደራሽ አባሉች የምግብ ማብሰያ እንጨት አላመጣም ብለዋል 100 ኩንታል ጨው ደብቆ ተገኝቷል ሽጉጥና የቦንብ ቀለበት በፍተሻ ተገኝቶበታል ከመ/ቤቱ ውስጥ የግብረስጋ ግንኙነት ፈጽመዋል ለችግረኞች የመጣ 26 ኬሻ ሰሊጥ ሸጧል አድሃሪ ነጋዴና አራጣ አበዳሪ ነው ወታደሮች በወንበዴዎች መገደላቸው ሲሰማ እንኳን ሞቱ ብለዋል ጥይተ ይዞ ተገኝቷል አውቶማቲክ መሣሪያ

ስለ ትክክል ግልባጭ

250

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ይዞ ተገኝቷል ጦር መሣሪያ ይ ዞ በአብዩቱ ላይ ለመተኮስ ሞክረዋል አጭበርብሮ የቀበሌ ሊ/መንበር ሆኖአል ደርግን ከግብረአበሮቹ አውድመዋለሁ ብለዋል ጦር አልመራም አለ በሚል የመንግስት መሬት ያለካርኔ ለግለሰብ ሸጧል በሚል አወ/መሣሪያ ይዟል የተባሉት ከ3ሰው ያላነሰ በተቀሩት ምክንያቶች እንዳንድ ሰው በድምሩ ከ13ሰው ያላነሰ እንዲሁም መለቀቅ የማይገባው ሰው ለቀዋል በሚል ከ2ሰው ያላነሰ መገደሉን ስንረዳ

በስህተት ጓደኛውን ገደለዋል የሚለውን ጨምሮ ሰው ገድለዋል ወይም ለመግደል ሞክረዋል በሚል ከ86ሰው ያላነሰ ከምድብ ቦታው ጠፍቷል በሚል ከ27ሰው ያላነሰ ከወንበዴ ጋር ደብዳቤ ተፃጽፈዋል ለወንበዴ መሣሪያ አስረክበዋል ወንበዴ ቀልበዋል የወረዳ አስተዳዳሪ ቤት ለወንበዴ አሳይቷል ትምህርታቸውን አቋርጠው በውንብድና ተግባር ላይ ተሠማርቷል የጦር ሰፈር ሰልለዋል የወረዳ አስተዳዳሪ ሆኖ ከወንበዴዎች ጋር ዕርቅ ፈጽመዋል በአብዩቱ ላይ አኩርፈው ጫካ የገቡ ወንበዴዎች ናቸው የውንብድና ተግባር የተሰማረ ዘራፊዎች ናቸው አኩርፈው ጫካ የገቡ ወንበዴዎት ጋር አብረዋል በሚሉ ምክንያቶች ከ38ሰው ያላነሰ የተለያየ የወንጀል ፈጸመዋል በሚል ከ3ያላነሰ በአጠቃላይ ጥፋተኛነህ ከተባለት 392 ሰዎችግፍ አገዳደል ውስጥ ከ339 ሰዎች ያላነሱ የተገደለት ፀረ አብዩተኞች በሚል ምክንያት ተይዘው ከተገደሉት ሰዎች ውጪ በሆነ ከፍ ብለው በተጠቀሱት ምክንያቶች መሆኑን ተገንዝበናል።

ስለነበረው መገለጫ ወይም የበታቾች የወሣኔ ሃሣብና የተከሣሹ አቀባበል ብለም ውሣኔ አሰጣጥ ሁኔታ ለአብነት ወስደን ስናየው በተከሣሽ እንዲገደሉ ከተደረጉት ውስጥ፡-

ንጉሤ ወርቅነህ /በ458ኛ ክስ/ ሠርቋል ቤት አቃጥለዋል መንጌ በላይ /በ459ኛ ክስ/ወንበዴ ነው ምስክር እየተሰማበት የነበረው ዳኘው መኮንን ፋናዩ የተባለው ሰው በጩቤ ወግቷል /በክስ 533ኛ/በሚል ጉዳያቸው ከሚታይበት ከፍተኛ ፍ/ቤተ በትዕዛዝ በማስመጣተ መሆኑን ወ/ር ፋንታሁን ተሻገር /502ኛ ክስ/በገበያ ላይ 40 ጅራፍ ተገርፎ 10ዓመት በልዩ ፍ/ቤት ተፈርዶበታል ተብሉ ወህኒ ቤት ከገባ በኋላ በ2ወሩ ውስጥ ከወህኒ ቤቱ ጓሮ ተጉድሉ አስክሬኑ በማዘጋጃ ቤት መወሰዱን አያሌው መለሰ /በ349ኛክስ የተገለፀው ጨው በማስቀመጥ ክስ በከፍተኛ ፍ/ቤት በታየ ጉዳይ ጨው አስቀምጧል በሚል መገደሉ

ተጠርጣሪዎቹ በተለያየ ጊዜ ለምርመራ በተላኩበት ምክንያተ ከባድ ምርመራ ቢደርግባቸውም የተጠረጠሩበት ወንጀል በመካዳቸውና ሌላ ማስረጃ ያላገኙባቸው መሆኑ ይህንኑ በመግለጽ፣

1/ በክስ 110ኛ የተገለፀው ተጉጂ የኔሁን ከበደ ከእስጌሻሉች አምልጫለሁ እያለ ያወራል ተብሉ ስለተነገረበት ተልኮ በ111ኛ ክስ የተመለከተው ተጉጂ ቴዎድሮስ ዋለ እነሻለቃ

ፀሐይ ትክክል ግልባጭ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

መላኩ እና ሻምበል ዘሪሁን አፋኞች ካሉበት ሄዶ ለመተኮስ ሄጂ ሣለ በብዙት የሚሰበስበት ባለማወቂ ተመልሻለሁ ብሉ ዜና አጋይስትና አብርሃም ዘለቀ ለተባሉት አናርኪስቶች ተናግረዋል ተብለ ተልኮ በክሱ 126ኛ የተጠቀሱት ተጉጂዎች እነሰለሞን አብተው 4ሰዎች ኢህአፓ ናቸው ተብለው ተልከው፤

በክስ 142ኛ እነ መስፍን ነጋሽ/ሁለት ሰዎች ኢህአፓ ናቸው ትብለው ተልከው በክሱ 213ኛ የተጠቀሱትን ተጉጂዎች እነ አሰፋ አለማየሁ በእስፔሻሉች ኤርፎርሶች ላይ በተጣለ ጊዜ መንገድ ላይ ሲዘዋወሩ በመገኝታቸው ተይዘው ተልከው በክስ 310ኛ የተገለፀው ደጀው ከበደ/ተጉጂ/ወ/ር ደግፍው ገዳሙ የተባለውን አቁስለዋል ተብሉ ተልኮ በተከሣሾች ላይ በተለያዩ ቀናቶች ከባድ ምርመራ አካሄድን ከመካዳቸውም በኌሁን ከበደ ላይ አሳማኝ ጥቁማ ማግኘት ስላተቻለ በቴዎድሮስ ዋለ ላይ የሚያሳምን ማስረጃ ስላላገኘን ለአብዩታዊ ሂስና እርምት በእነ ሰለሞን አብተው ላይ በአድራጉታቸው የሚያሣምን ማስረጃ ስላላገኘን በእነ መስፍን ነጋሽ ላይ ከየትም አቀጣጫ ምንም ዓይነት ጥቆማ ስላልቀረብልን በእነ አሰፋ ዓለማየሁ ላይ በጥርጣሬ ላይ ከመያዛቸው በስተቀር ለአድራጉታቸው የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ ጀጀው ከበደም አላቆሰልኩም ኢህአፓ አባልም አይደለሁም ብሉ ቃሉን ስለሰጠ በክስ 66ኛ የተገለፀው ተ/ወ/ር አየነወ ፍስሐ የተባለው ተጉጂ አሰሳ በሚደረግበት ጊዜ ሚስጢር በማውጣት እንዲሸሹ የሚያደርግ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ባይገኝም አባቱን አስልኮ ለማስወሰዱ የተመስከረበት ስለሆነ በተመሣሣይ ይፈጽማል ለማለት ስለሚያጠራጥር በክስ 105ኛ የተገለፁት እነ ዘለቀ ሀጉስ ሁለት ተጉጂዎች ኢህአፓ ናቸው ተብለው ተልከው በተለያዩ ቀናት በተደረገው ከባድ ምርመራ ስለካዱ የሰጡትን ቃል አያይዘን ለአስፈላጊው ውሣኔ አቅርበናል ሲሉ መርማሪዎች ባቀረቡት ምርመራ መግለጫ ላይ፤

2/ በክሱ 116ኛ የተገለፀው ተጉጂ ጌታቸው ወይም አዳነ እሸቴ ከአዲስ አበባ ወደ ጉንደር መምጣቱ ቅጥር ነፍሰ ገዳይ ለማቋቋም ይሆናል ተብለ ለምርመራ ተልኮ በ215ኛ ክስ በተጠቀሱት በእነ ታደሰ ገ/እግዚአብሔር ሁለት ተጉጂዎች/ወርቅ ሠሪዎች የነበሩ/ ያለ ይለፍ ሲዘዋወረ ተገኝተው የኢ.ኤል.ኤፍ ና ኢ.ህ.አ.ፓ ሰላዮች ይሆናሉ ተጠርጥረው እንዲሁም በ243ኛ ክስ የተገለፀው ተጉጂ ምትኩ ይፍረ ወ/ስላሴ ኢ.ህ.አ.ፓ ነው ተብሉ ለምርመራ ተልኮ በተለያዩ ቀናቶች በተከሣሾች ላይ ከባድ ምርመራ ብናካሂድም በመካዳቸው ጌታቸው ወይም አዳነ በአስም በሽታ አናቱ ወዳለበት ጉንደር መሄዱን በመግለጽ እነ ታደሰ ገ/እግዚአብሔር በተለይ 1ኛው ከአስመራ በእግሩ ወደ ጉንደር ሥራ ፍለጋ ስሄድ ምንም ጉዳት ሳይደርስበት ሊመጣ የቻለው ከወንበዴዎች ጋር ግንኙነት ያለው ይሆናል ብለን በመጠርጠራችን ስለሆነ እነሱም ስለካዱ ምትኩ ይፍሩም ምንም ፍንጭ ያልሰጠ ስለሆነ ክሱም ስለካደ በክሱ 109ኛ የተገለፀው ተጉጂተስፋ አብዬ ዩሐንስ ዕድሜው 16ዓመት የሆነው ስለሆነ በትምህርትና በማስጠንቀቂያ ሊመለስ ስለሚችል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ተከሾች የሰጡትን ቃል በማያያዝ ለአብዩታዊ ትምህርትና ክባድ ማስጠንቀቂያ አቅርበናል ሲሉ መርማሪዎች ባቀረቡት ምርመራ መግለጫ ላይ የውሣኔ ሀሳቡን ባለመቀበል እንዲገደሉ መወሰኑን ተረድተናል።

በአዘዞና በጠዳ እየተዘዋወረ የገበሬ ማህበራት እንዳይደራጁ አወናብደል ተብሉ ለምርመራ ተልኮ በተለያየ ጊዜ ባደረግነው ክባድ ምርመራ ክዲል ከሕይወት ታሪኩ በተናገረው በ1968 አህያ ሰርቋል ተብሉ ተከሶ ከቀረበ በኋላ በአልታወቀ ምክንያት ተፈትቶ ዉሣኔ ሣያገኝ መቅረቡ የጠቆመ ስለሆነ እንዳየነው አደገኛ ወንጀለኛ በገጠር እየተዘዋወረ አርሶ አደሩን የሚያወናብድ የሚያታልል ያለሥራ የሚኖር ስሙን በመለወጥ የሚጠቀም ስለሆነ ለአብዩታዊ ውሣኔ አቅርበናል በማለት መርማሪዎቹ የካደውን ክስ በራሳቸው ተርጉመው በጥሩነህ ይኸይስ /208ኛ ክስ/ላይ ባቀረቡት ምርመራ መግለጫ ላይ እንዲገደል ወስኖ እንዲፈፀም በፃፈው ላይ የተካደው ክስ ከማመኑም በማስረጃ ተረጋግጧል ካለ በኋላ በስርቆትና ውንብድና ተግባር ተሰማርቶ የሠላማዊ ሕዝብ ሀብትና ንብረት ሊዘረፍ የቆየ ልማደኛና አደገኛ ወንበዴ ለመሆኑ ከአለፈው ታሪኩ መረዳት መቻሉን የገለፀበት ሁኔታ ውሣኔውም የሰጠው በመግለጫው ላይ እስከሆነና በውሣኔው መርማሪዎች ያላቀረቡት ማስረጃ ያቀረብለት ስለመሆኑ ባልተገለፀበት በአፈፀፃም ደብዳቤ በዚህ ሁኔታ መግለጹ ሊበሉዋት የፈለጉዋት አሞራ ጅግራ ብለው ይጠሩዋታል ዓይነት ሁኔታ መሆኑን የሚያሣይ ነው።

የሊቦ አውራጃ አዘአኮ በ267ኛ ክስ የተገለፁትን እነ ያለው አሰፋ 11 ተጉጂዎች ላይ በግርፋትና በእስራት እንዲቀጡ ወስነው እንዲፀደቅላቸው ባቀረቡት ላይ ተከሣሽ የላኩትን ውሣኔ ጠቅሶ በውሣኔው የተጠቀሱትን ግለሰባች ድርጊታቸው ስንገመግመው ፍፁም መሻሻል የማይችሉ ሆነው ስለተገኘ በወንጀለኞች ላይ ለመወሰን በወጣው የዲሲፒሊን መመሪያ መሠረት ለንብረተሰብ ትምህርት ይሰጣል ተብሉ በታመነበት በተለያ ቦታ በመጥቀስ በሕዝብ ፊት በጥይት እንዲመቱ ራሱን በቻለ ውሣኔ በመስጠት አፈፃፀምም ሪፖርት እንዲደረግለት ያዘዘ ሲሆን በክስ 270 እስከ 273ኛ ክስ በተጉጂነት በተጠቀሱት ላይ 24ሰዎች ላይ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ወስነው ቅጣቱንም መፈፀመ ገልፀው ባቀረቡት ሪፖርት ላይ በእሱ ከመጽደቁ በፊት ውሣኔው ማስፈፀማቸው ሣይቃወም ውሣኔው በመቀበል አጽድቆታል።

መርማሪዎቹ በ325ኛ ክስ የተጠቀሰው ተጉጂ ሙሉጌታ አያሌው ጥይት በሰው ላይ ተኩሶ መሣቱ የመግደል ሙከራ ፈጽመዋል ተብሉ ለምርመራ የቀረበላቸውን ሲመርምሩት በመካድ ወደ ሰወ ቤት የገባሁት ሲተኮስ ደንግጨ ነው ሲል የሰጠው ቃል ሌላ ማስረጃ መኖሩን ሣይገልፁ ሮጦ ለማምለጥ ከሰው መኖሪያ ገብቶ እንደተደበቀ መያዙ ወንጀሉን ለመፈፀሙ አያጠራጥርም በማለት በ330ኛ ክስ የተጠቀሱትን ተጉጂዎች ማዕረጉ ድንቁ ሁለት ሰዎች ትምህርት አቋርጠው በመኮብለል እያወናበዱ

ዐቃቤ ትክክል ግልባጭ

259

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ነው ተብለው ለምርመራ ተልከውላቸው በክባድ ቢመረምሩዋቸው ክሱን በመካዳቸውና ማስረጃ ባይገኝባቸውም በሁኔታቻው ሲታዩ ከመጋቢት ወር ጀምሮ ትምህርት አቋርጠው ወደ ገጠር መሰማራታቸው ለውንብድና ተግባር ሳይሆንም አይቀርም በማለት በ345ኛ ክስ የተገለፁትን ተጉጂዎች እነ ዋሴ በላቸው የተባሉት ሁለት ሰዎች ሰው ገድለዋል ተብለው ለምርምራ ተልከው በምርመራ ወቅት የካዱ ሲሆን መርማሪዎቹ ወንጀለኞቹ አደገኛ የሕብረተሰብ ጠንቆች በመሆናቸው እንደሌላው ገበሬ ቢለቀቁ አስቸጋሪ ነው በማለት በ400ኛ ክስ የተገለፀው ጠጋው አዝልቀው/ተጉጂ/የኢ.ዲ.ዩ ወንበዴ የዘረፈው አህያ ይዞ ሲገለገልበት በመገኘቱ ከወንበዴ አብረዋል በማለትና በ323ኛ ክስ የተገለፀወ ተጉጂ አብረሃ ተክለ ለወንዴ መደምሰሻ የተሰጠውን መሣሪያ በብር 400 ሸጠዋል በሚል ለምርመራ ቀርቦላቸው የምርመራ ወጤቱ ለክፍተኛ ፍ/ቤት ይላክ የነበረው ከፀረ -አብዮተኛ ተለይቶ አይታይም በማለት ወደ ተከሣሽ የተከሣሽነት ቃል አያይዘው ለአስፈላጊው ውሣኔ አቅርበናል በማለት በራሳቸው እየተረጉሙ ያቀረቡለትን የምርመራ መግለጫ ይህ ሣያጣራና ሣይጠራጠር እንዳል ተቀብሉ እንዲገደሉ ወስኗል።

በጠቅላላው የአፈፃፀም ሂደት ተከሣሹ /ተከሣሹ/ ምን ሚና እንደነበረው ስንመለከትም በምርመራ ሂደትም ሆነ ውሣኔውን ለማስፈፀም በስልክም በአካል እንዲቀርብለት ያዝ እንደነበረ ውሣኔው በገመድ ወይም ጥይት እንዲገደሉ እና ከ20 እስከ 40 ጅራፍ በሚደርስና መጠኑን በመግለጽ ሁሉም ዓይነት ውሣኔዎች ሕዝብ በተሰበሰበበት ወይም በገበያ ቀንና በጦሩ ፊት እንዲፈፀም ለመፈፀሙም ሪፖርት እንዲደረግለት በጥብቅ ያዛል በአውራጃና ወረዳ ባሉት ከተሞች ጭምር ስማቸውን እየገለፀ እንዲፈፀም ያስተላለፈው ስለመፈፀሙ በሚቀርበወ ራፖርት ላይ ውሣኔው የተፈፀመበት ቀን እንኳ በድንገት ሣይገለጽ ክፍት ሆኖ ካገኘው በሪፖርቱ ላይ የአውራጃው ፖሊስ አዛዥ ይቅረብልኝ እያለ በማዘዝ በጥብቅ ይከታተል እንደነበረ ተረጋግጧል በወህኒ ቤት ግቢ እየተገኘም ሌቦች አምጡልኝ እያለ በፍ/ቤት በቀጠሮ የታሰረትን ሆነ በፍርድ የተሰሩትም ጭምር ከቀረቡለት በኋላ እነዚህ ለህብረተሰቡ አይጠቅሙም ጭንቅላት ጭንቅላቱን አውልቀህ ጣልልኝ እያለ በማዘዝ በቆመበት በአደራጃቸው የተለዩ ሀይሎች/እስፔሻሉች/ ይገደሉ እንደነበረ አስረኛውም ወጥቶ አስከሬኑን እየዞረ እሪ እምሷ እንዲሉ በማዘዝ ያስብል እንደነበ በየትምህር ቤት ሆነ እስረኞች ሲፈታ በሚያደርገው ስብሰባ ጥቆማው ስህተት ነው ብለን አልተውነውም ሰዎቹ እያጣራን ገድልናቸው ይል እንደነበረና የተገረፉት ሆነ የተሰቀሉት በተከሣሹ በፈረመ ዎራንት የታሰሩ በተከሣሹ ብቻ በሚታዘዝ የተለየ ሀይሎች/እስፔሻሉች/ በሚያዙ የሚመረመሩና የሚገደሉ ለብቻቸው በተለየ ታስረው የነበሩ መሆኑን ከምርመራ ሲመለሱ እጅና እግራቸው ተቆራርጦ ይታይ እንደነበረ፣

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

የታሰሩባቸው ቤተሰቦች ለመጠየቅ በሄዱበትም ጊዜ የማየቱ ዕድል የገጠማቸው ከጉናቸው ሲለዩ ጤናማ የነበሩ ልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው እግራቸው ተገርፎና እንክትክት ብለ አብጦ ፋሻና አልኮል አምጡልኝ እያሉቸው እግራቸው ፈራርሶም እየጠመጠመ ያዩዋቸው እንደነበረ እራት ይዘው ሲሄዱም ከ11 እና 12 መኪና ባላነሰ ተጭነው ከሚወሰዱ እስረኞች ውስጥ አይናቸው እያየ የወሰዱትን ስንቅ ሳይሰጡዋቸው ሲወሰዱ የነበረበትና የማየት እድል ያልገጠማቸውን የእስር ቤቱ ጠባቂዎች ሲጠይቁ ለልማት ሃደዋል ወደ አዲስ አበባ ሄደወለዋል እየተባለ ይነገራቸው እንደነበር ጠያቂዎቹ ግን እንዲሞቱ በመረዳት ያለቅሱ እንደነበር ማልቀስ ግን የተከለከለ ስለነበረ ደብደባ ይደርስባቸው እንደነበረ ለግድያ የሚወሰዱ እስረኞች ሁሉጊዜ ከቀኑ 11:30 በኋላ እስረኛ ግባ ተብሉ በመቶ አለቃ አበራ የእስፔሻሉች ሃላፊ በሚመራ የተለዩ ሀይሎች አስቀድሞ ሚስጢር እንዳይወጣ ለልማት እየተባለ በእስረኞች በተቆፈረው ሣሙና በር ለተ/ማረያምና አዘዞ እንደነበረ ወደግድያ ሲወሰዱ በሲጋራ ወረቀት ከ60ሰው ጋር ተገድያለሁ የሚል የፃፍ ሰዓታቸውና ልብሳቸውን መንገድ ላይ እየጣሉ በመሄዳቸው ተገድለው ማደራቸው ሰምቶ ያለቀሰ በእስፔሻል እየታደነ ቤቱ ድረስ ይደበደብና ይታሰር እንደነበረ በመጀመሪያ ለግድያ በመኪና ተጭነው ሲሄዱ ኡኡታና ጩኸት ስለሚያሰሙ ግድያው በገመድ ይፈፀም እንደነበረ በትልቅ ጉድጓድም አስከሬናቸው ይደፋ እንደነበረ በኋላ ግን ገደለው በየእናት አባታቸው ቤት በር በራሳቸው ቤት በር በሚሠሩበት ቦታ በር አዘውትሮ ይጠጣበትነበር በሚባለው በር ሌላ ምክንያት በሞተከ ሰው በተሰበሰበው ሀዘንኛ ፊት እና አስፋልቱ/መንገዱ/ አስከሬኑ ይጥሉን እንደነበር እንዳይነሳ ያየም እንዳያለቅስ እየተጠበቀ ወርጭና ፀሐይ እየተፈራረቀበት ተነፋፍቶ ውሉ የሚነሳበት የሚያድርበት ሁኔታ እንደነበረ ጭንቃላቸው ፈርሶ እግራቸወ አበጠና ቆስሉ ውሻም በልቶት ይታይ እንደነበረ አስቀድመው ሰሚናር ላይ ናቸው በቅዱስ ዩሐንስ ይውጡላቸውል ታሠሩ ነጭ ልብስ ልበሱ ተኳሉ ጨፍረ ሲባሉ የቆየበት ጉዳይ በዚህ ሁኔታ የወደቀ ሬሣ ባዩበት ጊዜ መጥ ተይዛ አዋላጅ እንዳይገባ ተከልክላ የነበረች በድንጋጤ የተገላገችበት ሁኔታና በዚህ ሁኔታ እልል በሉ ሆ በሉ ጨፍረ እየተባሉ መገደዳቸው አእምሮአቸው በሽተኛ ሆነው 3ወር ባልሞላ ጊዜ የሞቱ እናቶች እነደነበሩ አስከሬኑም ለቤተሰብ ሣይሰጥ በመርዝ የተገደሉ ሉሾች የሚቀበሩበትና በገመድ የሚገደሉ ሰዎች የሚቀበሩበት ተወስደው ከጠባቂዎች ጋር እንዲቀበሩ ተነግረዋቸው እንዲቀበሩዋቸው ከ/ዘአኮ ኪ/ምህርት በታች 50 እና 60 ሬሣ የሚይዝ ጉድጓድ ተምሶ የተቀመጠ እንደነበረ በአዘአኮ የተቀበሩበት ጦር ከምኝ የተሠራ በመሆኑ እንዲሁም በሉዛ ማርያም መፀዳጃ ቤትና ቤቶች እንደተሠሩበት ከ1983ዓ/ም በኋላ ተቆፍሮ ከሉዛ ማርያም ወደ 10.000 ጭንቅላት ብቻ መወጣቱና ከሌላም ወደ 1400 አጽም መውጣቱን በአውራጃና በወረዳ ከተሞች ግድያ ይፈፀም

የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ

ስሙ ትክክል ግልባጭ

255

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

እንደነበሩ በወቅቱ በሥራ ላይ የነበሩ ታዘው ሲያስፈፅሙና ሲመለከቱ በነበሩ ምስክሮች ጭምር ተነግረዋል።

ተከሣሹ የፈፀመውና ያስፈፀመው አሰራር ውጤቱ ከሕግ አኳያ ስንመለከተው በማንኛውም አገር ሕዝብን የሚመራ መንግስት የአገሪቱ ዜጐች መብትና ግዴታ አጠባበቅ በሚደነግገው ሕግ መሠረት መብቱን ማስከበር የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣው ዜጋም ለሠራው ሥራ እንዲጠየቅ በሚደነግገው ሕግ እንዲሁም ሥነሥርዓታዊ አፈፃፀም ዳኝነትን ለማየት በሕግ በተቋቋመው አካል እንዲጠየቅ ማድረግና ማስቀጣት ግዴታ እንዳለበት የሕግ መርህ እንደሆነ ለክርክር የሚጋዝብ አይደለም በማንግስት የተሾሙ ሃላፊዎችም በዚህ መሠረት እንዲሰሩ ግዴታ አለባቸወ ከዚህ አንፃር ተከሣሹ የሠራው ሥራ በአዋጅ ቁጥር 129/69 መሠረት ሕጋዊ ነወ ይበል እንጃ ይህንኑ አዋጅ ሆነ ሌሎች አዋጆች/ሕጐች/ ነጭሽብርን ወደቀይሽብር በመለወጥ እንዲገደሉ ለማንም አካል ሥልጣን የሚሰጡ አይደሉም ሰዎች የተገደለትና የተገረፉት መሣሪያ ይዘው እየተዋጉ የተያዙ ሣይሆኑ ከየአለበት ቤት ሥራና መንገድ ባደራጃቸው ሃይሎች ታፍሰው የታሰሩ መቃመዋ የማይችሉ በቁጥጥሩ ስር የነበሩ እንክብካቤ ማግኘ ትና የሕግ ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚገባ የነበሩ ናቸው የተያዙት የተገደለትና የተገረፉት ኢህአፓ፣ኢዲዩ ሕወሐት፣ኢኤልኤፍ እና መኤሶን በሚልና በአጠቃላይ ፀረ ሕዝብ ነው በሚል ነው እንዲሁም ደረቅ ወንጀል የሠሩትም በትዕዛዝና በመመሪያ በራሱ እንዲታዩ በማድረግ ነው ፀረ ሕዝቦች ናቸው አይደለሉም ፀረ ፀዝብ ወይም ወንጀለኛ ሆነው ምን ሠሩ የሚለው መጣራት ያለበት በገለልተኛ አካል ነው ይህንንም ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት ወ/መቅጫ ሕጉና ሥነሥርዓቱን መሠረት በማድረግ ነው ተከሣሹ ግን ድርጊቱን የፈፀመውና የስፈፀመው በአዋጅ የወጣው የመ/ወ/ሕግና ሥነሥርዓቱ ባልተሻረበት ሁኔታ ይህንኑ ሕግ የሚፃረር ትዕዛዝና መመሪያ በማውጣት ነው በዚህ ሕገወጥ ትዕዛዝና መመሪያ መነሻነት በሕጉ የተቀመጡና ዛሬ በተከሣሹ ላይ የቀረበው ክስና የፍርድ ሂደት ስለተጠርጣሪዎች አያያዝና አጠባበቅ ከአካል ጉዳት ነፃ የመሆን እስኪፈርድ ድረስ ንፁሕ ሀኖ የመገመት መብት መኖሪያ ቤትን ያለመደፈር መብትን በአንድ ጉዳይ ሁለት ጊዜ ያለመከሰስ መብትና በገለልተኛ አካል የመዳኘት መብት እንዲሁም ያለሕግ ሕይወትን ያለማጣት መብትን የመሣሠሉትን መሠረታዊ ዓለም አቀፍ ይዘት ያላቸው መብቶችን የሚመለከቱ ድነጋጌዎች በጣስ መልኩ ሰዎች በማንኛ ውም ሰዓት ያለ ፈ/ቤት ትዕዛዝና ፍቃድ እየተያዙ ቤተሰበቻቸው ለአካል ጉዳትና ሞት በሚዳርግ መልኩ ባደራዳቸው ሰዎች እየተደበደቡ በመወሰድ ተጠርጣሪዎቹ ፍ/ቤት ሳይቀርቡ ተከሣሹ በሚኖርበት ቤተ መንግስት ባቋቋመው የምርመራ ክፍል በተለያዩ የቶርች ስልት ተሰቃይተው ቃላቸው እንዲሰጡ እያደረጉ በዚህ መነሻነት የተገኘው ቃል ማስረጃ አድርጉ የካዳትም ሌላ ማስረጃ ሣይቀርበለት ያመነም በሰይፍ የካደም በሰየፍ

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

በሚያስብል መልኩ ተከራክረው ነፃ የሚወጡበት ሁኔታ መኖሩ እንዳለ ሆኖ ጥፋተኛ ሆነው ተገኝቷል ተብለው የመጨረሻውን የቅጣት ጣሪያ ከአምስት ዓመት ጽኑ እስራት በላይ ሚያሳስረው አንድ መለኪያ አረቄ ልብስ አንሶላ ዱቄት በርበሬ ብረት ድስት 85 ሣንቲም አህያ በግ በሬና የመሣሠሉትን ሰርቋል በሚል በፍ/ቤት የተያዘውንም እያስመጣ እንዲገደለ በማድረግና የአገዳደሉም እንዳይታወቅ ይህንን ሥራ የሚሠሩ አካሉችና ሃይሉች በማደራጀት በእሱ ብቻ የሚታዘዙ ከእሱ ዕውቅና ውጪ ሊፈፀም በማይ ችል መልኩ ሥልጣኑን በማመከል እየተቋጣጠረ ድምጽም እንዳይሰማ በኤሌክትሪክ ገመድ የሚገደሉበት ሁኔታ እንዲፈጠር በማስደረግ ማስፈፀሙ የሠራው ወንጀል ከባድና አደገኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

በአጠቃላይ የተከሣሹ የወንጀል አፈፃፀም ባሕርይ በሕግ ላይ ያመፀ ፍ/ቤቶች እንዳይሰረ ያደረገ ኢ-ሰብአዊ የሆነ ድብደባ ቶርች እንዲፈፀምባቸው በማድረግ እንዲገደሉ በሕይወት ያሉትም የሽባነትና ግብረ ሥጋን ግንኙነት መፈፀም ያለምቻል ቋሚ የአካል ጉዳትን ያስከተለ ከእናቱ ጋር ያሰረ ሕፃን ሳይቀር በምርመራ ወቅት መንጭቀው መሬት ላይ በመጣል ዕድሜልኩ በዱላ እስኪሄድ ያደረሰ ቆም እያስቀደለ ተራውን የሚጠባበቀው እስረኛ እሪ እምቢል በል ያስባል ለልማተ እያለ አስቀድሞ በኋላ የሚያለማው ሃይል ገድሎ የሚቀብርበት ጉድጓድ በታሳሪው እያስቆፈረ ገድሉም እስገድሉም በሕጋችን ሬሣን መድፈር የሚያስቀጣ ሆኖ እያለ በቤተዘመዶቻቸው በየሚሠሩበት መ/ቤት በየመንገዱ እየተጣሉ ወርጭና ፀሐይ እንዲፈራረቅባቸው የፈራረሰው ጭንቅላታቸውና እግራቸው ሕዝቡ እንዲያየው ውሻም እንዲበላው መጨረሻም ውለሾች በተቀበሩበት እንዲቀበሩ ያስደረገና በላያቸውም ላይ መፀዳጃ ቤትና ቤት እንዲሰራ ያስደረገ የሥራ ወጤት መሥራቱ የሰው ልጅን ሰብአዊ ክብር ያዋረዳና ያበሳበሰ ጨካኝና ነውረኛነቱን የማያሣይ ተግባር ተገኝቷል።

ተከሣሹ በስህተት ሰው ገድለዋል በዱላ ሰው ገድለዋል የሚልና መገደል ሙከራ የመሣሠሉትን የሚያስቀጡ ናቸው ወይስ አይደለም ብሉ በማጣራት በዚህ ሕግ ከቀረቡት ክስ ከመቶ ስድሳ ሰባት ሰው የላነሰ ነፃ የመሆኑ ተጠቃሚ እንደሆነ ማየት ቀርቶ ከመጀመሪያወም በመደበኛ መታየተ የነበረባቸው ጉዳዩች ማስመጣቱ ለወሣኔ የሚያበቃወ መክንያት በከባድ ምርመራ የሚወጡ መርማሪዎችና ኮሚቴዎች የማስጠይቅ መሆኑን የገለፁለትን ሁሉ ተጨማሪ ማጣራት ሣያደርግ እንዲገደሉ መወሰኑ ለመግደል ምክንያት የማይፈልግ ወጣት የሚባል ሃይል ማየት የማይፈልግ የመግደል ሱስ የተጠናወተው መሆኑን በተለይም የሚፈልገው የጠረጠረውን ብቻ ሣይሆን ቤታቸው ተደፍሮ ከጉያቸው የሚነጠቁትን እናቶች ለምን ብሉ መጠየቅ ነውር ሆኖ በየቤታቸው በር ላይ ወድቀው የፈረሰው አንገላቸውና እግራቸው እያዩ ደንግጦ ማልቀስ በወጉ መሠረት ዘመድ አዝማድ ሰብስቦ ቀብሮ በክብር ማልቀስ ነውር ሆኖ ለአካል ጉዳትና

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ለሞት በሚዳርግ እየተደበደቡ ልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ከውሻ ጋር እየተቀበሩ አዝዞ የሰው ቁራ ሆኖ ያዘዛውን ጐመን አልበላም እርሜነው ዝናም አይደለም ያበቀለው ደም ነው በሚል እንጉርጉሮ ወደ ውስጥ ያለቀሰ የዛሬውን ማረኝ ሁለተኛ አልወልድም እያሉ ቢማፀኑም ሰሚ ጠፍቶ ግድያው ዓመታት ማስቆጠሩ ባልዋ ልጅዋ በአሰቃቂ መገደሉ ልጅ ታስሮ ሲፈታ በማበዱ ያዘነች እናትና የደረሰበት ስቃይ በዓይን ያየች አናትና እንደአቅሙ በዓመት በዓል የቅርጫ ሥጋ የሚበላበት ደስታውን የሚገልጽበት ጊዜ በገመድ የተሰቀለ የሰው ቅርጫ እንድታይ በተደረገበት ሁኔታ ይባስ ብለ ይውጡ ይሉቸዋል ፀጉር ተሰሩ ዘፈኑ ሆ በሉ ተኳሉ ተብሎ መደድ የሰማች ወላድ ሦስት ወር ባልሞላ አእምሮ በሽተኛ ሆኖ እንድትሞት መደረግዋ በሕዝቡ ላይ የወረደ መዓት መሆኑና ለሕዝብ ተብለ ሕዝብ የሚያሰማ ሀይል የሚያጠፋ ወግና ባህሉ የሚደመሰስ በዚህ ሥራው አደገኛ ሠው መሆኑን የሚያሣይ ሥራ የሠራ ሆኖ ተገኝቷል። በአጠቃላይ ተከሣሹ 971 ሰዎችን በግፍ በመግደል እና 83 ሰዎችን ከባድ አካል ጉዳት በማድረስ የፈፀመው የወንጀል ድርጊት ሕግ ብቻ ሣይሆን ለሰው ልጆች ጎሊና እና ማህበራዊ እሴቶች እጅግ በሚክብድና በሚሰቀጥጥ ዘግናኝ ነውረኛ እና ጨካኝነት በተሞላበት ሁኔታ በመሆኑ በተከሣሹ ላይ የሚጣለው ቅጣት ሌሎች እንዲህ ዓይነት ዘግናኝ የወንጀል ድርጊት እንዳይፈጽሙ ለማስተማር ቅጣቱ እጅግ ከብዶ በመጨረሻው ቅጣት ሊቀጣ እንደሚገባ ፍ/ቤቱ ያመነበት ስለሆነ ተከሣሽ ሻለቃ መላኩ ተፈራ በሞት እንደቀጣ በማለት ወስነናል።

ይህ ውሣኔ ተግባራዊ የሚሆነው በአገራቱ ርዕሰ ብሔር ሲፀድቅ ነው። አፈፃፀሙም በማረሚያ ቤት ውስጥ ሰብአዊ ርህራሄ በተሞላበት ሁኔታ እንዲፈፀም በማለት አዘናል። የማዕከል ማ/ቤት በውሣኔው መሠረት እንዲፈጸም አዘናል መዝገቡ ውሣኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቶ ለመ/ቤት ይመለስ ብለናል።

የዳኞች ፊርማ፡-ሰለሞን አረዳ

ሐፊዝ አባጀማል

ረዳኢ በላይ

13/4/98

13/4/98

ወሰደ ትክክል ግልባጭ

258

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ቀን:- 30/3/1998 ዓ.ም
የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት መ/ቁ/ቁ 918/89
የመ98/ወ/ቤት ወ/ቁ 16/87
የመንደኩ ዓይነት ክስ:- ማታለል
የመዝገብ ቁጥር:- ፍርድ

ከፌዴራሉ ጠቅ/ፍ/ቤት
35ኛ መንደፎ ችሎት
ትዕዛዝ ተሰጠ::

ጉዳዩ:- በወ/መ/ሥ/ሥ/ሥ/ቁ 185, 187/1 እና 189 መሠረት የቀረበ ቃለመጠይቅ::

በከሳሽ --- ዕዳ ዐቃቤ ሕግ
እና
በተከሳሽ --- ኃ/ቅ መለሰ = ተፈሪ
በአቶ ተፈሪ የመንደፎ ክስ ጉዳይ ጉዳዩ ቀጠሮ ተሰጥቶ:
የፌዴራሉ ጠቅ/ፍ/ቤት 35ኛ መንደፎ ችሎት ሐምሌ 29ቀን 1998 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በዋለ ትእዛዝ መሠረት:
የሚታወቅ ነው::-

ከመሠረታዊ ነጥቡ ለአዲሱ መሻሻል ቃር በመሆኑ ቃለመጠይቁን ለማከናወን ፍ/ቤት ማቋረጥ ትእዛዝ የሰጠበት ምክንያት ሳይገኝ ተቋርጦ ማቆየቱ ለተከሳሽ መብት ጥበቃ ሲባል ትእዛዝ ተሰጥቶበት ለዕዳ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሥ/ቁጥር 185, 187/1 እና 189 መሠረት ቃላቸውን እንዲሰጡ ትእዛዝ ተሰጥቷል::

ከሠላምታ ጋር

ፈተለወርቅ ኃ/ቅ መለሰ - ዳኛ

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

የከ/መ/ቁ. 03112
ቀን 22-6-98

ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
አዲስ አበባ

በከሣሽ ልዩ ዐቃቤ ህግ እና በተከሣሾች ኃ/ስ/ቅ/ማርያም ተፈራ መካከል ስላለው የ[illegible] ወንጀል ክስ ጉዳይ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት ጉዳዩን አይቶ 29/3 ቀን 1998 ዓ/ም በሰጠው ውሣኔ 15ኛ ተከሣሽ ኃ/ቅ/ማርያም ተፈራ ቅር በመሰኘት በ 30/3/1 ቀን 1998 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ለፍ/ቤት 012-4 ቀን 1998 ዓ/ም ቀርቦ ይግባኝ ስለጠየቀ በጠየቀው መሠረት መዝገቡ ተገለብጦ ፣ ተነቦ በ20-4 ቀን 1998 ዓ/ም ለይግባኝ ባይ እንዲደርሰው ሆኖ ይግባኝ ባይ 18-5 ቀን 1998 ዓ/ም በተፃፈ ለፍ/ቤት በ13-5 ቀን 1998 ዓ.ም. ይግባኝ ቅሬታ ቀረበ፣

1ኛ. የዐቃቤ ህግ የክስ ቻርጅ 29 ገጽ
2ኛ. የይግባኝ ባይ የይግባኝ መጠየቂያ 2 ገጽ
3ኛ. ፍ/ቤቱ በ2/3/1 ቀን እና በ29/3/1998 ቀን የሰጠውን የውሣኔ ግልባጭ 40 ገጽ
4ኛ. የድህነት ማስረጃ 2 ገጽ
5ኛ. የይግባኝ ቅሬታ 7x2=14 ገጽ
በድምሩ 277 ገጽ

የመዝገብ ቁጥር 03112 የሆነውን በውስጡ
1ኛ. በችሎት የተሠራ 720 ገጽ
2ኛ. ልዩ ልዩ አባሪ 1982 ገጽ
በድምሩ 2702 ገጽ

እንደያዘ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አማካይነት መላካችንን እንገልፃለን።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ኮሚሽን ጽ/ቤት ቁ.

ሙያዊ ቦርጋ
የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት
ጊ/ም/ሬጅስትራር

260

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ጥር 18 ቀን 1998 ዓ.ም.

የጥብቅና አገልግሎት ውል

በይግባኝ ባይ ሻለቃ መላኩ ተፈራና በመልስ ሰጭ ልዩ ዓቃቤ ሕግ መካካል ላለው የይግባኝ ክርክር በሻለቃ መላኩ ስም ውል ሰጭ አቶ ፍቅሬ ንጉሤ አድራሻ አዲስ አበባ፣ ወረዳ 17 ቀበሌ 16 የቤት ቁጥር 059 (ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 የቤት ቁጥር 059) እና ውል ተቀባይ የሕግ አማካሪና ጠበቃ ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም አድራሻ አዲስ አበባ ፣ወረዳ 12 ቀበሌ 07 (የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/02) የቤት ቁጥር 1261 በሚከተሉት ሁኔታዎች ተስማምተዋል።

1. ውል ተቀባይ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ውስጥ ያልተካፈሉና ለጉዳዩም አዲስ በመሆናቸው በርካታና ሰፊ የሆነውን ክስና ክርክር በሚገባ አጥንቶ በበቂ ሁኔታ ተዘጋጅቶ ለመከራከር የሚወሰደውን ጊዜና የሚጠይቀውን ጥረት በመመልከት ውል ሰጭ ውል ተቀባይ ለሚሰጡት የሙያ አገልግሎት ጠቅላላ ብር 25.000 (ሃያ አምስት ሺህ) ለመክፈል ተስማምተዋል። ክፍያውም የመጀመሪያ ብር 15.000 (አስራ አምስት ሺህ) የይግባኝ ማመልከቻው ተዘጋጅቶ ሲቀርብ ሁለተኛው ብር 10.000 (አስር ሺህ) ክርክሩ እንደ አስፈላጊነቱ ሰበር ችሎት ጭምር ቀርቦ ሲጠናቀቅ የሚከፈል ይሆናል።

2. ውል ተቀባይም ተገቢውን የምክር፣ የጹሁፍና የቃል ክርክር አገልግሎት ሕግና የሙያ ስነ ምግባር በሚጠይቀው መጠን ለማበርከት፣ ከአቅም በላይ ካልሆነ በቀጠሮ ቀናት ፍርድ ቤት ለመቅረብ፣ በአጠቃላይ ሥራቸውን በትጋትና በታማኝነት ለመሥራት ግዴታ ገብተዋል።

ውል ሰጭና ውል ተቀባይ ይህን ውል ስናቋቁም ቀጥሎ የተመለከቱት ምስክሮች ተገኝተዋል።

ውል ሰጭ

ውል ተቀባይ

መንግሥቱ ኃ/ማርያም አርአያ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ
Mengistu H/mariam Araya
Counsellor & Attorney at Law

ምስክሮች

1. አቶ መሐሪ ኪዳኔ

2. ወ/ት ፍቅርተ ወርቅነህ

ECHR

262

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

በመጨመር. በጥላቻ ስሜት የተደረሱ የማጥላያ ተረቶችን በመጥቀስ የመጨረሻውን የሞት ቅጣት ወስኖብኛል።

እንደ እውነቱ ከሆነ የእግዚአብሔር ፍርድ ስላልታከለበት እንጂ በፍርድ ቤት ሳይሆን በጠላቶቼ ተፈርዶብኝ በጥይት ተደብድቤአለሁ። ከአንድ ዓመት ተኩል በላይ በሆስፒታል የአልጋ ቁራኛ ሆኜ ተሰቃይቻለሁ። ገመምተኛ ሆኜ በሰውነቴ ጥይት ተሸክሜ የሰው ልጅ ከሚሸከመው በላይ የበቀል ድርጊት ተፈጽሞብኛል። ፍርድ ቤቱ ግን ይህን ሁኔታ ማን እንደተኮሰብህ አይታወቅም ወዘተ. በማለት አልፎታል። ነገሩ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ይህ ሁሉ እርምጃ የተወሰደብኝ በምን ምክንያት እንደሆነ ከአጠቃላይ ሁኔታዎች ግምት መውሰድ ይችል ነበር። በዚህም ግምት ላይ ተመስርቶ ቅጣቱን ሊያሻሽልልኝ እና እግዚአብሔር እስከሚጠራኝ ድረስ በንስሐ እንድኖር ሊያደርግ ይችል ነበር።

በፍርድ ሂደቱ ውስጥ ተደረገ የተባለው ነገር ሁሉ እውነት ቢሆን እንኳ ያንን የፈጸመው መላኩ ተፈራ ከዚህ ዓለም ጣጣ በሞት በመገላገል ሳይሆን በዚህች ዓለም ውስጥ አይዞህ ባይ ቤተሰቡን አጥቶ ከነቁስሉ፣ከነስቃዩ፣ከነውርደቱ እየተቀጣ ይገኛል። የስር ፍርድ ቤት የሞት ፍርድ የፈረደው እግዚአብሔር በፈጠረው መላኩ ተፈራ ላይ ሳይሆን በቸርነቱና በማይታወቅ ምስጢሩ ለትንግርት ባቆየው ሁለተኛው መላኩ ተፈራ ላይ ነው። ይህ ሁኔታ በታሪክም፣ በፍትሕም ምክንያት በተለየ ሁኔታ ሊታይ የሚገባው ይመስለኛል።

ይግባኝ ባይ የምጠይቀው ዳኝነት

ከዚህ በላይ ባጭሩ እንዳስቀመጥኩት ፍርድ ቤቱ በእኔ ላይ በዳኝነት ለመቀመጥ የሕግ ድጋፍ የሌለው መሆኑን፣ የቀረበብኝ ማስረጃ ብቃት የሌለው መሆኑን፣ ፈፀምክ የተባልኩትም በመንግሥት አዋጅ እና ትዕዛዝ ላይ ተመስርቼ በሕግ የታዘዘውንና የተፈቀደውን በመሆኑ፣ ቅጣቱን ለማሻሻልም በቂ ምክንያት ስላለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በነጻ እንዲያሰናብተኝ፣ ይህ የሚታለፍ ቢሆን ግን የሞት ቅጣቱን አሻሽሎ ወደ እስራት እንዲለውጥልኝ አመለክታለሁ።

14/06/98

ይግባኝ ባይ

መንግሥቱ ኃ/ማርያም አራያ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ
Mengistu H/mariam Araya
Counsellor & Attorney at Law

FCLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ይግባኝ ባይ እንድከላከል በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው ብይን መሠረት ከጊዜ ርዝመት ነገሮች ስለተረሱኝና በምስክርነት ሊቀርቡ የሚችሉ ሰዎች አድራሻ ማግኘት ስልላቻልኩ፣ አብዛኞቹም ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ፣ በመኖሪያ ቤቴ ተቀምጠው የነበሩ ሠነዶቼ በሙሉ በመወሰዳቸው ማቅረብ የቻልኩት ስማቸው በድርጊት 284 ስር በተጎጂነት ተጠቅሶ የነበረ ምስክሮችን ብቻ ነው። እነርሱም በሚገባ ስለተከላከሉልኝ በድርጊቱ ከመጠየቅ ነጻ ሆኛለሁ።

ዓለም አቀፍ እውቅናና ተቀባይነት የነበረው የደርግ መንግሥት ያወጣቸውን አዋጆችና መመሪያዎች በመከተል ፈጽመሃል የተባልኩትን ድርጊት ፈጽሜም ከሆነ በወቅቱና በሁኔታው አስገዳጅ በሆነ የበላይ ትዕዛዝ መሠረት መሆኑን ገልጬ በዝርዝር ያቀረብኩትን ክርክር የስር ፍርድ ቤት ሳይቀበለኝ ቀርቷል።

4. ከክርክር በፊትና በክርክር ሂደት የደረሰብኝ በደልና ተፅዕኖ

ኢህአዴግና የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ግንቦት 22 ቀን 1983 ዓ.ም. (ማለትም ኢህአዴግ አዲስ አበባ በገባ በሁለተኛው ቀን) ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በውል መሠረት በኪራይ ከያዝኩት ቤት በጦር መሣሪያ ኃይል ከነቤተሰቤ በማስወጣት በውስጡ የነበሩኝ ሠነዶች፣ መጻሕፍት ከፍተኛ የገንዘብ ግምት ያለው ንበረቴ ተወሰዶብኛል።

ከሀገር ተሰድጄ በስደተኛ መጠለያ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ አብረውኝ ይበሉና ይጠጡ በነበሩ የመንግሥት ወኪሎች ጠቋሚነት ታህሣሥ 26 ቀን 1985 ዓ.ም. በድምጽ አልባ አውቶማቲክ መሣሪያዎች በበርካታ ጥይት ተደብድቤ ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል በጅቡቲ ሆስፒታል አራት ጊዜ ጠቅላላ ቀዶ ሕክምና ተደርጎልኝ ከጉዳቴ ሳላገግም ታፍኜ እጅና እግሬን በሰንሰለት ታስሬ ወደ ኢትዮጵያ እንድመለስና እስር ቤት እንድገባ ተደርጌአለሁ።

ተይዤ ከመጣሁበት ጊዜ ጀምሮ በመንግሥት የመገናኛ ቡዙሀን ስብዕናዬን በመንፈግ እንደአውሬ ሲያቀርቡኝ ፣ ከሳሽ ዐቃቤ ሕግም በእኔ ላይ ያዘጋጀውን ክስ በወ/መ/ሕግ ሥ.ሥ.ቁ 136(1) መሠረት በትክክል ያለአድልዎ ማቅረብ ሲገባው (የተቋቋመበት አዋጅ ሥራው ማስቀጣት መሆኑን ብመለከትም) የፈራጅን ሕሊና ሊያዛባ በሚችል፣ የአድማጭን ስሜት በሚዘገንን፣ ጥላቻና በቀል የተላበሰ ቋንቋ በመጠቀም በተገኘው አጋጣሚና የክርክር ምዕራፍ ሁሉ እንድጠላና በሕግ ላይ ያልተመሠረተ ፍርድ እንዲፈረድብኝ አድርጓል። ይህ አፈጻጸም የዓቃቤ ሕግን የሙያ ተግባርና ኃላፊነት የሚጻረርና ተገቢ አለመሆኑን ገልጬ ለፍርድ ቤት ባመለክትም፣ ክርክሬ ምንም ግምት አልተሰጠውም።

የስር ፍርድ ቤት ተወዳዳሪ በሌለው የወንጀል ድርጊት ብዛት መክሰሴን፣ ይህን ከባድ ወንጀል በብቃት ሊከራከርልኝ የሚችል ጠበቃ ለማቆም እኔም ሆንኩ ቤተሰቤ አቅም እንደሌለን ከግምት ውስጥ አስገብቶ ጉዳዬን ለማስረዳት አልፎ አልፎ ሰሜት እየገፋኝ ከስርዓት ለመውጣት የተገደድኩበት አጋጣሚ መኖሩ ባይካድም ሊያርመኝና ሊያስተምረኝ ሲችል ከ1995 ዓ.ም. ጀምሮ ጨርሼ እዳልናገር ገደብ ጥሎብኛል። በሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔም ከተጠቀመበት ቋንቋና ዘለፋ ባልተናነሰ ተችቶብኛል። ይህም አንድ ሰው ተከሶ ቢቀርብም ጥፋተኝነቱ በማስረጃ እስኪረጋገጥ ድረስ ንጹሕ እንደሆነ ይቆጠራል የሚለውን መሠረታዊ የሕግ መርህ የሚጻረር ነው።

5. ቅጣትን በተመለከተ

የስር ፍርድ ቤት ይግባኝ ባይ ያቀረብኩትን የሕግ ክርክር ከግምት ውስጥ ሳያስገባ፣ ለቅጣት ማቅለያ ይረዳኛል በዚ ያስማሁትንም ክምንም ሳይቆጥር የእኔን ክፉ ገጽታ የሚመለከቱና በዓቃቤ ሕጌ የተሰነዘሩ ትጽሎችንና ኃይለቃሎችን በመድገም ራሱም



መንግሥቱ ኃ/ማርያም አርአያ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ
Mengistu H/mariam Araya
Counsellor & Attorney at Law

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ለድርጊቱ ስለባዎች በማዘንና በመወገን ወይም ፈጻሚዎችን በመደገፍ አስሜት ውጭ ሆነው ሚዛናዊ ዳኝነት ለመስጠት ይቸገራሉ ከሚል ነው።

የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የወጣው የጆኖሳይድ ኮንቨንሽን ከፀደቀ ከስምንት ዓመታት በኋላ ነው። ኢትዮጵያ የጂኖሳይድ ኮንቨንሽንን ከተቀበሉትና ካፀደቁት ሀገሮች አንዷ ነች። በመሠረቱም የ1948 ዓ.ም. ሕገመንግሥት ኢትዮጵያ ተካፋይ ከምት ሆንባቸው ከኢንተርናስዮናል ወሎች፣ ከዓለም ስምምነቶችና ግዴታዎች ጋር የበላይ ሕግ እንደሆነ፣ ወደፊት የሚሠሩ ሕጎች፣ ድንጋጌዎች፣ ፍርዶች፣ ውሳኔዎች ሁሉ ከሕገ መንግሥቱ ጋር የማይስማሙ ሲሆኑ ዋጋ የሌላቸውና የማያገለግሉ እንደሆነ በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 122 ላይ ተደንግጓል።

ሕገመንግሥቱ ከፀደቀ ከአንድ ዓመት በኋላ የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በቁጥር 281 የጆኖሳይድ ኮንቨንሽን ከጸደቀበት መንፈስና ይዘት ውጭ (የፖለቲካ ቡድንን) አካትቶ ወጥቷል። ይህም ኢትዮጵያ የተቀበለችውን ኮንቬንሽን የሚቃረን ነው። የዚህ ዓይነት የሕግ ግጭት ቢያጋጥም ምን መደረግ አለበት? ለሚለውም ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ግልጽ ሙያዊ አስተያየት ሰጥቶበታል። ፍርድ ቤቱ እ.ኤ.አ. በግንቦት 28 ቀን 1951 ዓ.ም. ኮንቬንሽኑ የተመሠረተባቸው መርሆዎች በሥልጣኑ መንግሥታት ተቀባይነት ያገኙና ኮንቬንሽኑን ለማክበር ግዴታ ባልገቡ ሀገሮች ጭምር ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ናቸው በማለት አስተያየቱን ሰጥቷል። ከዚህ አንጻር የወ/መ/ሕግ ቁጥር 281 የፖለቲካ ቡድንን "እንዲጨምር ሆኖ መደንገጉ ኮንቬንሽኑን የሚጻረር በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 122 የተደነገገውንም ያልተከተለ ነው። ስለዚህም የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የወ.መ.ሕግ ቁጥር 281ን ድንጋጌ ተላልፎ በተለይም በፖለቲካ ቡድኖች ላይ ወንጀል ፈጽሟል በሚል የሚቀርብላቸውን ክስ ተቀብለው ሊመረምሩ አይገባም፣ ልዩ ዓቃቤ ሕግ የፖለቲካ ቡድን አባላት በመሆናቸው ወንጀል ተፈጽሞባቸዋል ብሎ ያቀረበውን ክስም ሊቀበሉ አይገባም። ከዚህም አንጻር የስር ፍርድ ቤት ክሱን መርምሮ የመወሰን ስልጣን የለውም ተብሎ የቀረበለትን ክርክር ውድቅ ያደረገው በማይገባ ነው።

3. ማስረጃን በተመለከተ

3.1. የልዩ ዓቃቤ ሕግ ማስረጃ

አንድ ተከሳሽ በቀረበበት ክስ ጥፋተኛ ተብሎ እንዲቀጣ ከሳሽ ዓቃቤ ሕግ ክሱን ከማናቸውም ጥርጣሬ በጸዳ ሁኔታ የማስረዳት ግዴታ አለበት። ከሳሽ ያቀረባቸው ምስክሮች ተፋራጅና ተጎጂ የተባሉ በሚመሰክሩበት ጊዜ ይህንኑ ያረጋገጡ፣ በጎንደር፣በአዲስ አበባ በወረዳ 11 ፍርድ ቤት እና በምኒልክ ትምህርት ቤት የማጋለጥ ዘመቻ በጥላቻና በበቀል ስሜት እንዲመሰክሩ የተደረጉ ከዚህም አልፎ የወ/መ/ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 31(1)ን ድንጋጌ በመተላለፍ ማስፈራረት፣ መደለል፣ የተሰፋ ቃል መሰጠት የተፈጸመባቸው መሆኑን አሳይቻለሁ። ፍርድ ቤቱ ግን ሳይቀበለው ቀርቷል። የጹሁፍ ማስረጃዎች በሙሉ ፎቶ ኮፒ ሲሆኑ ከዋናው ጋር የተመሳከሩ ለመሆኑ ማረጋገጫ የላቸውም። ከዋናው ሠነድ ጋር ሊመሳከሩ የማይችሉ ወይም ስለትክክለኛ ነታቸው ደንበኛ የባለሥልጣን ማረጋገጫ በሌለበት ሁኔታም ሠነዶቹ በማስረጃነት ተቀባይነት የላቸውም። በሠነዶቹ ላይ የሚታየው ፊርማ የማን እንደሆነ ያረጋግጣል በሚል የቀረበው የቴክኒክ ሪፖርት ዓቃቤ ሕግ ካቀረበው ጹሁፍ ውጭ በርግጥ በባለሙያ ስለመርመሩ፣ መረመረ የተባለው ባለሙያ ተገቢው የሙያ ዕውቀት ያለው ስለመሆኑ ፍርድ ቤት ቀርቦ ያልተጠየቀና ያልተጣራ በመሆኑ የቴክኒክ ምርመራ ውጤት ነው የተባለው ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም። በዚህ ረገድ በጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጡ ትዕዛዞች በማሳያነት ቀርበው የነበረ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ አልተቀበላቸውም።

3.2. የመከላከያ ማስረጃ

የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር

መንግሥቱ ኃ/ማርያም አርአያ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ
Mengistu H/mariam Araya
Counsellor & Attorney at Law

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ድርጊት 1-3፣ 11፣ 15-74፣ 76 ፣ 79-195 ፣ 197፣ 200-261፣ 264-277፣ 279-292 ድርጊቱ የተፈጸመበትን ስፍራ የማይገልጹ በመሆኑ፣

እንዲሁም ከድርጊት 293-540 በተመለከቱት ድርጊቱ 332፣ 464፣ 465፣ 488፣ 502 እና 508 ድርጊቱ የተፈጸመበትን ወርና ቀን የማይገልጹ በመሆኑ፣ ድርጊት 293-309፣ 311፣ 313፣ 325-328፣ 330-332፣ 334፣ 337፣ 339፣ 341-344፣ 346-354፣ 366-373፣ 375፣ 376፣ 379-385 391-393፣ 394፣ 396፣ 398፣ 402-404፣ 406፣ 407፣ 469-477፣ 479፣ 481-487፣ 489-500፣ 503-516 518-522፣ 525፣ 526፣ 535፣ 540፣ ድርጊቱ የተፈጸመበትን ሥፍራ የማይገልጹ በመሆኑ፣

ከድርጊት 541-605 በተመለከቱት ድርጊት 569-592 ድርጊቱ የተፈጸመበትን ወርና ቀን የማይገልጹ በመሆኑ

ድርጊት 569-592 ድርጊቱ የተፈጸመበትን ሥፍራ የማይገልጹ በመሆኑ ልዩ ዓቃቤ ሕግ ክሱን እንዲያሻሽል፣ ማሻሻል ካልቻለ ክሱ እንዲሰረዝ ለስር ፍርድ ቤት የቀረበው የመቃወሚያ መልስ ውድቅ የተደረገው የይግባኝ ባይን የመከላከያ መብት በማሰጣት ስለሆነ አግባብነት የለውም።

2.2. የተጠቀሰውን አንቀጽ ሕጋዊነት በተመለከተ

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 281 " ዘርን ስለማጥፋት በሰብዓዊ ፍጥረት ላይ ስለሚደረግ ወንጀል" የሚል ርዕስ የተሰጠው ነው። ዘርን ማጥፋት ወይም በእንግሊዝኛው ጄኖሳይድ የሚለው ፅንሰ ሐሣብ ዳብሮ የወጣውና በቀጣይ ትውልዶች ላይ እንዳይደርስ ለመከላከል የሚያስቀጣ ወንጀል ሆኖ የተደነገገው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍፃሜ በኋላ ነው። የዘር ማጥፋት ወንጀል ምን ዝርዝር ሁኔታዎችን ይዞ ሊወጣ ይገባል? የሚለውም የተወሰነው በጊዜው የናዚ ጀርመን ባለሥልጣናት ይሁዳውያንን አስሰው፣ አሳደውና ለቅመው ለመጨረስ፣ ዘራቸው እንዲመተር ለማድረግ ወጥነውና አዘጋጅተው የፈጸሟቸውን ተግባራት መነሻ በማድረግ ነበር።

የተባበሩት መንግሥታት ጉባዔ በዲሴምበር 9 1948 ዓ.ም. ያጸደቀው የጀኖሳይድ ኮንቬንሽን አንቀጽ 2 ለጀኖሳይድ የሰጠው ትርጉም የወንጀል ድርጊቱ ተጎጂዎችን በብሔር፣ በዘር፣ በጎሣ ወይም በእምነት የተሳሰሩ ቡድኖችን ብቻ የሚመለከት ነው።
ለጀኖሳይድ የተሰጠውና እስካሁን ፀንቶ የሚገኘው ትርጉም የፖለቲካ ቡድኖችን አይጨምርም። በተቡዳዮች ዝርዝር ውስጥ የፖለቲካ ቡድኖች ይጨመሩ የሚለው የማሻሻያ ሐሳብ በወቅቱ ለጠቅላላ ጉባዔው ቀርቦ የነበረ ቢሆንም ተቀባይነት ሳይኖረው ቀርቷል። በመሆኑም በቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ የተፈጸመውን ወንጀል ለመዳኘት ኢ.ኤ.አ. በሜይ 3 ቀን 1993 ዓ.ም. በተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀሐፊ በቀረበው ሪፖርት እንዲሁም የፀጥታው ምክር ቤት የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤትን ማቋቋሚያ ቻርተር ያፀደቀበት ውሣኔ ቁጥር 827፣ በተመሳሳይ ሁኔታ በሩዋንዳ የተፈጸመውን የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚዳኝ ፍርድ ቤት ለማቋቋም የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ ቁጥር 955 ላይ ለጀኖሳይድ የተሰጠው ትርጉም ያው በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 2 የተሰጠው ብቻ ነው። የተለወጠ ወይም የተሻሻለ የለም። የፖለቲካ ቡድንም አልተካተተም።

ዘር ማጥፋትና በሰብዓዊ ፍጥረት ላይ የሚፈጸም ወንጀል በመሠረቱና በባህርዩ ዓለም አቀፋዊ ነው። የዓለም መንግሥታት ይህን አመለካከትና አቋም እንዲይዙ የተገደዱት ናዚ ጀርመን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የፈጸመው አሰቃቂ ድንበር ዘለል እልቂት ነበር። ተመሳሳይ እልቂት የሚፈጸምባቸው አጋጣሚዎች ሲፈጠሩም መዳኘት የሚገባው የዓለም መንግሥታት በሚወስዱባቸው የዳኝነት መድረኮች እንዲሆን መሠረታዊ ስምምነት አለ። ይህም በሁለት ምክንያት ነው። አንደኛው ወንጀሉ ከዜግነት አልፎ የሰው ዘርን ሁሉ የሚያስከፋና የሚመለከት ነው ተብሎ ስለሚታመን፣ ሁለተኛውና ትልቁ ግን ድርጊቱ በፈጸመበት ቦታ ይዳኝ ቢባል በዳኝነት የሚሰየሙት ሰዎች

የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማረሚያ ቤትና ፅድ ጥበቃ ማረሚያ ቤት

መንግሥቱ ኃ/ማርያም አራያ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ
Mengistu H/mariam Araya
Counsellor & Attorney at Law

265

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ቋሚ የአካል ጉዳትን ያስከተለ፣ ከእናቱ ጋር የታሰረ ሕጻን ሳይቀር በምርመራ ወቅት መንጭቀው መሬት ላይ በመጣል ዕድሜ ልኩን በዱላ እስኪሄድ ያደረሰ፣ ቆሞ እያስገደለ ተራውን የሚጠባበቀው እስረኛ እሪ እምቢልበል ያስባለ ለልማት እያለ አስቀድሞ በኋላ የሚያለማው ኃይል ገድሎ የሚቀብርበት ጉድጓድ በታሳሪው እያስቆፈረ ገድሎም አስገድሎም በሕጋችን ሬሣን መድፈር የሚያስቀጣ ሆኖ እያለ በቤተዘመዶቻቸው በየሚሰሩበት መ/ቤት፣ በየመንገዱ እየተጣሉ ውርጭና ፀሐይ እንዲፈራረቅባቸው የፈረደ ሰው ጭንቅላታቸውና እግራቸው ሕዝቡ እንዲያየው ውሻም እንዲበላው መጨረሻም ውሾች በተቀበሩበት እንዲቀበሩ ያስደረገና በላያቸው ላይ መፀዳጃ ቤትና ቤት እንዲሰራ ያስደረገ የሥራ ውጤት መሥራቱ የሰው ልጅን ሰብዓዊ ክብር ያዋረደና ያበሳበሰ ጨካኝና ነውረኛነቱን የሚያሳይ ተግባር ተገኝቷል::

. . . ለመግደል ምክንያት የማይፈልግ፣ ወጣት የሚባል ኃይል ማየት የማይፈልግ፣ የመግደል ሱስ የተጠናወተው መሆኑን በተለይም የሚፈልገው የጠረጠረውን ብቻ ሳይሆን ቤታቸው ተደፍሮ ከጉያቸው የሚነጠቁትን እናቶች ለምን ብሎ መጠየቅ ነውር ሆኖ በየቤታቸው በር ላይ ወድቀው የፈረሰው አንጎላቸውንና እግራቸውን እያዩ ደንግጠ ማልቀስ በወጉ መሠረት ዘመድ አዝማድ ሰብስቦ ቀብሮ በክብር ማልቀስ ነውር ሆኖ ለአካል ጉዳትና ለሞት በሚዳርግ እየተደበደቡ ልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ከውሻ ጋር እየተቀበሩ አዘዘ የሰው ቄራ ሆኖ ያዘዘውን ጎመን አልበላም እርሜ ነው፣ ዝናም አይደለም ያበቀለው ደም ነው በሚል እንጉርጉሮ ወደ ውስጥ ያለቀሱ፣ የዛሬውን ማረኝ ሁለተኛ አልወልድም እያሉ ቢማፀኑም ሰሚ ጠፍቶ ግድያው ዓመታት ማስቆጠሩ ባልዋ ልጅዋ በአሰቃቂ መገደሉ ልጅ ታስሮ ሲፈታ በማበዱ ያዘነች እናት የደረሰባት ስቃይ በዓይን እያየች እናትና እንደአቅሙ በዓመት በዓል የቅርጫ ስጋ የሚበላበት ደስታውን የሚገልጽበት ጊዜ በገመድ የተሰቀለ የሰው ቅርጫ እንድታይ በተደረገበት ሁኔታ ይባስ ብሎ ይውጡ ይሏቸዋል፣ ፀጉር ተሰሩ፣ ዝፈኑ፣ ሆ በሉ፣ ተኳሉ ተብሎ መደድ የሰማች ወላድ ሦስት ወር ባልሞላ አእምሮ በሽተኛ ሆና እንድትሞት መደረጓ በሕዝቡ ላይ የወረደ መዓት መሆኑና ለሕዝብ ተብሎ ሕዝብ የሚያሰማ ኃይል የሚያጠፋ ወግና ባህሉ የሚደመሰስ በዚህ ሥራው አደገኛ ሰው መሆኑን የሚያሳይ ሥራ የሠራ ሆኖ ተገኝቷል:: በአጠቃላይ ተከሳሹ 971 ሰዎችን በግፍ በመግደልና 83 ሰዎችን ክባድ አካል ጉዳት በማድረስ የፈጸመው የወንጀል ድርጊት ሕግ ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጆች ህሊና እና ማኅበራዊ እሴቶች እጅግ በሚከብድና በሚሰቀጥጥ ዘግናኝ ነውረኛ እና ጨካኝነት በተሞላበት ሁኔታ በመሆኑ በተከሳሹ ላይ የሚጣለው ቅጣት ሌሎች እንዲህ ዓይነት ዘግናኝ የወንጀል ድርጊት እንዳይፈጽሙ ለማስተማር ቅጣቱ እጅግ ከብዶ በመጨረሻው ቅጣት ሊቀጣ እንደሚገባ ፍርድ ቤቱ ያመነበት ስለሆነ ተከሳሽ ሻለቃ መላኩ ተፈራ በሞት እንዲቀጣ ወስነናል:: " ብሏል::

2. ክሱን በተመለከተ

2.1. የክስ ማመልከቻውን ይዘት በተመለከተ

አንድ ተከሳሽ የተከሰሰበትን ወንጀል ለይቶ ዐውቆ መልስ ለመስጠት እንዲችል እያንዳንዱ ክስ ወንጀሉንና ሁኔታውን፣ ወንጀሉ የተፈጸመበትን ጊዜና ሥፍራ ወ.ዘ.ተ. በዝርዝር መያዝ እንዳለበት በወ/መ/ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 111 እና 112 ላይ በግልጽ ተመልክቷል:: ይህም ማንኛውም ሰው (ሕይወቱን ነፍነቱን ወይም ንብረቱን ያለ ሕግ አያጣም) ከሚለው የ1948 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕገመንግሥት አንቀጽ 43 እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት የዩኤምበር 10 1948 ዓ.ም. የሰብዓዊ መብቶች ዲክላራሽን አንቀጽ 3 የመብት ድንጋጌ የመነጨ ነው:: ልዩ ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ክስ ከድርጊት 1-292 በተመለከቱት ድርጊት 14፣ 18፣ 19፣ 21-59፣ 71፣ 78፣ 79፣ 81-83፣ 90 221፣ 222፣ 257፣ 274 ድርጊቱ የተፈጸመበትን ወርና ቀን የማይገልጹ በመሆኑ፣



ሙ/ሥላሴ ኃ/ማርያም አራያ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ
Mengistu H/mariam Araya
Counsellor & Attorney at Law

ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ተሰጥቶታል። ይህ ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም ሰው በተግባር ማዋል ሕጋዊ ግዴታው ነው። በበላይ ትዕዛዝ ለፈጸምኩት ድርጊት አያስጠይቀኝም፣በትዕዛዙ መሠረት ባልፈጽም ለሕይወቴ ያሰጋኝ ነበር ለሚለው ክርክር ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በመንግሥትነት ቢቋቋምም በአገር ውስጥ በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሕግጋት ስር የተደነገጉትን የሰብዓዊ መብት ሕጎችን በመጣስ የወንጀል ተግባር ከፈጸመ በወንጀል አይጠየቅም ማለት አይደለም። ተከሳሽ ከግብረ አበሮቹ ጋር በሌላ ሕግም ሆነ በአዘአኩ አዋጅ ቁጥር 129/69 በተሰጠው ሥልጣን ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር ይለወጥ በማለት ውሳኔ ማስተላለፍ ሕጋዊ አያሰኘውም። . . ድርጊቱን የፈጸምኩት በሕግ መሠረት ነው ቢልም ይህንን የሚያስረዳለት ማስረጃ ሳያቀርብ የህገራቱን ሕግ በመተላለፍ በፈጸመው የወንጀል ተግባር መከላከያ ሊሆን የማይችል ነው።

ተከሳሹ . . የፈጸመው የወንጀል ተግባር ሊያስወግደው የማይችል መገደድ ስር ሆኖ ለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም፣ ድርጊቱን የፈጸምኩት ታዝገፎ ነው ቢልም ፍጹም መገደድ የሌለበት ሁኔታ የተሰጠው የበላይ ትዕዛዝ ሕገወጥ ድርጊት እንዲፈጸምበት ከሆነ መፈጸም እንደሌለበት የሕግ ግዴታ መኖሩን እያወቀ ለፈጸመው የወንጀል ተግባር ድርጊቱን የፈጸምኩት ታዝገፎ ነው ማለት መከላከያ ሊሆነው የማይችል ስለሆነ አልተቀበልነውም።

ተከሳሹ ቤቱ ተበርብሮ መከላከያ ሊሆነኝ የሚችል ማስረጃ ጠፍቶብኛል ያለ ቢሆንም ምን እንደ ጠፋበት በዝርዝር ባልገለጸበት ሁኔታ ተከሳሹ ማስረጃ ጠፍቶበታል ለማለት አስቀድሞ ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ያረጋገጠበትን አላቀረበም።

ተከሳሹ የመግደል ሙከራ ተፈጽሞብኛል ማለቱ ድርጊቱ ሕገወጥ ቢሆንም የመግደል ሙከራ ኢህአዴግ የፈጸመበት ለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም፣ አድራጊው ከታወቀም ክስ የሚቀርብበት እንጂ መከላከያ ሊሆነው የሚችል አይደለም።

በተከሳሹ ላይ የስም ማጥፋት ወንጀል ተፈጽሞብኛል ይበል እንጂ ማን እንደፈጸመበት አልገለጸም፣ ተፈጽሟል ቢባል እንኳ ስም አጥፊው በሕግ ከመጠየቅ አልፎ ላቀረበበት ክስ መከላከያ አይሆንም፣ ተገቢነትም የለውም፣ በመሆኑም አልተቀበልነውም።

የተደረገውን አጠቃላይ ክርክርና የቀረበውን ማስረጃ በማገናዘብ ፍርድ ቤቱ ሲመዝነው ተከሳሽ በልዩ ዓቃቤ ሕግ ክቀረበበት ክስ ውስጥ በ284ኛ ክስ ከተመለከቱት. . . በስተቀር በሌሎች ተከላከል በተባለባቸው ክሶች በማስረጃ የተነገረበት በማነጣጠር የልዩ ዓቃቤ ሕግን ክስና ማስረጃ በመፈታተን ተቃራኒውን አስረድቶ ማፍረስና ማስተባበል ያልቻለ ሆኖ ተገኝቷል።

በመሆኑም

1. . . . በድምሩ በ579 (አምስት መቶ ሰባ ዘጠኝ) ሰዎች ግድያ በማስፈጸምና ተሳታፊነት ተጠቅሶ በቀረበበት የሕግ አንቀጽ ስር ጥፋተኛ ነው።
2. .. . . . በድምሩ በ392 ሰዎች ግድያ በወ/መ/ሕግ ቁጥር 32(1ለ) እና 522 ስር ጥፋተኛ ነው።
3. . . .. ሆነ ተብሎ ስለተደረገ ከባድ የአካል ጉዳት ወንጀል ክስ ስር በ83 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት በማድረስ ጥፋተኛ ነው በማለት በወ/መ/ሕግ ሥ/ሥ ቁጥር 149 መሠረት ፍርድ ቤቱ ወስኗል። " ብሏል።

<u>የቅጣት ውሳኔ</u>

" በአጠቃላይ ተከሳሹ የወንጀል አፈጻጸም ባሕርይ በሕግ ላይ ያመጸ፣ ፍ/ቤቶች እንዳይሠሩ ያደረገ፣ አስከፊ የሆነ ድብደባ ቶርች እንዲፈፀምባቸው በማድረግ እንዲገደሉ፣ በሕይወት ያሉትም የሚኖሩትና ግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ያለመቻል

መንግሥቱ ኃ/ማርያም አርአያ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ
Mengistu H/mariam Araya
Counsellor & Attorney at Law

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ጥር 18 ቀን 1998 ዓ.ም.

የወ/ይ/መ/ቁጥር

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
አዲስ አበባ

ይግባኝ ባይ . . .ሻለቃ መላኩ ተፈራ

መልስ ሰጭ . . . .ልዩ ዐቃቤ ሕግ

ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት በወ/መ/ቁ 918/89 የኮምፒተር ቁጥር 03112 ሕዳር 02 ቀን 1998 ዓ.ም. በሰጠው የጥፋተኝነት እና ሕዳር 29 ቀን 1998 ዓ.ም. በሰጠው የሞት ቅጣት ውሳኔ ቅር በመሰኘት በወ/መ/ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 185 እና 189 መሠረት የቀረበ ይግባኝ

የይግባኝ ባይ የቅሬታ ነጥቦች

የስር ፍርድ ቤት በሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ " ተከሳሹ ተከላከል ለመባል ያበቁትን በሰውና በሠነድ ማስረጃ የተነገሩበት ድርጊቶች አለመፈጸማቸው ለማስረዳትና ለማስፈረስ ያነጣጠረ መከላከያ ማቅረብ የሚጠበቅበት እንጂ በአባባል ማስተባበል የማይቻለው ስለሆነ ክርክሩን በማስረጃ አስደግፎ ያላስረዳ ስለሆነ አባባሉን የሚገልጹትን የልዩ ዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ለማስተባበል በሕግ እና በማስረጃ ብቃት የተደገፈ ሆኖ ስላላገኘነው ክርክሮቹን ፍ/ቤቱ አልተቀበላቸውም::

በወ/መ/ሕግ ቁጥር 281 ስር የቀረበው ክስ የዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ስለጂኖሳይድ የወሰነውን በሚቃረን መልኩ በስህተት እንዲካተት መደረጉ ከዓለም አቀፍ ሕግና በ1948 ዓ.ም. ከወጣው ሕገ መንግሥት መንፈስ ውጭ በመሆኑ ሊያስከስሰኝ አይችልም፣ ተመሳሳይ ክስ በ1ኛ እና በ6ኛ ወንጀል ችሎቶች እንዲቀርቡ መደረጉ ያለ አግባብ ነው፣ ወንጀሉ የተፈጸመበት ቦታ፣ ሰዓት፣ወርና ቀን አልተገለጸም የሚለውና ከይርጋ ሕግ ጋር በተያያዘ ሆኖ በወ/መ/ሕግ ሥ/ሥ ቁጥር 130 መሠረት ተደርገው መቅረብ ይገባቸው የነበሩ ሆነው የቀረቡትን መቃወሚያዎች ፍርድ ቤቱ ዘርዝ የማጥፋት በሰብዓዊ ፍጥረት የሚፈጸም ወንጀል በሚደነግገው የወ/መ/ሕግ ቁጥር 281 ስር የሚወድቅ ክስ መሆኑን በመቀበልና በወቅቱም ቀርበው የነበሩ መቃወሚያዎችን ውድቅ በማድረግ . . . ክርክሩ ተካሂዶ ከተከሳሽ አስተያየት ጋር እንዲከላከል የሚያደርግ ብይን ከተሰጠ በኋላ የቀረቡ ሆነው ስለተገኙና በመከላከያ መከራከሪያነት ሊቀርቡ የማይገባቸው ሆነው ስለተገኙ ውድቅ እንዲሆን ወስኗል::

በልዩ ዓቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ቀደም ሲል አቅርቧቸው የነበሩ በወቅቱ ታይተው የታለፉትን አሁንም የቀረቡት አልተቀበልናቸውም::
ተከሳሹ በማስረጃነት የጠቀሳቸው በሌላ የክርክር መዝገብ የተሰጡ ውሳኔዎች ክርክሮች በዚህ መዝገብ ለቀረበው አግባብነት ስለሌላቸው አልተቀበልናቸውም::

ደርግ ሕጋዊ መንግሥት ነው የሚሰራባቸው ሕጎች አውጥቷል:: መንግሥት የፖለቲካ ቡድኖችን ዕውቅና አልሰጠም፣ ፀረ-አብዮት ቡድኖች ከወዛደሩ ፓርቲ ውጭ ናቸው:: የአብዮት ዘመቻ አዋጅ የወጣው ፀረ-አብዮተኞችን ለመደምሰስና ለመከላከል ነው፣ ይህን ለመተግበር በሰሜን ጎንደር ክ/ሀገር ቀጠናዊ ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ በሕግ ሥልጣን

ጥር 18 ቀን 98

መንግሥቱ ኃ/ማርያም አርአያ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ
Mengistu H/mariam Araya
Counsellor & Attorney at Law

268

ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

25/08/98

ቁጥር 23776

ለ ጉ-ከማ

በይግባኝ ባይ አቶ ሀሳን ተሬ እና

በመልስ ሰጭ ፅዮ ሀሰን ሃማ መካከል

ስላለው የ ዘር ማጥፋት ወንጀል ይግባኝ ክርክር ጉዳይ ይግባኙ

ሊሰማ ለ ሳንሶ 22 ቀን 1998 ዓ.ም. ስለተቀጠረ ይግባኝ ባዩን

ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ወ/ችሎት ከጥዋቱ በ2:30 ሰዓት ለቃል ክርክር ተዘጋጅቶ

እንድታቀርቡ ፍርድ ቤቱ አዟል።

25/08/98

ጠቅላይ መንግሥቱ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ም/ሬጅስትራር

26/8/98

26-08-98

ECLN

አገራችን ኢትዮጵያ በኤድስ በሽታ በገጠማት ችግር ዙሪያ በግልፅ
በመነጋገር መንቀሳቀስ የእያንዳንዳችን የዜግነት ግዴታ

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ቀን 25/08/98

ቁጥር 23776

ለ ሸዋ ወረዳ ከተማ ፍ/ቤት

ጉ-ጎጠ

በይግባኝ ባይ ፍቅሬ ሠለሞን እና በመልስ

ሰጭ ሸዋ ወረዳ ከተማ መካከል ስላለው የ ሐሬ ማጭ ፈታ

ወንጀል ይግባኝ ክርክር ጉዳይ በ ጥር 18 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ

ማመልከቻ 7 ገጽ ከዚህ ጋር አያይዘን ልከናል።

ስለዚህ ይግባኙ ሊሰማ ለ ግንቦት 22 ቀን 1998 ዓ.ም ስለተቀጠረ ለቃል

ክርክሩ ተዘጋጅተው ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ወንጀል ችሎት ከጥዋቱ 2:30 ሰዓት እንዲቀርቡ

ፍ/ቤቱ አዟል።

ጎሽው መንግሥቱ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ም/ሬጅስትራር
26-08-98

26/8/98

የኤድስ ቫይረስ በደማቸው የሚገኙ ሕሙማንን
ማግለልና መድልዎ ማድረግ አይገባም!!!

170

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ቁጥር 23776
ቀን 26/03/99

ለ ከፍተኛ ፍ/ቤት
ጉራጌ ዞን

በይግባኝ ባይ አቶ ሙሉጌታ ተሰራ እና
በመልስ ሰጭ አቶ መኮንን ሃ/ማ መካከል
ስላለው ፍሬ ነገር ወንጀል ይግባኝ ክርክር ጉዳይ
የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ወ/ችሎት ግንቦት 22 ቀን 199 9 ዓ.ም. በዋለው
ችሎት ጸድቆ ሰጥቷል።

ስለዚህ ተልኮልን የነበረው ቁጥር 03112 መዝገብ የተፈለገበት ጉዳይ ያለቀ
ስለሆነ በችሎት የተሠራ 720 ገጽ ልዩ ልዩ አባሪ 1982 ገጽ በድምሩ 2702 ገጽ
እንደያዘ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልፃለን።

Awol
27/3/99

ስንሽ መ.ር
የፌ ጠቅላይ ፍ/ቤት
ምዝገባ ክፍል ኃላፊ
27-3-99

ECLN



ፍርድ ቤታችን ስለጤንነትዎ ይጨነቃል፣ እባክዎን
ራስዎንና ቤተሰብዎን ከኤች.አይ.ቪ ኤድስ ይጠብቁ !!!

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

ሕዳር 29 ቀን 1999 ዓ.ም.
የወ/ይ/መ/ቁ 23776

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
<u>አዲስ አበባ</u>

ይግባኝ ባይ . . . . . ሻለቃ መላኩ ተፈራ

መልስ ሰጭ . . . . . ልዩ ዓቃቤ ሕግ

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠና ከመረመረ በኋላ ሕዳር 22 ቀን 1999 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ አፅንቷል።

በውሣኔው ቅር የተሰኘን ስለሆነና ለሰበር ሰሚው ችሎት አቤቱታ ማቅረብ ስለምንፈልግ ውሣኔው ተገልብጦ እንዲሰጠን አመለክታለሁ።

የይግባኝ ባይ ጠበቃ
መንግስቱ ኃ/ማርያም አርአያ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ
Mengistu H/mariam Araya
Counsellor & Attorney at Law

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤት

ቁጥር 23776
ቀን 10/04/99

ከሳሽ፡ መሐሪ፡ተፈር.
ለ ፊከተ፡ጣይዓለ፡መሠጣናዊ
ጉ-ከሰሰ

በይግባኝ ባይ ጸሐፊ መሐሪ፡ተፈር፡ — እና በመልስ
ሰጭ ሕጉ፡መኮንን፡ሃ/ማ — መካከል
ስላለው የ ዛር፡መንገሥት — ወንጀል ይግባኝ ክርክር ጉዳይ
የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ወ/ችሎት ሃሌ 22 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው
ችሎት ውሣኔ ሰጥቷል።

ስለዚህ የውሣኔው ትክክል ግልባጭ 11 ገጽ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አያይዘን
የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ለ
17/4/99

ስንዱ ወርቁ
የፌ መቅሳይ ፍ/ቤት
ምዛፎስትራር

የኤድስ ቫይረስ በደማቸው የሚገኙ ሕሙማን
ማግለልና መድልዎ ማድረግ አይገባም!!!

273

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/domestic-case